አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# በጭልጋ ወረዳ የክመንት ማኀበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ

ለሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር የኤም. ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ

በ

ሜሮን ሞላ

አማካሪ

ዘሪሁን አስፋው (ተ/ፕሮፌሰር)

ግንቦት 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# በጭልጋ ወረዳ የክመንት ማኅበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ


## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት ፣የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ፣ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


## የድኅረ ምረቃ መርሀ - ግብር

ለሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር የኤም. ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ


በ

ሜሮን ሞላ

አማካሪ

ዘሪሁን አስፋው (ተ/ፕሮፌሰር)



ግንቦት 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት ፣የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ፣ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሀ - ግብር

### በጭልጋ ወረዳ የክመንት ማኅበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ

በ
ሜሮን ሞላ

### የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

የአማካሪ ስም ______________________ ፊርማ ______________

የውስጥ ፈታኝ ስም ___________________ ፊርማ ______________

የውጭ ፈታኝ ስም ____________________ ፊርማ ______________

ግንቦት 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ምስጋና

ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይሉ ሳገዙኝና ሳበረታቱኝ ለአማካሪዬ ለዘሪሁን አስፋው /ተ/ፕሮፌሰር/ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡

ሳይማሩ ሳስተማሩኝ መሰላል ሆነው ከዚህ ደረጃ ሳደረሱኝ ለአባቴ ለአቶ ሞላ ገላጋይ እና ለእናቴ ለወ/ሮ ይጋርዱ ተስፋዬ ልመናየ የዕድሜ ባለፀጋ ይሁኑልኝ ነው፡፡ እንዲሁም ለወንድሞቼ እና ለእህቶቼ እኔ እንድማር በብዙ መንገድ ሳገዙኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

እዚህ እንድደርስ መሰላል ለሆነኝ ወንድሜ ለወጣት ብዙ አዳም ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡ እንዲሁም በአካልም ይሁን በስልክ በመደወል አይዞሽ በርቺ እያለ ከጎኔ በመሆን ብዙ መረጃዎችን ለሰጠኝ ወንድሜ ለወጣት ክፍለስላሴ አሰፋ መልካሙን ሁሉ እመኝልሀለሁ፡፡ ሌሎችም ለጥናቴ ሰራ መረጃዎችን ለሰጡኝ እና ሳገዙኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ለባለቤቴ መላኩ እንግዳወርቅ እንድማር የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመግዛት፣ እንዳልቸገር ገንዘብ በመስጠት፣ በትራንስፖርት ከምማርበት ቦታ በማመላለስ ሳገዘኝ ውድ ባለቤቴን አአመሰግናለሁ፡፡ ልጆቼ ሆነው ልጄን ይቤላ መላኩን ተንከባክበው ሳሳደጉልኝ ለወንድሞቼ ልጆች ለተማሪ ረድኤት ቢያድግልኝ እና ለተማሪ መስከረም አብራራው ትልቅ ደረጃ እንድትደርሱ ፈጣሪን እለምናለሁ፡፡

በመቀጠል ክፍለ ጊዜዬን በመሸፈን ለተባበሩኝ እና መረጃም ለሰጡኝ ለአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ መሰናዶ ት/ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተለይ ለሴት መምህራን ምስጋናዬ ፈጣሪ መልካሙን ሁሉ ያድርግላችሁ በማለት እመኛለሁ፡፡ በመጨረሻም ለወጣት አዜብ ቦጋለ በፍጥነት ጽፋ ስላደረሰችልኝ ውድ እህቴ እደጊልኝ ብያለሁ፡፡

# *አጠቃሎ*

*ይህ ጥናት በሰሜን ጎንደር ዞን በሚገኘው "በጭልጋ ወረዳ በክመንት ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ" ላይ ያተኮረ ነው፡፡ መረጃዎች የተሰበሰቡት  በተፈጥሮ መቼት ላይ ሲሆን ዘዴዎቹም ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት ናቸው፡፡ በመረጃ ሰጭነት የተሳተፉት ባህሉን፣ ወጉን፣ ልማዱን የሚያውቁት አስር ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች እና አምስት አጋዥ መረጃ ሰጪዎች ሲሆኑ መረጃው በድምጽና በፎቶ ግራፍ ተሰብስቧል፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በጭልጋ ወረዳ በተመረጡ አራት ቀበሌዎች በሚኖሩ የክመንት ማህበረሰብ የሚከወነውን የለቅሶ ስርዓት መግለጽና በገላጭና ተንታኝ ዘዴ በስርዓቱ የሚፈፀሙ ድርጊቶችን፣ የሚባሉ የሙሾ ቃል ግጥሞችን የሚያዘ ቁሳቁሶችንና ምርቃትን መተንተን ነው፡፡ ጥናቱ ክዋኔ /performance/ ንድፈ ሀሳብ እና ስርዓት /Ritual/ ንድፈ ሀሳብን የተከተለ ነው፡፡ ለጥናቱ መረጃ ይገኝባቸዋል ተብሎ የታሰቡት አራቱ ቀበሌዎች ጃልሽም፣ ድኮላጌ፣ ጮንጮቅ እና ስራግና ናቸው፡፡ እነዚህ ቀበሌዎች የተመረጡበት ምክንያት በጃልሽም ቀበሌ የህገ-ልቦና ሃይማኖት ኃላፊ የሆኑት ወንበር አማረ ሙሉነህ መርሻ ሲገኙ ሦስቱ ቀበሌዎች ደግሞ "ከመዘና" ወይም "ገላለካ" የሚባሉት አጋዥ ቄሶች ስለሚገኙ ነው፡፡ ከእነዚህ ቀበሌዎች መካከልም አጋጣሚ በጃልሽም ቀበሌ አንድ የሞት ክስተት በመገኘቱ ስርዓቱን ለመመልከት ተችሏል፡፡ በክመንት የለቅሶ ስርዓት ላይ የሙሾ ቃል ግጥሞች፣ የሚያዙ ቁሳቁሶች የሚቿን ማንነትና ያከናወኗቸውን ተግባራት የሚያንፀባርቁ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በማህበረሰቡ አንድ ህፃን ተወልዶ በስድስተኛ ቀኑ ከሞተ በመንደር አካባቢ በተዘጋጀ የህፃናት መቅበሪያ ደን ውስጥ የሚቀበር መሆኑ ታውቋል፡፡  በመሆኑም የሟች ህፃን እናትም ሀዘንተኛ መሆኗን ለማሳወቅ ከለበሰችው በስተኋላ የህፃኑን ልብስ ቀዶ በመስፋትና ፀጉሯን በክብ ወይም አዙራ የምትሰራ መሆኑ በጥናቱ ተገልጿል፡፡*

# ሙዳዬ ቃላት

| | |
|---|---|
| ህገ ልቦና | በክመንት ማህበረሰብ ያለ የሃይማኖት ዓይነት |
| ምዝሻና | የህገ ልቦና ሃይማኖት ተከታዮች በዓል /በሁለት ሳምንት አንድ ቀን ሀሙስ የሚውል |
| ስንክራ | የአጋዥ ቄስ ሚስት /ለእመቤታችን የሚሰጥ መጠሪያ ስም |
| ሸወን | ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የልመና ፀሎት |
| አመና | መቋደሻ፣ ማቋደስ፣ ማቅመስ |
| አንዘይ | የጌታ ሚስት |
| አንዘይ መርኩ | የእመቤታችን መኖሪያ ማጀት |
| አንዛ | ለእመቤታችን የሚሰጥ መጠሪያ ስም/ የአጋዥ ቄስ ሚስት/ |
| ከመዘና | ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው የህገ ልቦና አጋዥ ቄስ |
| ኪዱስ ምዝሻና | ምስጋና ለእግዚአብሔር ይድረስ |
| ክብር | ለከመዝናው ቄስ ሌላ መጠሪያ ስም የሚሰጠው |
| ይተንቲ | በቅዳሴው ላይ ለከመዘናው አጋዥ የሚሆን የክመንት የህገ-ልቦና ቄስ ሲሆን ኃላፊነቱም በመስዋዕት ሂደቱ ከመዘናው ሲያርድ የሚታረደውን እንስሳ እግሩን በመያዝ የሚያሳርድ ነው፡፡ |
| ድዝና ግቤው | ድህረ ቀብር |
| ድግና | የህገ ልቦና እምነት ተከታዮች መቀበሪያ ቦታ |
| ጀከረንታ | ተላላኪ መላእክት /ቅዱስ ሚካኤል |
| ገወተን ገላለካ | የይተንቲ ሌላ መጠሪያ ስም |
| ግበሩኽ | የህገ ልቦና ሃይማኖት ተከታዮች በዓል (በሁለት ሳምንት አንድ ቀን ሀሙስ የሚውል) |

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና ........ I

አጠቃሎ........ II

ሙዳዬ ቃላት ........ III

ማውጫ ........ IV

የፎቶ ግራፍ ማውጫ ........ VII

1.መግቢያ ........ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 2

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 3

1.3 የጥናቱ ዋና ዓላማ ........ 3

1.3.1 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ........ 3

1.3.2 ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች ........ 3

1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 3

1.5 የጥናቱ ወሰን ........ 4

1.6 የጥናቱ ዘዴ ........ 4

1.7 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ........ 5

1.7.1 ምልከታ ........ 5

1.7.2 ቃለ መጠይቅ ........ 6

1.7.3 ቡድን ተኮር ውይይት ........ 7

1.8 የናሙና አመራረጥ ዘዴ ........ 7

1.9 የመረጃ መተንተኛ መንገድ ........ 7

1.10 የመስክ ክንውን ........ 8

1.11 ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሄ ውሳኔዎች ........ 11
1.11.1 ያጋጠሙ ችግሮች ........ 11
1.11.2 የተወሰዱ መፍትሄዎች ........ 11
2.ክለሳ ድርሳናት ........ 12
2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 12
2.1.1. በለቅሶ ስርዓት ላይ የተደረጉ ጥናቶች ........ 14
2.2 ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝት ........ 16
2.2.1 ስርዓት (Ritual) ........ 16
2.2.2 ሞት ምንድን ነው? ........ 17
2.2.3 የለቅሶ ስርዓት ምንድነው ........ 18
2.2.4 የሙሾ ስርዓት ምንነት ........ 19
2.3 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ........ 20
3.የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ ........ 23
31. የክመንት ማህበረሰብ ስያሜና አመጣጥ ........ 23
3.2 የክመንት ማህበረሰብ ቋንቋ ........ 26
3.3 የክመንት ማህበረሰብ መተዳደሪያ ........ 29
3.4 የክመንት ማህበረሰብ ሃይማኖት ........ 30
3.5 የክመንት ማህበረሰብ ባህላዊ አስተዳደር ........ 35
3.6 የክመንት ባህላዊ እምነት የፀሎት ስነ ስርዓቶች ........ 37
3.6.1 አዳሪ ፊርዳዳ (የጌታ ፊረስ ረገጠ) ታሪካዊ የጸሎት ቦታ ........ 37
3.6.2 ለፀሎቱ ክዋኔ የሚውሉ ቁሳቁሶች ........ 39
3.6.3 የፀሎት ስነ ስርዓት ህግና ደንብ ........ 40
3.6.4 የጸሎት ስነ ስርዓት ቅደም ተከተል ........ 41

3.6.5 የማይፈለጉ ድርጊቶችን የፈፀሙ የሚወገዙበት ስርዓቶች .................... 43

4የክመንት ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ .................... 45

4.1 በክመንት ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ምንነት .................... 45

4.2 የክመንት የመርዶ ለቅሶ ስርዓት .................... 46

4.3 የህጻናት ቅድመ ሞት ክዋኔ (ክዳም ሼው) .................... 47

4.4 የህጻናት የቀብር ጊዜ ክዋኔ (ጊዛ ግቬው) .................... 48

4.5 ለአዋቂዎች የሚደረግ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ .................... 49

4.5.1 ቅድመ ሞት ክዋኔ (ክዳም ሼው) .................... 50

4.5.2 ጊዜ ሞት /ጊዛ ሼው/ .................... 52

4.5.3 ቅድመ ቀብር ክዋኔ /ደቬው ሰኟቬው/ .................... 57

4.5.4 የቀብር ጊዜ /ጊዛ ሼው/ .................... 60

4.5.5 ድህረ ቀብር /ድዝና ግቬው/ .................... 70

4.5.6 የማሳረጊያ /የምርቃት/ ስርዓት .................... 71

4.5.7 ተዝካር (የሙት ዓመት) አከባበር ስነ ስርዓት .................... 72

5 ማጠቃለያ .................... 78

ዋቢ ጽሑፎች .................... 81

አባሪ አንድ፡ የሙሾ ግጥሞች .................... 84

አባሪ ሁለት ለሙት ዓመት አዘጋጆች የተደረገ የምርቃት ስነ ስርዓት .................... 85

አባሪ ሦስት ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች .................... 87

አባሪ አራት ቃለ መጠይቆች .................... 89

# የፎቶ ግራፍ ማውጫ


ፎቶ 1፦ የህገ ልቦና እምነት የበላይ ኃላፊ ወንበር አማረ ሙሉነህ (ፎቶ በአጥኚዋ) ............... 36

ፎቶ 2 የህገ ልቦና ታሪካዊ የፀሎት ቦታ (ፎቶ በአጥኚዋ)........................................................ 39

ፎቶ 3፦ ለአስክሬኑ መከፈኛ የሚሆኑ ቁሳቁሶች ላይ ፀሎት ሲያደርጉ (ፎቶ በአጥኚዋ) .......... 52

ፎቶ 4፦ ገናኞች አስክሬኑን በአቡጀዴ ውስጥ ከተው በሰሌን ሲጠቀልሉት (ፎቶ በአጥኚዋ)... 54

ፎቶ 5፦ አስክሬኑ ከተከፈነ በኋላ ሰባት ቦታ ታስሮ (ፎቶ በአጥኚዋ) ...................................... 55

ፎቶ 6፦ የሚች አስክሬን ከመኖሪያ ቤታቸው ወለል ላይ ሆኖ እጣን እየታጠነ ፍትሃት ሲደረግ....... 56

ፎቶ 7፦ለሀዘንተኛው የተዘጋጀ እንጀራ እና አዋዜ.................................................................. 58

ፎቶ 8፦ የሚች ቤተዘመዶች ካባ ለብሰው ሲያለቅሱ (ፎቶ በአጥኚዋ)....................................... 63

ፎቶ 9፦ የሚቿ ታናሽ እህት ባህላዊ ጥልፍ ቀሚስ ለብሳ ሀዘኗን ስትገልጽ (ፎቶ በአጥኚዋ). 64

ፎቶ 10፦ የሚች የመጨረሻ ልጅ የእናቷን የወገብ መቀነት ለብሳ ስታለቅስ (ፎቶ በአጥኚዋ). 64

ፎቶ 11፦ የሚች ሚስት የባሏን ሱሪ ዘቅዝቃ እና ፎቶውን ይዛ ስታለቅስ (ፎቶ በአጥኚዋ).... 65

ፎቶ 12፦ የልጅ ሚስት የሚችን ጌጣጌጥ ይዛ ስታስለቅስ (ፎቶ በአጥኚዋ)............................. 66

ፎቶ 13፦ የሚች ታላቅ ልጅ ዋንጫ ይዞ ሲያለቅስ (ፎቶ በአጥኝዋ/ ........................................ 67

ፎቶ፡ 14 አስክሬኑ ከመውጣቱ በፊት የሚች ቤተዘመዶች በማልቀስ ላይ (ፎቶ በአጥኚዋ)...... 68

ፎቶ፡ 15 የሚች መቃብር ስፍ /ፎቶ በአጥኝዋ /.................................................................... 70

ፎቶ 16፡ በወንበሩ ከድግናው ቦታ የማሳረጊያ የምርቃት ስነ ስርዓት ሲደረግ (ፎቶ በአጥኚዋ) 71

ፎቶ 17 የነፍስ ይማር እንጀራ ከቀብር ስነ ስርዓት በኋላ ሲበሉ (ፎቶ በአጥኚዋ)................... 72

## 1. መግቢያ

በሀገራችን ሀዘን እንደ ማህበረሰቡ፣ እንደ አካባቢው እና እንደ እምነቱ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል፡፡ የሀዘን መነሻው ሞት ነው፡፡ ሞት ደግሞ ለሰው ልጆች አስከፊ እና ትልቅ ጠባሳ ነው፡፡ በክመንት[1] ማህበረሰብ ከቅድመ ሞት እስከ ድህረ ቀብር የሚደረጉ የአምልኮ ስርዓቶች ክንውን የሚደረጉ ሲሆን የሙት አመት (የተዝካር) አከባበር ላይ ጭምርም የሚደረጉ የአምልኮ ስርዓቶች አሉ፡፡

ማህበረሰቡም እነዚህን ፎክሎራዊ ድርጊቶች ሲያከናውንና ሲተገብር ሁል ጊዜም መልካም ነገር እንደሚያጋጥመው ያምናል፡፡ በክመንት ማህበረሰብ የለቅሶው ስርዓት ጎልቶ የሚታየው በሰልስቱ በሚደረገው ስነ ስርዓት እና በሁለተኛው የቀብር ስነ ስርዓት ወይም ሙት ዓመት በሚባለው ስነ ስርዓት ላይ ነው፡፡ በዚህ ሰዓት የፀሎት ስነ ስርዓት ሲደረግ ሟች መንግስተ ሰማያት ይገባል ተብሎ ይታመናል፡፡

ይህ ጥናት አምስት ምዕራፎችን የያዘ ነው፡፡ በመጀመሪያው ምዕራፍ መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናት ዓላማ፣ የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ዘዴ ተካተዋል፡፡ ምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት እና ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ናቸው፡፡ ምዕራፍ ሦስት የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ ሲሆን ምዕራፍ አራት የመረጃዎችን ትንታኔ የተሰጠበት ነው፡፡ ምዕራፍ አምስት የጥናቱ ማጠቃለያ ቀርቧል፡፡

በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ስር ሰባት ጥናታዊ ጽሑፎች ተቃኝተዋል፡፡ እነዚህ ጥናቶችም በአማራ ብሔረሰብ ላይ ብቻ ትኩረት ያደረጉ ሲሆን አራቱ ጥናቶች በለቅሶ ስነ ስርዓት ላይ እና ሦስቱ ደግሞ በክመንት እምነት ላይ ናቸው፡፡

[1] ይህ ማህበረሰቡ ራሱን የሚጠራበት ስያሜ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ቅማንት በመባልም ይታወቃል፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ይህ ጥናት ያተኮረው በሰሜን ጎንደር ጭልጋ ወረዳ በክመንት ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ላይ ነው፡፡ ጭልጋ ወረዳ ቁጥር አንድ የቅማንት ማህበረሰብ እና ቁጥር ሁለት የአማራ ማህበረሰብ ተብሎ ተከፍሏል፡፡ ጥናቱ በቁጥር አንድ በክመንት ማህበረሰብ ላይ ትኩረት የተደረገ ነው፡፡ በማህበረሰቡ የለቅሶ ስርዓት ላይ የሚባሉና የሚደረጉ የተለያዩ የፎክሎር አይነቶች አሉ፡፡

የክመንት እምነት ተከታይ የነበረ ሰው የክርስትናን እምነት ሲከተል ቆይቶ ከዕለታት አንድ ቀን በዕድሜም ይሁን ካለዕድሜ ሞት ቢመጣ የውስጥ ክንውኑ የሚታየው የክመንት ሃይማኖት ፎክሎራዊ ገፅታን የተላበሰ ነው፡፡ በክመንት እምነት አንድ ህጻናት በተወዱ እስከ ስድስተኛው ቀን ባለው ውስጥ ከሞቱ የሚቀበሩበት ቦታ በመንደር አካባቢ ድግና /መቅበሪያ/ ቦታ ነው፡፡ የመቅበሪያ ቦታው እና የአገናነዝ ስርአቱ ቢለይም የለቅሶ ስርዓቱ ከትልልቅ ሰዎች የለቅሶ ስርዓት ጋር አንድ ነው፡፡ ልዩነቱ በባህሉ የለም፡፡

ለዚህ ጥናት በጭልጋ ወረዳ ቁጥር አንድ ተብሎ በተከፈለው በክመንት ማህበረሰብ 25 ቀበሌዎች ሲኖሩ ከእነዚህ ውስጥም ጥናቱ ትኩረት ያደረገው በአራቱ የገጠር ቀበሌዎች ነው፡፡ እነሱም ጮንጮቅ፣ ድኩላጌ፣ ሰራግና እና ጃልሽም ናቸው፡፡ እነዚህ ቀበሌዎችም የተመረጡት መረጃ ወይም ስርዓተ ክዋኔው ከአራቱም ቀበሌዎች ማግኘት ይቻላል በማለት ነው፡፡ ጀልሽም ቀበሌን የመረጥኩበት ምክንያት የክመንት ሃይማኖት ሃላፊ የሆኑት ወንበር አማረ ሙሉነህ መርሻ የሚባሉት የአያት የቅድመ አያታቸውን እና የአባታቸውን ቋንቋና እምነት ይዘው አሁን ድረስ ያሉ በመሆናቸው ነው፡፡ ሌላው ጮንጮቅ፣ ድኮላጌ፣ ሰራግና የተመረጡበት ምክንያት "ገላለካ" (አጋዥ ቄሶች) የሚባሉት የወንበሩ የበታች የሆኑት ቋንቋቸውን ሳይቀይሩ በየአካባቢው ማህበረሰቡ ሲለመኑ እየዞሩ ፀሎት የሚያደርሱበት ቀበሌዎች ስለሆኑ ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ጥናት ለማድረግ ያነሳሳኝ ምክንያት አንደኛ በክመንት ማሕበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ባለማግኘቴ ነው፡፡ ሁለተኛ ደግሞ የአካባቢውን ባህል ስለማውቀው ለማያውቀው ማህበረሰብ ወጉን ፣ልማዱን፣ባህሉን ለማሳወቅ ጥናት ለማድረግ ተነሳሳሁ፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በጭልጋ ወረዳ በተመረጡ አራት ቀበሌዎች በሚኖሩ የክመንት ማህበረሰብ የሚከወነውን የለቅሶ ስርዓት መግለጽና በገላጭና ተንታኝ ዘዴ በስርዓቱ የሚፈጸሙ ድርጊቶች እና የሚባሉ የሙሾ ቃል ግጥሞችንና ምርቃትን መተንተን ነው፡፡

### 1.3.1 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

- በለቅሶ ስርዓቱ ላይ በየደረጃው የሚታዩትን ክዋኔዎች ማሳየት፣
- በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚያዙ የቁሶችን ትዕምርት መግለፅ፣
- በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚንፀባረቁ የፀሎት ስርዓቶችን መለየት፣
- በለቅሶ ስርዓት ላይ የሚነገሩ ስነቃሎችን ተርጉሞና ተንትኖ ማቅረብ፣

### 1.3.2 ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል ተብሎ ይታሰባል፡፡

- በክማንት ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ምን ይመስላል?
- በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚያዙ የቁሶች ትዕምርት ምንድን ነው?
- በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሙሾ ቃል ግጥሞች ምን ላይ ያተኩራሉ?
- ከለቅሶ ስርዓቱ ጋር ተያይዞ የሚታዩ አምልኮዎች ምን ምን ናቸው?

## 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታመናል፡፡

- የክመንት ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔን ለሌሎች ያስተዋውቃል፡፡
- የክመንት ማህበረሰብ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚያሳየውን አንድነትንና ማህበራዊ ህይወትን ለይቶ ያሳያል፡፡
- የክመንት ማህበረሰብ አባላት በለቅሶ ስርዓቱ ላይ ሃይማኖታቸው፣ ወግ ልማዳቸው እንዴት እንደሚገልጽ ለማወቅ ለሚሹ መረጃ ይሰጣል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በጭልጋ ወረዳ በክመንት ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ላይ ብቻ የሚያተኩር ነው፡፡ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ የመስክ መረጃዎች በተሰበሰበባቸው ቀበሌዎችም የተወሰነ ነው፡፡ በወረዳው ካሉ 25 ቀበሌዎች ውስጥ በአራቱ የገጠር ቀበሌዎች በጮንጮቅ፣ በድኩለጌ፣ በሰራግና እና በጃልሽም ቀበሌዎች ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ ጥናቱ ከለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ውጭ ያሉ የክመንት ባህላዊ ገጽታዎችን አይመለከትም፡፡

## 1.6 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት ያተኮረው ገላጭና ተንታኝ የአጠናን ዘዴን ነው፡፡ ገላጭ ዘዴ አንድን የፎክሎር አይነት ሰብስቦ መግለጽ ላይ ያተኩራል፡፡ "የገላጭ የምርምር ዘዴ ሂደት ተፈጥሯዊ መልክ ያለው ሲሆን ምልከታ ማካሄድም ያዩትን መመዝገብ፣ የዘገቡትን በተገቢው መንገድ መግለፅን ያካትታል" (ያለው፣1998፣ 21)፡፡

በተደረገው ምልከታ የተነገሩ ስነ ቃሎችን፣ የተያዙ ቁሶችንና የተደረጉ አልባሳትን እንዲሁም የእምነቱ ሁኔታ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

በምልከታ፣በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ተኮር ውይይት የሰበሰብኳቸው መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔን ትኩረት በማድረግ የክዋኔ የጥናት ዘዴን ጽንሰ ሀሳብ፣ የክዋኔውን አውድ የሚመለከት" ያለውን ነገር እንዳለ መግለጽ ዋናው ዓላማ" /ያለው 1998፣132/፡፡ መረጃውን የተነተንኩት የክዋኔ /performance/ እና የስርዓትን /Ritual/ ገላጭ /Descriptive/ እና ተንታኝ ዘዴን በመጠቀም በለቅሶው ስርዓት ላይ የሚታዩትን፣ የሚደረጉትን በሙሉ ተንትኖ ማሳየት ነው፡፡ ገላጭ የመተንተኛ ዘዴን የተጠቀምኩት በለቅሶው ስርዓት ላይ የሚያዙትን ቁሳቁሶች ለመተንተን እና የሚደረደሩ ሙሾዎችን ለመተንተን እንዲያመቸኝ ነው፡፡

በትንተና ማህበረሰቡ በለቅሶ ላይ ሀገረሰባዊ ልማዱን እንዴት እንደሚገልፅ፣ በጊዜ ሞት ክዋኔ፣ በቅድመ ቀብር ክዋኔ፣ የቀብር ጌዜ ክዋኔ፣ በድህረ ቀብር ክዋኔ እና በሙት ዓመት የሚያስተላልፋቸውን፣ እንዲሁም በለቅሶ ጊዜ የሚያዙ ቁሳቁሶችን ትዕምርት በመግለጽና በመተንተን ባህላዊ ስርዓቶችን ለማሳየት ነው፡፡

## 1.7 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎች ከቀዳማይና ከካልዓይ ምንጮች የተሰበሰቡ ሲሆን ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ከመስክ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ተኮር ውይይት የተገኙ ናቸው፡፡ ካልዓይ የመረጃ ምንጭ ደግሞ ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ፅንሰ ሀሳቦችና ንድፈ ሀሳቦችን የያዘ ነው፡፡ በተመራማሪዎች ዘንድ አስፈላጊና ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው (ፈቃደ፡ 1991፤90)፡፡

የአንድ ፎክሎራዊ ቅርፅና መልክ እንዲሁም ትክክለኛ ትርጉም በማግኘት ለክዋኔው ትኩረት መስጠት ተገቢ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ምልከታ አይነተኛ መሳሪያ ነው፡፡ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ክዋኔ ከፍተኛ የሆነ ትኩረትና ግንዛቤ ሊሰጠው ይገባል (Finnegan 1992:87)፡፡ በምልከታ ጊዜ ብዥታ የፈጠሩ የክዋኔ መልኮች በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ተኮር ውይይት እንደ አስፈላጊነታቸው ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ደግሞ ፎቶ ካሜራ፣ ቪዲዮ ካሜራ እና ተንቀሳቃሽ ስልክ መቅረጸ ድምፅ ጥቅም ላይ ውለዋል ፈቃደ(1991፤133)፡፡ እነዚህ መሳሪያዎች የተመረጡበት ምክንያት መረጃዎችን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመያዝና ለመሰነድ አመቺ በመሆናቸው ነው፡፡

### 1.7.1 ምልከታ

*ምልከታ በሚደረግበት ሰዓት መረጃ ሰብሳቢው ሰው ከሚፈልግባቸው ተጠኚዎች ጋር ወይም አካባቢ በመሆን የሚያደርጉትንና የሚናገሩትን ነገር በቅርበት ሆኖ እያየ እና እየሰማ በመዝገብ መረጃ የሚሰበስብበት መሳሪያ ነው፡፡ /ያለው 1998፤ 182-183/*

ምልከታ በጣም አስፈላጊና የማይቀር የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ ምልከታ አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከወን አጥኚው በቀጥታ አውዱን በመመልከት በዓይን እይቶ በጆሮ ሰምቶ መረጃውን የሚሰበስብበት ዘዴ ነው፡፡

> *The term observation, as used in this context, is not limited only to visual aspects of the situation, but also involves a full range of sensual experience including bearing, teeling, smelling and tasting, whenever these may be approapriate (Goldstein; ፣ 1964፡77).*

ምልከታ በቀላሉ የመቼቱንና የሰዎችን አጠቃላይ እንቅስቃሴ መመልከትና መከታተል ማንነታቸውንና የሚሰጡትን ትርጓሜ መረዳት የሚያስችል ነው፡፡ ምልከታ በተፈጥሮው አውድ ላይ በአካል በመገኘት ድባቡን፣ የአልቃሹን እንቅስቃሴ፣ ሚችን በምን መንገድ እንደሚገልጿቸው፣ በለቅሶው ላይ የሚያዙ ቁሳቁሶች፣ አልባሳት፣ የለቅሶው ረገዳ፣ የአቀባይና የተቀባይ፣ የቃል ግጥም አደራደር የድምፅ አወጣጥ፣ የፊት መከፋት፣ ማዘን፣ መደንገጥ፣ የእንባ ማፍሰስ፣ ደረት መምታት፣ መውደቅ መነሳት የሚለውን በሙሉ መመልከት ያስችላል፡፡

### 1.7.2 ቃለ መጠይቅ

ለቃለ መጠይቅ Gray እንዲህ በማለት ገልጸውታል፡፡

> *An interview is a conversation between people in which one person has the role of researcher. Very often, the interviewer will have on hand a set of written questions which are posed in a structured and methodical fashion /Gray, 2004, 213)*

ቃለ መጠይቅ ጠያቂው ተጠያቂውን ፊት ለፊት በማነጋገር የተፈለገው ግብ መቺ መረጃ እንዲሰጥበት የሚደረግ ነው፡፡ ቃለ መጠይቅ በምልከታ ጊዜ ግልፅነት የጎደለውን የመረጃ ክፍተት ለመሙላት የሚጠቅም የመረጃ ዘዴ ነው(Goldstein; 1964:103)፡፡ ስርዓቱን ጠብቆ የተዋቀረ ቃለ መጠይቅ ማህበረሰቡ ለኑሮው የሚሰጠውን ፍቺ ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ያስገኛል፡፡

በዚህ ጥናት የተጠቀምኩት ነፃ ቃለ መጠይቅ ሲሆን ለአጥኚውም ለመረጃ ሰጪዎች ያልተገደበ ነፃነት በመስጠት ስለተጠየቁት ጉዳይ የፈለጉትን ያህል እንዲናገሩ እድል ፈጣሪ ነው፡፡ ነፃ ቃለ መጠይቅ ጠያቂው በሚያጠናው ችግር ዙሪያ ጠቃሚ ማስረጃ ያስገኙልኛል ብሎ የሚያስባቸውን ጥያቄዎች በፈለገውና ለተጠያቂው ይመቻል ብሎ ባሰበው መንገድ ማቅረብ የሚችልበት ተጠያቂው ደግሞ ነፃ መልስ ይሆናል ብሎ የሚገምታቸውን እና ያመነውን መረጃ የሚሰጥበት ነው (ያለው፤ 180)፡፡

ቃለ መጠይቅ ያደረኩላቸው ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ስምንት ወንዶች እና ሁለት ሴቶች ናቸው፡፡ አምስት ደግሞ አጋዥ መረጃ አቀባዮች ሲሆኑ ክመንተኛም አማርኛም የሚችሉ ናቸው፡፡

### 1.7.3 ቡድን ተኮር ውይይት

ቡድን ተኮር ውይይት በቂ መረጃ ይኖራቸዋል ተብሎ የታሰቡ ሰዎችን በመምረጥ በሚነሳው ጥያቄ ዙሪያ እየተወያዩ መረጃ እንዲሰጡ የሚደረግበት ዘዴ ነው፡፡ ተሳታፊዎችም እስከ 12 ሊደርሱ ይችላሉ (ያለው 1998፤191) በማለት ገልፀዋል፡፡

የቡድን ተኮር  ውይይት በተወሰኑ ሰዎች መካከል የሀሳብ ቅብብሎሽ የሚካሄድበት ነው፡፡ ለዚህ ጥናት በትልልቅ ሰዎችና በወጣቶች መካከል ተደርጓል፡፡ የተካሄዱትም ሶስት ቡድን ተኮር ውይይቶች ናቸው፡፡ አንደኛው እምነቱን፣ ታሪኩን፣ ባህሉን፣ ወጉን፣ ልማዱን ቋንቋውን ጠለቅ ብለው በሚያውቁት የዕድሜ ባለፀጋ በሆኑ አራት የክመንት ሃይማኖት አባቶች ነው፡፡ ከአራቱ ውስጥ አንደኛው የክመንት ሃይማኖት መሪ ወይም ወንበር ሲሆኑ፣ ሦስቱ አጋዥ ቄሶች /ከመዘና/ የሚባሉት ናቸው፡፡

ሁለተኛው ቡድን ተኮር ውይይት ስድስት ሰዎችን የያዘ ሲሆን እነሱም ቀደም ሲል የክመንት ሃይማኖት ተከታይ የነበሩና ወደ ክርስትና ሃይማኖት የገቡ ናቸው፡፡ ሁለቱ ሴቶችም በእምነቱ ላይ የነበሩ የቤት እመቤት ሲሆኑ ሶስቱ ደግሞ ወጣቶችና  የአካባቢው ጸጥታ አስከባሪዎች ናቸው፡፡

## 1.8 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

መረጃ ሰጪዎች የተመረጡት በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ነው፡፡ በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ስልት "ተሳታፊዎቹ የተመረጡት ከጥናቱ ዓላማ አንፃር ነው፡፡ በግዴለሽነት የተገኘ ሰው ሳይሆን ለጥናቱ ዓላማ ተጨባጭ መሆንና ሀሳብ በመስጠት ይጠቅማሉ ተብለው የታሰቡ ተሳታፊዎችን የመምረጥ ስልት ነው" /ያለው 1998፤ 132/ ይገልጻሉ፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ መረጃ አቀባዮች አስራ አምስት ሲሆኑ፤ በዕድሜ ከፍ ያሉና ወጣት የሚባሉ ናቸው፡፡

## 1.9 የመረጃ መተንተኛ መንገድ

ጥናቱ ትኩረት ያደረገው "በለቅሶ ስርዓት ክዋኔ" ላይ ሲሆን የቀረበበት መንገድም በገላጭ እና ተንታኝ ዘዴ ነው፡፡ ጥናቱ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን ይህም ዘዴ "በአንድ ውስን ቦታ ስለተከሰተ ችግር ወይም ስለሚከናወን ሂደት ጠንካራ፣ ሰፊና የዳበረ ማብራሪያ የሚሰጥ ነው" (ያለው 1998፡410)፡፡

## 1.10 የመስክ ክንውን

በጭልጋ ወረዳ በማንነት ጥያቄ ከጥቅምት 24 እስከ ጥር 20 ቀን 2011 ዓ.ም በነበረው የእርስ በርስ ግጭት ምክንያት ወደ መስክ መሄድ ስላልቻልኩ ካለሁበት አዲስ አበባ ሆኜ ነገሮችን እዛው ቦታው ላይ ከሚሰሩ የመንግስት ሰራተኞች ጋር ግጭቱ መቆም አለማቆሙን ስልክ በመደወል እያጣራሁ ቆየሁ፡፡

በዚህ ምክንያት ከመንግስት ሰራተኞች ጋር ደግሜ በህዳር ባሉት ቀናቶች እየደጋገምኩ ስደውል ብጥብጡ አላቆመም ይሉኛል፤ በመሀል እየደወልኩ ስጠይቅ ግጭቱ እየተባባሰ እስከ ታህሳስ 30 ቀጠለ፡፡ ቦታው ላይ ያሉ ሰዎችም ጥር 15 ቀን ደውለው ግጭቱ እንደቀነሰ ነገሩኝ፡፡

የመጨረሻ ጥር 25 ስደውልላቸው አሁን መምጣት ትችያለሽ፤ ሁሉም ነገር ተረጋግቷል አሉኝ፡፡ እኔም ከምሰራበት መስሪያ ቤት ለ20 ቀናት አስፈቅጄ የምወስዳቸውን ቁሳቁሶች ጥር 29 ቀን 2011 ዓ.ም አዘጋጀሁ፡፡

ከትምህርት ክፍሉ የተሰጠኝን የድጋፍ ደብዳቤ ይዤ ወደ መስኩ ልሄድ መሆኔን ለአማካሪዬ ነገርኳቸው፡፡ እሳቸውም መረጃ ስትሰበስቢ እያንዳንዷን ጥንቃቄ በተሞላበት ጥቃቅን ነገር ሳታስቀሪ የተባለውን በሙሉ ሰብስበሽ እንድትይዢ በማለት ምክር ሰጡኝና ተሰነባበትን፡፡

የካቲት 1 ቀን 2011 ዓ.ም የአውቶብስ ትኬት ቆርጬ የካቲት 2 ቀን 2011 ዓ.ም ወደ ባህር ዳር ጉዞ አድርጌ ከቀኑ 12:00 ሰዓት ባህር ዳር ገባሁ፡፡ ከዘመድ ቤት አድሬ የካቲት 3 ቀን 2011 ዓ.ም በጠዋት ተነስቼ ወደ ጎንደር ጉዞ ጀመርኩ፡፡ በመቀጠል ጎንደር ከቀኑ 10:00 ሰዓት ከደረስን በኋላ እኔም ጥናቴን ወደማረግበት ስፍራ ወደ ጭልጋ ለመሄድ ስለመሸብኝ ከዘመድ ቤት አድሬ ሁሉንም ጉዳይ በደንብ ካጠራሁና ከጠየኩ በኋላ በ04/6/2011 ዓ.ም ወደ ጭልጋ ጉዞዬን ቀጠልኩ፡፡ ከቤተሰቦቼ ጋር ያለውን ችግር በሙሉ ከተነጋገርኩ በኋላ ጥናቴን ከማካሄድበት ቦታ ሁለቱን ወንድሞቼን ቢያድግልኝ ሞላ እና መልካሙ ሞላን በመያዝ ከነሱ ጋር በ05 ቀን 2011 ዓ.ም በጠዋቱ ምርት አምባ ከምትባል ቀበሌ ወደ ዋናው ጭልጋ 2:00 ሰዓት በእግራችን ተጉዘን ደረስን፡፡ ጭልጋ ከደረስን በኋላ ከወረዳው አስተዳዳሪ ቢሮ ገብቼ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለጥናት የመጣሁ ተማሪ መሆኔን በመግለጽ ከክፍሌ የተሰጠኝን ደብዳቤ አሳየሁ፡፡ በጥርጣሬ አይን ሲመለከቱኝም 25 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ከምትገኝ ምርት አምባ ቀበሌ ነው ተወልጄ ያደኩት አልኳቸው፡፡ እሳቸውም ጊዜው አስተማማኝ ስላልሆነ ነው ጥያቄ ያበዛሁብሽ አሉኝና የምፈልገውን ደብዳቤ ጽፈው ሰጡኝ፡፡ ወንድሞቼን ይዤ 05/06/2011 ዓ.ም

ወዲያውኑ ወደ ጃልሽም ቀበሌ የክመንት ሃይማኖት ሃላፊ ወደሆኑት ወንበር አማረ ሙሉነህ መርሻ ከቀኑ 7፡00 ተነስተን ወዲያውኑ በ8፡30 ሰዓት ደረስን፡፡

አባ ወንበሩንም ከቤታቸው ከደረስን በኋላ በአጋጣሚ ቤታቸው ውስጥ ቁጭ ብለው አገኘናቸው፡፡ ከየት ነው የመጣሽው በማለት ጠየቁኝ፡፡ እኔም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ መሆኔንና የክመንት የለቅሶ ስርዓት ለማጥናት መምጣቴን ገለጸኩላቸው አመኑ፡፡ እሳቸውም እኔ እየተፈለኩ ነው በማለት ወጋቸውን ቀጠሉ፡፡ ታላቁ ወንድሜም ቀጠል አደረገና ለምን ሲሏቸው ዋናው የክመንት ነገር አጫሪ ነህ በማለት ነገሩን፡፡ እኔም ወዲያውኑ ጥያቄ ስጠይቅዎት የድምፅ ቀረጻ አደርጋለሁ ስላቸው፤ ለእኔ ድምፅ መቅረጽ ፎቶ መነሳት አዲሴ አይደለም፤ በማለት መለሱልኝ፡፡ እኔም ስለ ክመንት ማህበረሰብ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ፣ አመጣጡን፣ ወግ፣ ልማዱን፣ ባህሉን፣ ታሪኩን፣ እምነቱን በሙሉ ስጠይቃቸው ፈቃደኛ በመሆን ለ1፡30 የድምጽ ቀረጻ አደረኩ፡፡ የድምጽ ቀረጻውን ካከናወንኩ በኋላ 10፡30 ከጃልሽም ቀበሌ ተነስተን 12፡00 እያዘገምን ከዘመድ ቤት አይከል ከተማው ደርሰን ገብተን አደርን፡፡

ወንድሞቼም በማግስቱ የካቲት 6 ቀን 2011 በከተማ መንቀሳቀስ ስለማይቻል ወደ ቀያቸው ተመለሱ፡፡ እነሱንም ሌሎች የአካባቢውን ማህበረሰብ በሙሉ ሰው በሰው በመላክ እግዚአብሔር በቃህ ያለው ሰው ካለ እና የታመመ ሰው ካለ እንድትደውሉልኝ በማለት ነገርኳቸው፡፡ እኔም አይከል ከከተማው ሆኜ የምፈልጋቸውን መረጃዎችን ሰበሰብኩ፡፡

ይህን ሁሉ መረጃ ስሰበስብ ከወረዳው የተጻፈልኝን ደብዳቤ በመያዝና በማሳየት ነው፡፡ ምክንያቱም በወረዳው በነበረው ችግር በሰዓቱ መንቀሳቀስም አልቻልኩም ነበር፡፡ ምክንያቱም በወረዳው ህጋዊ ያልሆነ ሰው ሲንቀሳቀስ ከታየ ልዩ ኃይል የሚባሉት ፀጥታ አስከባሪዎች በጠቋሚም ይሁን በራሳቸው ይሆናል በማለት ያገኙትን ሰው ስለሚመቱና ስለሚገድሉ መንቀሳቀስ አይቻልም ነበር፡፡ ከአይከል ከተማ 18 ኪ.ሜ ርቃ የምትገኝ ጮነጮቅ የገጠር ከተማ በ09 /2011 ዓ.ም አቶ መኮንን ፈንቲ የሚባሉ ሰውዬ አርፈዋልና ድረሺ ሲሉኝ መኪና መንገድ ስላለው ከጭልጋ ከተማ እስከ ጮንጮቅ በኮንትራት ባጃጅ ሄጄ ከደረስኩ በኋላ የደወለልኝን የቀበሌውን ፀጥታ አስከባሪ የሆነው አቶ አስቻለው ቀናውን አገኘሁት፡፡

እኔም የለቅሶው ስነ ስርዓት እዛው ጮንጮቅ መስሎኝ የቀበሌውን ፀጥታ አስከባሪ አስቻለው ቀናውን ስጠይቀው ከጮንጮቅ 30 ኪ.ሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ባስድበብ የሚባል ቀበሌ ነው ሲለኝ እኔም በፍጥነት እንሂድ ስለው መሄድ አትችይም በጣም ገደል ነው አንሻራትተሽ ከወደቅሽ አትመለሽም፤ እንደገና ከደረሰሽ በኋላም እንደ ህንፃ ቤት ወደ ላይ የቆመ ነው፤

መመለስ አትችይም ሲለኝ እኔም ለህይወቴ ፈርቼ ቀረሁ። ከገጠር ወደ ከተማ ከሆነችው ጮንጮቅ አንድ አንድ የክመንት ሃይማኖት ተከታይ ሆነው ወደ ክርስትና ሃይማኖት የተቀየሩትን ግለሰቦች ስለ ባህሉ፣ ስለ እምነቱ ወይም ስለ ህገ ልቦና ምንነት ያለውን በሙሉ በቀን 10/06/2011 በቡድን ውይይት መረጃ ሰበሰብኩ።

በተጨማሪም በ13/2011 ዓ.ም ብስለት የክመንት ቄሶች እና ከሌሎች ወንዶችና ሴቶች ቡድን ተኮር ውይይት አደረግሁ። በ17/2011 ዓ.ም ከለሊቱ 11:00 ሊነጋጋ አካባቢ ጃልሽም ከሚባል ቀበሌ ስልክ ተደውሎ የ75 ዓመት አዛውንት እማሆይ አዋጋሽ አበራ የሚባሉ አርፈዋልና ቶሎ ድረሽ ተብሎ ተነገረኝ። ከጠዋቱ 1:30 ከለቅሶው ቤት ደረስን። አባ ወንበሩን መጀመሪያ ተዋውቂያቸው ስለነበር የአስክሬኑን ቦታ ሲጠቁሙኝ ከሟች ቤት ጓሮ ከተሰራው ዳስ ገብቼ ሀዘንተኞችን በእናታቸው ሞት ማዘኔን ገለፅኩላቸው። በወንበር አማረ ሙሉነህ አማካይነት አስክሬኑ ወዳለበት ገብቼ ማየት እንድችል የሟችን ዘመዶች አስፍቀደው የፀሎት ስነ ስርዓቱን ተመለከትኩ።

በመስክ ስራው ወቅት በተፈጥሮ መቼት የቅሶ ስርዓት ክዋኔ ላይ ተገኝቼ መረጃዎችን በማስታወሻ ደብተር ይዤያለሁ። የለቅሶ ስርዓቱ መቼ፣ የት፣ በማን፣ ለማን፣ በምን፣ እንዴት እንደተከናወነ ገልጫለሁ።

በመስክ ዙሪያ የተያዙት ማስታወሻዎች በሙሉ በስርዓት ተደራጅተው ተይዘዋል። በመቅረጸ ድምፅ፣ በፎቶ ግራፍ የተሰበሰቡትን ለራስ ለራሳቸው መለያ ቁጥር በመስጠት አደራጅቻለሁ። በመቅረጸ ድምፅ የተቀረፁትን ድምፆች ከክመንተኛ ቋንቋ ወደ አማርኛ ቋንቋ በዛው በቋንቋው ተናጋሪዎች በማስተርጎም ጥቅም ላይ ይውላሉ የተባሉትን ወደ ጽሑፍ ቀይሬ አስቀምጫለሁ። በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የተባሉትን፣ የተነገሩትን፣ የተሰሙትን፣ የታዩትን በሙሉ ሰፊ በሆነ ትንተና ሰጥቼበታለሁ። በመጨረሻም በ19/06/2011 ቀጥታ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ።

## 1.11 ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሄ ውሳኔዎች

### 1.11.1 ያጋጠሙ ችግሮች

በአካባቢው የማንነት ጥያቄን ሰበብ በማድረግ የእርስ በርስ ግጭት በመፈጠሩ ለጥናቴ መረጃ ለመሰብሰብ ጭንቀት ፈጥሮብኝ ነበር፡፡ እኔም ችግሩን እቋቋማለሁ በማለት ቦታው ላይ ተገኘቼ መረጃ ሰጪዎችን ስጠይቃቸው መጀመሪያ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ የሰጡኝ ምክንያትም "የብሔርን ጥያቄ መነሻ በማድረግ እንደፈለግን ሀሳባችንን በነፃነት ለመግለጽ አላስቻሉንም፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ በተለያየ ምክንያት እየመጡ ስለ ክመንት ማህበረሰብ ጥናት ልናጠና ነው በማለት ቃለ መጠይቅ እያደረጉ የክመንትን እምነት፣ ባህሉን፣ ወጉን፣ ልማዱን ሰንደን ለማስቀመጥ ነው በማለት ይወስዳሉ፤ የወሰዱትንም መልሰው አያሳዩንም" የሚል ነው፡፡

መረጃ ሰጪዎች የሚገኙት በተለያዩ ቀበሌዎች በመሆናቸው የመጀመሪያውን የለቅሶ ስርዓት ሄጄ ለማከናወን አካባቢው ዳገታማ፣ ቁልቁለት እና ገደላማ በመሆኑ ሳልሄድ ቀርቻለሁ፡፡ ሁለተኛውን የለቅሶ ስርዓት ክንውን አስክሬኑ ታጥቦና ተገንዞ እንዳለቀ ፎቶ ሳነሳ የእናቴን አስክሬን ፎቶ ለምን አነሳሽ አጥፊ በማለት አስቸገሩኝ፡፡ እኔም አስፈቅጄ መሆኑን ከገለጽኩላቸው በኋላ ወንበሩ መጥተው ሲያናግሯቸው ቀዝቀዝ በማለት ተውኝ፡፡

ከሰሌኑና ከአቡጀዲው ፀሎት በሚካሄድበት ጊዜ የእምነቱ ቀሳውስት ሴት በመሆኔ በቦታው መገኘቴን በጥሩ ጎን አላዩትም፡፡ ይህም በጊዜው አስጭንቆኝ ነበር፡፡ ፡፡

በለቅሶው ስርዓት ላይ ከቀብር በኋላ የማታውን የሀዘንተኞችን ድባብ ሄጀ መመልከት አልቻልኩም፣ምክኒያቱምበወረዳው ፀሀይ ከገባ በኋላ ማንመ ሰው በሰዓቱ መነቀሳቀስ አይችልም ነበር፡፡

### 1.11.2 የተወሰዱ መፍትሄዎች

የተፈጠረው የእርስ በርስ ግጭት ተረጋግቶ ቦታው ላይ ሄጄ መረጃ እንድሰበስብ አድርጎኛል፡፡ ነፃነታችን ተገፎብናል ያሉትም ሁሉም ነገር ተስተካክሎ ተረጋግተው በነፃነት እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ በመጀመሪያው የለቅሶ ስርዓት በመንገዱ ርቀትና ገደል ሆኖ ብቀርም በሁለተኛው የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ላይ የፈለኩትን መረጃ በሙሉ ማግኘት ችያለ፡፡

# 2. ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ክፍል ውስጥ ሦስት ርዕሰ ጉዳዮች ትኩረት የተደረገባቸው ሲሆን የመጀመሪያው የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ሁለተኛው ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ሲሆን ሦስተኛው ጽንሰ ሀሳባዊ ዳራ ናቸው፡፡

## 2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በድህረ ምረቃ ፕሮግራም በክመንት ማህበረሰብ ላይ ሰባት ጥናቶች ተደርገዋል፡፡ በመጀመሪያ በክመንት ማህበረሰብ ላይ የተደረጉትን ጥናቶች እቃኛለሁ፡፡ ቀጥሎ በአማራ ክልል በተደረጉ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ላይ ሶስት የኤም.ኤ ጥናቶች እና አንድ የፒኤች.ዲ ጥናቶችን እቃኛለሁ፡፡

አብነት ሰለሞን (2005) “በቅማንት ማህበረሰብ የሚናገሯቸው ዝርው የቃል ተረኮች” በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት ዓላማ ከመግለጽ አንፃር ያላቸውን ፋይዳ መተንተን ነው፡፡ መረጃዎችን የሰበሰበው ከስድስት ቀበሌዎች ነው፡፡ ከትንተናው ባገኘው ውጤት ተረኮቹ በማህበረሰቡ ውስጥ የመገንባትና የመቅረፅ ተግባር አላቸው፡፡ የተሰበሰቡትን ተረኮች መነሻ በማድረግ የህብረተሰቡን ማንነት በሦስት ከፍሎ ማየት ችሏል፡፡ ማንነታቸውን ለመለየትም ሃይማኖታዊ ማንነት፣ በአላትና የጋብቻ ሁኔታ ናቸው፡፡

በተረኮቹ መነሻነትም በህገ ልቦና እምነት ዓለምን ሁሉ የፈጠረው “ምዝገና” ሲሆን እሱ በመብረቅ ከድንግል ሴት የወለደው “አደረንኪ” ደግሞ የሃይማኖታዊ ክንውኖቻቸው ሁሉ መሰረት እንደሆነ ገልጿል፡፡

ማህበረሰቡ ከአማራ ብሔር በተለየ ከሚያከብራቸው በዓላት ውስጥ “ምዝገና”፣ “ግብሩኽ” እና “ሽምኩላ” ወይም “ከረመዩኪኩና” “ዳኒቃ” ዘመን መለወጫና ደመራ ዋናዎቹ እንደሆኑ ተመልክቷል፡፡

በክመንት ማህበረሰብ የበላይ ሆኖ የሚመራው ወንበሩ እንደሆኑና ለአምልኮ ስርዓቱ የሚያቀርቡት ቄሶች መሆናቸውን ለይቶ አሳውቋል፡፡ የህገ ልቦና የጸሎት ቦታ ከብት የማይገባበት በደን ጥቅጥቅ ያለ ተራራማ ቦታ መሆኑን ገልጿል፡፡ አጥኚው ሁለቱን ወረዳዎችና ስድስቱ ቀበሌዎች ሲመርጥ መረጃውንም በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ውይይት ሰብስቧል፡፡

ማህሌት ሁነኛው /2005/ “ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በክማንት ማህበረሰብ” በሚል ርዕስ ያቀረበችው ጥናት ዓላማ በክመንት ማህበረሰብ ውስጥ የማህበረሰቡ አባል እርስ በእርስም ሆነ ከሌሎች ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት የሚፈጠሩ ግጭቶች ዓይነትና የሚፈቱበትን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱን ማሳየት ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ የተከሰተ ግጭት ተባብሶ የከፋ ጉዳት ከማድረሱ በፊት እንደ ግጭቱ አይነት ባህርይ እና ደረጃ ህግና ደንብ በማውጣት ሊያደርስ የሚችለውን ቀውስ የሚከለከሉበትን ዘዴ አሳይታለች፡፡

ለጥናቷ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት ሰብስባለች፡፡ በእነዚህ ዘዴዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች በጥናቷ ውስጥ በቅደም ተከተል ለመተንተን እንዲያስችላት ገላጭ የትንተና ስልትና የይዘት ትንተና ጥቅም ላይ አውላለች፡፡

የክመንት ማህበረሰብ ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀምባቸው የፍትህ ተቋማት የአካባቢ ሽንጎ አፈ-ሊቅ እና ወንበር መሆናቸውን አሳይታለች፡፡ እነዚህ የፍትህ አካላት ደግሞ ማንኛውንም ዓይነት ግጭት ለመፍታት “ሸወን” የተባለውን ስርዓት እንደሚጠቀሙና በአብዛኛው በማህበረሰቡ ውስጥ ግጭት የሚከሰትባቸው ምክንያቶች ከኢኮኖሚ፣ ከእሴት፣ ከሞራል እና ከሃይማኖት ጋር የተያያዙ መሆናቸውን በጥናቷ አመልክታለች፡፡ የግድያ ግጭት የሚፈታበትንና ካሳ የሚከፈልበትን መልክ ገልጻለች፡፡ ካሳ የሚከፈለው እንደ ግድያው ሁኔታ፣ እንደ ተጋጭዎቹ ማንነት የተለያየ ሲሆን አፈፃፀሙ ሀሬዝ፣ ድንገተ ሞትሊ ሂሽነንካ እና ዘመድሻ በተባሉ ደንቦች እንደሆነ አሳይታለች፡፡

የባልና ሚስት ጠብ በቅርባቸው ያለ ሰው ችግሩን ካልፈታ በሦስቱ የፍትህ ተቋማት እርቅ እንደሚፈፀም በማንኛውም የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ እርግማን፣ ምርቃትና ምሳሌያዊ ንግግሮች የእርቁ ስርዓት አንድ አካል መሆናቸው በጥናቱ ተመልክቷል፡፡ በጥናቱ ግኝትም እንደ ታየው ማህበረሰቡ ማንኛውም ዓይነት ግጭት መከሰት አይገባውም፤ ከተከሰተም በፍጥነት መፍትሄ ማግኘት አለበት የሚል አመለካከት አለው፡፡

በባህላዊው ስርዓትና በተቋሙ የበለጠ ለመጠቀምና ማህበራዊ ፋይዳቸውን እንደያዙ እንዲቆዩ ለማድረግ ለሀገር ሽማግሌዎች እውቅና መስጠት፣ በሞራልና በቁሳቁስ ማገዝ፤ ባህላዊውን ዕውቀት ለማስቀጠል ሁሉም የሚመለከተው አካል የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ በማለት የይሁንታ ሀሳብ አጥኚዋ ሰጥታለች፡፡

ከላይ የቃኘኋቸው ጥናቶች ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው ሁለታችንም በክመንት ማህበረሰብ ላይ መስራታችን ሲሆን ልዩነታችን በጥናት በመረጥናቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ነው፡፡

የዝናወርቁ (2007 ዓ.ም) "በሰሜን ጎንደር ዞን በጭልጋ ወረዳ በአይከል ከተማ በምትገኘው የ "እሜቴ አይከል" እምነትና ስርዓተ ከበራ ላይ ነው፡፡ ዋና ዓላማዋ የ "እሜቴ አይከል" ሀገረሰብአዊ እምነት የአምልኮ ስርዓቱን ለሚፈፅሙ የማህበረሰቡ ክፍሎች ያለውን ፋይዳ መግለጽ ነው፡፡ መረጃ የሰበሰበችው ከአውዱ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በተተኳሪ ቡድን ውይይት ነው፡፡

"የእሜቴ አይከል" እምነትና አምልኮ ክዋኔ ለእምነቱ ተከታዮች ማህበራዊ መቀራረብን የማዳበር ሚና እንዳለው የጥናቷ ግኝት ያሳያል፡፡ ለአማኞቹ ስነ ልቦናዊ ጥንካሬ የመስጠት ሚና ያላት መሆኑን በጥናቷ አመልክታለች፡፡

የእሜቴ አይከል እምነትና የአምልኮ ስርዓቱ የእስልምናና የክርስትና ሃይማኖት መሰረት ከሆነው የብሉይ ኪዳን ታሪኮች ጋር እንደሚገናኝ የሚያሳዩ መሆኑን ጠቁማለች፡፡ እምነቱና የአምልኮው ስርዓተ ከበራ በሚት ላይ የተገነባ መሆኑን አሳይታለች፡፡

## 2.1.1. በለቅሶ ስርዓት ላይ የተደረጉ ጥናቶች

ሞገስ ሚካኤል (2005 ዓ.ም) "በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረጉ የቀብር ስርዓቶች በስርዓቱ ላይ የሚካሄድ ቀረርቶ ፉከራና ክዋኔ" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት በለቅሶ ስርዓት ላይ የሚሰሙ ቀረርቶና ፉከራ ላይ ገላጭ ትንተናን ማድረግ ነው፡፡ በጀግና የቀብር ስነ ስርዓት ላይ የሚደረገውን በለቅሶ ስርዓቱ ላይ ሀይማኖታዊና ልማዳዊ ስነ ስርዓቶች በአንድነት የሚከወኑ መሆናቸውን አመላክቷል፡፡

የቀረርቶና የፉከራ ክዋኔን በተመለከተ በማህበረሰቡ ውስጥ በቀደሙት ትውልድ በቀብር ስነ ስርዓት አፈፃፀም ወቅት የሚፎከርላቸው አርበኞችና አዳኞች እንደነበሩና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ለጠንካራ በሬዎችም ጭምር መፎከር የተለመደ መሆኑን ገልጿል፡፡

በሪሁን መንግስቱ (2004) "በደብረ ታቦር ከተማ የወዮታና የፉከራ ግጥሞች ክዋኔና የይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት ሁለት አበይት ዓላማዎች አሉት፡፡ አንደኛው በደብረ ታቦር ከተማ የወየታና የፉከራ ግጥሞች ክዋኔ ምን እንደሚመስል ማሳየት ሲሆን፤ ሁለተኛው የግጥሞቹን ይዘት መተንተን ነው፡፡ ለጥናቱ መረጃ የሰበሰበው በተሳትፎ ምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ውይይት ነው፡፡

የሙሾ፣ የወየታና የፋከራ ግጥሞች የመከወኛ አጋጣሚያቸው አንድ ይሁን እንጂ የአከዋወን ሂደታቸውና በታዳሚው ላይ የሚፈጥሩት ስሜት የተለያየ መሆኑን በጥናቱ አመላክቷል፡፡ የወየታ ግጥሞች በእድሜ፣ በፆታ በማህበራዊ ደረጃ ልዩነት ላይ ተመስርተው የሚገጠሙ ሲሆን የፋከራ ግጥሞች ደግሞ ለጀግና ወንዶች የሚገጠሙ መሆናቸው ገልጿል፡፡ በቡድን የሚከወኑ በመሆናቸው ግለሰብ ተኮር አለመሆናቸውን ጠቁሟል፡፡

በሙሾ በወየታና በፋከራ ግጥሞች መካከል በአከዋወን ሂደት በከዋኞቹና በሚከወንላቸው ሰዎች ልዩነት መኖሩን በጥናቱ አሳይቷል፡፡ የግጥሞቹ አከዋወን ሂደት ይለያይ እንጂ አጠቃላይ ይዘታቸው የማህበረሰቡን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ገጽታ ማንፀባረቅና መጠበቅ መሆኑን በጥናቱ አመላክቷል፡፡

የበሪሁን እና የእኔ ጥናት በለቅሶ ስነ ስርዓት ላይ መሆናቸው ያመሳስለናል፡፡ የእኔ ጥናት ደግሞ ፋከራ፣ ቀረርቶ የሌላው መሆኑና ከፆታና በዕድሜ ልዩነት አለመኖሩም ያለያየናል፡፡

ማናዬ እንግዳወርቅ (2005) “በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ንጽጽራዊ ጥናት” በሚል ርዕስ ጥናት አድርጓል፡፡

የጥናቱ ዓላማ በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች እና ሙስሊሞች የለቅሶ ስርዓት ክዋኔን በንጽጽር ማሳየት ነው፡፡ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን የሰበሰበው በተፈጥሯዊ አውድ ላይ በመገኘት በተሳትፏዊ ምልከታ እንዲሁም ሃያ ሁለት ሰዎችን ቃለ መጠይቅ በማድረግ ነው፡፡ በትንታኔው በሁለቱም የሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ የሚደረገውን የቅድመ ሞት ክዋኔ የጊዜ ሞት ክዋኔ እንዲሁም የድህረ ሞት ክዋኔ በዝርዝር አሳይቷል፡፡ በተጨማሪም በስርዓቶች ላይ የታዩ አንድነቶችና ልዩነቶችን አመልክቷል፡፡ ሌላው የሃይማኖቱ ተከታዮች የለቅሶ ስነ ስርዓት ላይ የሚታዩ ልዩነቶች ከቅድመ ሞት እስከ ድህረ ሞት ድረስ ባሉት ክዋኔዎች ላይ መሆናቸውን ገልጿል፡፡

የለማ ንጋቱ (2006) ፒ.ኤች.ዲ “በደቡብ ጎንደር ዞን የለቅሶ ስርዓት ክወና” የሚል ሲሆን የዚህ ጥናት ዋና ዓላማው በደቡብ ጎንደር ዞን የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ማህበረሰብ ሞት ሲከሰት በቡድን የሚያከብሯቸውን የለቅሶ ስርዓቶችና ቃል ግጥሞች ክወና መግለፅ ነው፡፡ መረጃውን በኢትኖግራፊያዊ የጥናት ዘዴ ከተጠኚዎቹ ጋር አብሮ በመኖር ሞት ሲከሰት የሚያከናውኗቸውን ስርዓቶችና የለቅሶ ቃል ግጥሞች በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ፣ በቡድን

ውይይትና በሰነድ ምርመራ ሰብስቧል፡፡ ቪዲዮና ፎቶ ካሜራዎች፣ መቅረፀ ድምፅ፣ የጽሑፍ ማስረጃዎችን በመሰብሰብ አገልግሎት ላይ አውሏል፡፡

የለቅሶ ስርዓቱ ከእስራኤላውያን የለቅሶ ስርዓት ጋር የሚመሳሰልባቸው ነገሮች መኖራቸውን አሳይቷል፡፡ በሙሾ ክወና ሴቶች ከጣሊያን ወረራ በኋላ በፎካሪዎች ተገፍተው መውጣቸውንና በአሁኑ ሰዓት በከዋኝነትም ሆነ በታዳሚነት የሚሳተፉ መሆናቸውን አሳውቋል፡፡ የለቅሶ ስርዓቱና ቃል ግጥሞቹ ክወና የማህበረሰቡን አንድነት ማጠናከር ሀዘኑን ይፋ በማውጣት የማቅለልና ታሪኩን የማስተላለፍ ሚና የሚጫወቱ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ የእኔ ጥናት ከለማ ጥናት ጋር በርዕሱ ቢመሳሰልም በጥናቱ ስፋትና በአካባቢም ይለያያል፡፡

## 2.2 ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝት

### 2.2.1 ስርዓት (Ritual)

በሀገራችን ብዙው ማህበረሰብ ያለውን ስሜት መግለጽ የሚችለው በአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ የሚደረግ የስርዓት ዝግጅት ነው፡፡ በሌላ መልኩ ሀዘን ለመግለጽና ውስጣዊ ስሜትን በለቅሶ ለማውጣት በማህበረሰቡ ውስጥ የተለያዩ ዝግጅቶች ይደረጋሉ፡፡ ግማሹ ሲወድቅ ሲነሳ፣ ፊቱን ሲቧጥጥ፣ፀጉሩን ሲነቅል፣ያዙኝ ልቀቁኝ ሲሉ ይታያሉ፡፡

የሟች ቤተሰብም የሚለበስ አልባሳት፣ የሚያዝ ቁሳቁስ ይዘው ከታዳሚው ፊት ለፊት ተጠባብቀው በእርጋታ ያለቅሳሉ፣ ያነባሉ፣ ያዝናሉ፡፡ ዘመድ በየአቅጣጫው ስለሚመጣ አገናኝ ከሆነ መንገድ ላይ በማውጣት፣ ሴቶቹ ጥቁር ካባ በመልበስ እና ባህላዊ የሆነ የተጠለፈ ቀሚስ በጀርባ አዙረው ለብሰው ሀዘናቸውን እየገለጹ ለስለስ ካለ የድምጽ አወጣጥ ከለቅሶው ቦታ ይቀላቀላሉ፡፡ በመሆኑም ከዋኙ ከታዳሚው ጋር ያለው መስተጋብር ተግባቦታዊ ጉዳይ የሚታይ ነው፡፡ ታዳሚውም ክዋኔውን በማድመቅ በአካላዊ እንቅስቃሴ እና በፊት ገጽታ የተለያዩ ሙሾ በመደርደር ማልቀስ፣ ማስለቀስ፣ መጮህ፣ ማንባት፣ የእንባ መመንጨት፣ ማውረድ፣ ማፍሰስ ወይም ለመግለጽ ይሞክራሉ፡፡ ሙሾ የምትደረድረው የድምጿ ቃና የማይስብ ከሆነ የታዳሚው እንባ መድረቅ ይታያል፡፡

> *From the point of view of the audience, the act of expression on the part of the performer is thus marked as subject to evaluation for the way it is done, for the relative skill and effectiveness of the performers display of competence" (Bauman, 1975:293)*

ሰለሞን ተሾመ ስርዓተ ከበራን(Ritual)ን እንዲህ በማለት ገልጸውታል፣ አንድ ማህበረሰብ ያለውን ሃይማኖትና ባህል መነሻ በማድረግ የተወሰኑ ክወናዎችን ወይም ስነ ስርዓቶችን ካላቸው ማህበራዊ እና ሃይማኖታዊ ዋጋ አንጻር በመለየት በከፍተኛ ቅደም ተከተላዊ ስርዓት እና በተደጋጋሚ የሚከወነው ማህበረ-ሃይማኖታዊ ድርጊት ነው፡፡ ማህበረ-ሃይማኖታዊ ድርጊቱም በማህበረሰቡ ህይወት ውስጥ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ነው (2007፡159)፡፡ ስርዓተ ከበራዎች በማህበረሰቡ የእምነት ስርዓቶች ወይም የሃይማኖት አስተምህሮ ውስጥ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውንና ጎልተው የሚወጡት ሀሳቦችን፣ ህጎችን፣ ስርዓቶችንና አስተሳሰቦችን፣ ተመልካቾችን በቀላሉ ለመመልከትና ለመረዳት በሚችሏቸው ድርጊቶች አማካኝነት የሚቀርቡ ናቸው፡፡

እነ Sims ስርዓተ ከበራን ሲገልጹ ለምሳሌ በለቅሶ ስርዓት ላይ የቃል ግጥም ሲደረደር በሚስብና በሚማርክ ዜማ የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመያዝ የሚፎክሩና የሚያቅራሩ፣ የሚሸልሉ እንዲሁም ደረታቸውን የሚደልቁ፣ ፊታቸውን የሚቧጥጡ፣ ፀጉራቸውን የሚነጩ፣ ያዙኝ ልቀቁኝ እያሉ የሚወድቁ የሚነሱ በመሆናቸው የታዳሚውን መመልከት ሁል ጊዜም በተከታታይ የሚደረግ ክንውን ነው፡፡

> *Most ritual bring together many types of Folklore, verbal, such as chants, recitations, poems or songs, customary, such as gestures, dance or movements and materials, such as food, book, awards, clothing and costumes" (2005:95)::*

ይህም በአንድ የለቅሶ ስነ ስርዓት ላይ የሚደረደሩ ስነ ቃሎች፣ ባህላዊ ቁሱን የትወና ጥበቡን እንዲሁም የሚደረጉ ሀገረሰባዊ ልማዱን ትኩረት ሰጥቶ መመልከት የሚቻል ነው፡፡

### 2.2.2 ሞት ምንድን ነው?

ሞት ከሰው ህይወት ጋር ተያይዞ የሚኖር ሲሆን ፈጣሪ ፈቅዶ ወደዚህ ዓለም ያመጣው ነው፡፡ የሰው ልጅ ሞት ይሞታል፡፡ ላለመሞት የፈለገውን ያህል ጥረት ቢያደርግም በፈጣሪ የተቆረጠችውን ቀን ማለፍ አይችልም ብሎ ይታመናል፡፡ አንዳንዶች የሚቹን ጦስ የሚወስድለት ሌላ ነገር በማጣቱ ምክንያት ሞተ ብለውም ያምናሉ፡፡ ለምሳሌ በቤት ውስጥ በሬ ወይም ላም ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ቢሞት "ለባለቤቱ የመጣው ሞት/ጦስ/ ለእንስሳው ሆነ" ይባላል፡፡ ሞት እንደየአካባቢው ሁኔታ ይለያያል እንጂ ሞት ለማንኛው ሰው የማይቀር ዕዳ ነው፡፡ ይህ የማይቀር ዕዋ ሲከሰት ግን የተለያዩ የሀዘን ስርዓቶች ይከናወናሉ፡፡

ሞት ከህያውነት ወደ በድንነት መለወጥ ነው፡፡ ሞት በሚች ውስጥ ምድራዊ ዓለም በቃኝ ብሎ መለኮታዊ ወደሆነው ሌላ ዓለም መቀላቀል ነው፡፡ ሞት ከተኖረበት፣ በአእምሮም፣ በህሊናም፣ በአካልም ከሚሰማው፣ ከሚታየው ተነጥሎ መሄድ ነው፡፡

Hertz ሞት ለሰው ልጅ የተለመደ ክስተት እና ውስጣዊ ስሜቶችን በከፍተኛ ሁኔታ መቀስቀስ የሚችል መሆኑን ስለምናምን እኛ ሁላችንም የምንረዳበት መንገድ ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡

> "*We all belive we know that death is because it is familiar event and one that arouses intense emotion /1960:27/.*

የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች እንደገለጹልኝ ሰው ከአራቱ ባህሪያት የተፈጠረ ነው፡፡ አራቱ የሥጋ ባህርያት ንፋስ፣ እሳት፣ መሬትና ውሃ ሲሆኑ እነዚህም የስጋ ባህሪያት ይባላሉ፡፡ የነብስ ባህሪያት ደግሞ ህያዊት፣ ነባዊት፣ ነባቢት ተብለው በሦስት ይመደባሉ፡፡ እነዚህ ሰባቱ የማይሞት፣ የማይታመም፣ የማይናገር ተብለው ከመኖር ወደ አለመኖር ይሸጋገራሉ፡፡ በባህሉ መሰረት ሞት ሀዘንን ያስከትላል፡፡ በጣም ማዘን ደግሞ አስከፊ የሆነውን ለቅሶን ያመጣል (ቃለ መጠይቅ፣ ቄስ በላይነህ መንግስቱ 15/06/2011)፡፡

አንድ ሰው ሞቷል ተብሎ የሚታወቀው የልብ ትርታው/ምቱ ሲቆምና እስትንፋሱ ሲያቋርጥ ነው፡፡ በክመንት ማህበረሰብ ሞት ምንም አይደለም፡፡ በሕይወት እያሉ መረዳዳት፣ መተጋገዝ እንጂ ከሞቱ በኋላ እግዚአብሔርን ማስቀየም ይሆናል በማለት ያምናሉ፡፡ ሰው ከሞተ ሀዘኑን ቀለል አድርገው የማየት ባህል አላቸው፡፡

በክመንት ማህበረሰብ ሞትና ደስታ ጆሮ በጆሮ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ብር ከኪስ ተቀምጦ እንደማይኖር ሁሉ ሞትንም በዚህ መልኩ ይስሉታል፡፡ ለዚህም ነው ሞትን ቀለል አድርገው የሚያዩት (ቃለ መጠይቅ፣ ቄስ ጌጡ አያሌው 10/06/2011)፡፡

### 2.2.3 የለቅሶ ስርዓት ምንድነው

ለቅሶ ሰው የሞተበት ሀዘኑን የሚገልጽበት ስሜታዊ ምላሽ ነው፡፡ በውስጡ ያለውን የመከፋት፣ የማዘን፣ ስሜት ለገሀዱ ዓለም ማሳያ መንገድ ነው፡፡ ለቅሶ በየአካባቢው ይለያያል፡፡ ለህጻን፣ ለወንድ፣ ለሴት፣ ለትልቅ፣ ለትንሽ ተብሎ ሊለያይ ይችላል፡፡

በተጠኚው ማህበረሰብ የለቅሶ መገለጫው ደግሞ ቁሳቁስ በመያዝ የተለያዩ ሙሾዎችን በመደርደር ሟች ለማህበረሰቡ ሩህሩህ፣ ቸር፣ ደግ፣ የዋህ፣ የሚያበላ፣ የሚያጠጣ መሆኑን በቁሳቁስና በሙሾ ድርደራ ያለባቸውን ሀዘን በማልቀስ፣ እንባ በማፍሰስ፣ እጅን በትከሻ

በመንካት የለቅሶው ምንነት ያሳያሉ፡፡ በማህበረሰቡ አንድ ሰው ሲሞት የሞተው አካል ነፍሱ ከስጋው ሲለያይ ነብሱ ሲያልፍ፣ አስክሬኑ ከኖረበት ቤት ሲወጣ፣ ግብዓተ መሬት ሲወርድ (ሲቀበር) መሪር የሆነ የሀዘን እንጉርጉሮ ይሰማል፤ ይታያል፡፡ በማህበረሰቡ የሀዘን መገለጫው ነጭ ልብስ ነው፡፡ ፉከራ፣ ቀረርቶ፣ ሽለላ፣ ፀጉር መላጨት፣ ፊት መንጨት፣ ደረት መምታት አይደረገም፡፡

## 2.2.4 የሙሾ ስርዓት ምንነት

ደስታ ተክለወልድ ሙሾን እንደገለጹት "ለቅሶ፣ ቅንቀና፣ ኾመራ፣ ግጥም፣ ዜማ፣ ቁዘማ፣ እንጉርጉሮ፣ ረገዳ፣ ጭብጨባ ያለበት "ሰቆቃው" ነው (1962፡1016) ብለውታል፡፡ ሙሾ የሟች ቤተሰቦች የበለጠ እንዲያለቅሱ ሀዘናቸውን እንዲገልጹ ለማድረግ ማህበረሰቡ የፈጠረው የለቅሶ ስርዓት ነው፡፡ በሙሾ ያለፈ ታሪክ፣ ጀግንነትን፣ የአያት ቅድመ አያቶች ጉብዝና፣ ታታሪነት እየተነሳ ይደረሰራል፡፡ ሙሾ ደርዳሪው በለቀስተኛው ፊት እያዜመ ሀዘኑን የበለጠ ለማድመቅ የሚያድገው ስነ ቃላዊ ገለጻ ነው፡፡

ሙሾ ብዙውን ጊዜ ለሟች ቤተሰቦች ሀዘናቸው መሪር በመሆኑ ምክንያት የድካም ስሜት እንዳይኖር ለትንፋሻቸው ረፍት ማድረጊያ ነው፡፡ ሙሾ ሀዘንተኞች በለቅሶ ሰዓት የመጣውን ታዳሚ አስተውለው ለማየትና ለሟች ምን ያህል የሀዘን ስሜት እንደተሰማው ለመለየት የሚያስችል የለቅሶ ስርዓት ነው፡፡

በክመንት ማህበረሰብ የሙሾ ስርዓት በመጠኑ የሚባል ነው፡፡ ይህም አስክሬኑ ከቤት እስከሚወጣ እና መንገድ ላይ ሲያርፍ እንዲሁም ከድግናው ቦታ (ከመቀበሪያ ቦታው) ሀዘንተኞችን ለማረጋጋት ሲባል የሚመጡት ለቀስተኞች የሟችን ደግነት፣ ቸርነት የሚገልጹ ሙሾዎችን ይደረድራሉ፡፡ ሁሉም ተመልካች ብቻ ሳይሆን እንባ እያወረደ፣ እየቆዘመ፣ እያረገደ፣ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ በቅብብሎሽ ሀዘኑን ይገልጻሉ፡፡

## 2.3 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

ይህ ጥናት ከፎክሎር ዘውጎች መካከል በሀገረሰባዊ ልማድ ስር በሚጠቃለለው "በለቅሶ ስርዓት" ላይ ያተኮረ ነው። በዚህ ጥናት ውስጥ የምከተለው ክዋኔ (performance) ንድፈ ሀሳብ እና ስርዓት (Ritual) ንድፈ ሀሳብን ነው።

ክዋኔ አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከወን የሚተገበር ኪናዊ ጉዳዮችን ሁሉ አጠቃሎ የሚይዝ ነው። እንዲሁም ሰዎች በተግባቦት ሂደታቸው ውስጥ ማህበራዊ ባህላዊ ጉዳዮቻቸውን የሚገልፁበት መንገድ ነው። ክዋኔ በራሱ የማህበረሰቡን የእርስ በርስ ትስስር የሚፈጥር ነው።

> *Performance is a made of communicative behavior and type of communicative event. Write the term may be employed in an acsthetically neutral sense to designate the actual conduct of communication /as apposed to the potential for communicative action/. Performance usually suggests an aesthetically marked and heightened mode of communication, framed in a special way and put display for an audience. The analysis of performance, the very conduct of performance-highligthts the special, cultural, and aesthetic dimentions of the communicative process /Bauman, 1992:3/.*

በክዋኔ መሰረታዊ ጉዳዮች የሚባሉት በዋናነት ከዋኝ፣ ታዳሚ እና አውድ ናቸው። ክዋኔ ማለት ጥበባዊ ድርጊት ሆኖ የክዋኔውን ድባብ ከዋኞቹንና በውስጡ ያለውን እምቅ ጥበቡን ታዳሚውን እና መቼቱን የያዘ መሆኑን ወይም ክዋኔ በውስጡ በርካታ ነገሮችን የያዘ ነው። አንድ ክዋኔ የታለመለትን ግብ ይመታ ዘንድ የከዋኙን የአከዋወን ብቃትና የመድረክ አያያዝ ችሎታው ያሳያል።

**ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ፡-** በዋናነት በመስክ ጥናትና ምርምር ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ስለ ተጠኚው ማህበረሰብ ወይም ቡድን ዝርዝር መረጃ ከነባራዊ ሁኔታዎች መሰብሰብን ይጠይቃል።

Bauman እንዲህ በማለት ገልጸውታል። የአንድ ድርጊት ክዋኔ ከዋኙ ለተመልካች ኃላፊነት ወስዶ መልእክት የሚያስተላልፍበት መድረክ ነው። ተመልካችም ከቀረበለት ሀሳብ በመነሳት የቀረበው ርዕስ እና የአቅራቢ ችሎታ እውቀት በመገምገም ምላሽ የሚሰጡበት መድረክ ነው።

*Performance involves on the part of the performer an assumption of accountability to an audience for the way in which communication is carried out, above and beyond its referential content. From the point of view of the audience, the act of expression on the part of the performer is thus marked as subject to evaluation for the way it is done, for the relative skill and effectiveness of the performer's display of competence (Bauman: 1975:293).*

አውድ አንድ ፎክሎራዊ ተግባር ሲከወንበት በቅርብ ተዘጋጅቶ ያለ ተራክቢዊ አንዳች ክንውን በቅርበት የሚካሄድበት ሰፊ አካባቢያዊ አውድ ነው፡፡ ተግባቦታዊ ሂደቱ የሚተላለፍበት ጊዜና ቦታ አውድ ነው ማለት ይቻላል፡፡ አውድ ለአንድ ክዋኔ ቅርጽና መዋቅር እንዲሁም የሚተላለፈው መልእክት መሰረት ነው፡፡ በመሆኑም አውድ ቃል ግጥም በሚከወንበት ጊዜ የሚፈጠረውን አጠቃላይ የከዋኙ ማንነት፣ የታዳሚው ፈጠራና ተሳትፎ የሚከወነው ነገር ጊዜና ቦታ ቁሳቁሶች በቅንጅት ተደራጅተው ገላጭና ጥበባዊ በሆነ መንገድ የሚቀርብበት የእርስ በርስ ግንኙነትና ተደራጅተው ገላጭና ጥበባዊ በሆነ መንገድ የሚቀርብበት የእርስ በርስ ግንኙነትና መስተጋብር የሚፈጠርበት ተፈጥሯዊ መቼትና ማህበራዊ አውድ ነው (Dundes 1980)፡፡

Bauman (1986፡363) አውድን ባህላዊ አውድ እና ማህበራዊ አውድ በማለት ከፍሏቸዋል፡፡

**ባህላዊ አውድ፡-** በውስጡ ልማዳዊ ተግባራትን እና የሰዎቹን አኗኗር፣ ባህል፣ ወግ፣ ልማድ፣ እምነት በፎክሎር ውስጥ የተቀረፀበትን መንገድ የሚያሳይ ነው፡፡ በተጨማሪም እንደ ዝምድና፣ ጉርብትና ከበራ ወዘተ ያሉ ተቋማትን እንዲሁም የመስተጋብር መንገዳቸውን ያመለክታል፡፡ ማህበረሰቡ የመፈቃቀርን የመተሳሰብን እንዲሁም ለእያንዳንዱ የፎክሎር አይነት በየባህሉ የሚሰጠውን ትርጉም እና ትዕምርታዊ ግንኙነቶችን ይገልጻል፡፡

ባህላዊ አውድ የአንድ ማህበረሰብ መገለጫ እንዲሁም የህልውና መሰረት የሆነ ማህበረሰቡ ራሱ የሚፈጥረው የሚተገብረው፣ የሚከውነው፣ የሚያከብረውና የሚገዛለት ነው፡፡

በአጠቃላይ ባህላዊ አውድ የፈጠራና የአዳዲስ ግኝቶች ምንጭና የሀገር በቀል ዕውቀቶች ትብብር የመሰረት ድንጋይ የዕውቀት መገለጫና ማስተላለፊያ መንገድ በመሆን የነገን ተግዳሮቶች ለመቋቋምና የማህበረሰቡን ልማድ ለማጥበቅ የሚያስችል ነው፡፡

**ማህበራዊ አውድ፦** የፎክሎር ማህበራዊ ጉዳዮች የሚገኝበት ቡድን ፎክሎሩ የሚያንጸባርቃቸውን ጠቃሚ ሁኔታዎች ላይ ያተኩራል፡፡ ባህላዊ ሁኔታዎችን የሚያሳዩ በተለያዩ ግለሰቦች መካከል የጋራ የሆነ የራሳችን ነው የሚሉ የሚያስተሳስሯቸው ነገሮች ሲሆኑ የቋንቋ የእውቀት፣ የእሴትና የእምነት ስርዓት የአስተሳሰብ ደረጃ የአመጋገብና የአለባበስ የአንድ አይነት የታሪክ ባለቤትነት የሚገለፅባቸው ናቸው

# 3. የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ

የክመንት ማህበረሰብ በአማራ ብሔራዊ ክልል መንግስት በሰሜን ጎንደር ዞን ጭልጋ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡

ጭልጋ ወረዳ ከአዲስ አበባ በስተ ምዕራብ 752 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን ከአማራ ክልል ዋና ከተማ ከባህርዳር 553 ኪ.ሜ እንዲሁም ከባህር ዳር ጎንደር 149 ኪ.ሜ ከጎንደር 50 ኪ.ሜ ርቆ ይገኛል፡፡

ጭልጋ ወረዳ ላይ አርማጭሆ፣ ምስራቅ ደምቢያ፣ ምዕራብ ደምቢያ እና አለፋ ጣቁሳ ያዋስኑታል፡፡ ይህን የሚገልጽ ካርታ አላገኘሁም፡፡ ምክንያቱም ወረዳው ቁጥር አንድ እና ቁጥር ሁለት ተብሎ ስለተከፈለ ለወደፊቱ በዕቅድ ላይ ነው፡፡ ነገር ግን ባይጠቀሙብትም የድሮው ካርታ እንዳለ ገልፀውልኛል (ቃለ መጠይቅ ኪዳነማርያም አበራ 06/06/2011)፡፡

ወረዳውም በ2008 ዓ.ም ቁጥር አንድ እና ቁጥር ሁለት ተብሎ ተከፍሏል፡፡ ቁጥር አንድ የክመንት ማህበረሰብ ሲሆን እሱም አንድ የከተማ አስተዳደር፣ አንድ የገጠር ከተማ እና ሃያ ሶስት የገጠር ቀበሌዎች አሉት፡፡

የከተማ አስተዳደሩ አይከል ከተማ ሲሆን፤ የገጠር ከተማው ደግሞ ጮንጮቅ ከተማ ነው፡፡ የገጠር ቀበሌዎች ደፉድ፣ ገመናውራ፣ ጀልሰም፣ ድኩላ፣ ላጌ፣ ምርት አምባ፣ አዲስ ዘመን፣ ምድረ ባራ፣ ኩሻይና እንግዳጌ፣ ከንተብ ባሰከኒት፣ ከንተብ ዳንጉራ፣ ኳበር ሎሚዬ፣ ሞላሊት፣ ዋሊዶገ፣ ተምበራ፣ እያሆ፣ ሰራባ፣ ስርጢያ፣ ሹምጌ፣ ማርሆና፣ ሰራግና፣ ናራ አውራርዳ፣ ሽብድባ እና ባስድባብ ተብለው ተለይተዋል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ኪዳነማርያም አበራ 06/06/2011)፡፡ ቁጥር ሁለት የአማራው ማህበረሰብ ሲሆን ጥናቴን ያደረኩት ግን በቁጥር አንድ በህገ ልቦና እምነት ላይ ብቻ የተመሰረተ በመሆኑ ትኩረት አልተደረገበትም፡፡

## 31. የክመንት ማህበረሰብ ስያሜና አመጣጥ

የክመንቶች የዘር ምንጭ የኖኅ ልጅ "ካም" እንደሆነና "ካም" ደግሞ ኩሽን፣ ምዝራይብን እና ከነዓንን ወለደ፡፡ ይህም የካም ዘሮች የተሰጣቸው መጠሪያም "ክመንት" እንደሆነ (የቡድን ተወያዮች በ10/06/2011) ያስረዳሉ፡፡

*የክመንት ማህበረሰብ ከኖኅ ዘመን አንስቶ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደኖረ የሚያትት ነው። በመሆኑም ኖኅ ከጥፋት የዳነበት መርከብ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኘው አራራት ተራራ ላይ ካሳረፋት በኋላ ሁለቱ ልጆቹ ሴምና ያፌት ወደ መካከለኛው ምስራቅ እንደሄዱ /አለቃ ታዬ 1993፤3) ያስረዳሉ።*

የክመንቶች አባት ካም ኑሮውን ከአባቱ ከኖኅ ጋር ኢትዮጵያ ውስጥ መስርቶ መሆኑን የሚገልፅ ነው። ለዚህ የሚጠቀሱት መካከል የኖኅ ሚስት የ "እሜቴ አይከል" መቃብር መገኛ ጭልጋ ወረዳ አይከል ከተማ ውስጥ እስከ አሁን ድረስ ተጠብቆ የህገ ልቦና ሃይማኖት የአምልኮት ስርዓት አሁንም ድረስ ዘልቆ በክመንት ህዝብ ውስጥ ይታያል።

ቀዳሚዎቹ የሰሜንና የመካከለኛው ኢትዮጵያ ሰፋሪ የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪ የአገው ህዝብ አካል የሆነው የክመንት ማህበረሰብ ነው ይላሉ (Gamst 1969:1)::

ሌላው ስያሜ Bruce J. "ክመንት" ብሎ ሲጠራው Blanc. H" ክመውንት የሚል ስያሜ ሰጥተውታል። "ካም" እና "እንት" የሚሉት ሁለት ቃሎችም የሰጡት ትርጉም "አንተ-ካም" ይህ ማለት ነው። ይህም ክመንት "የካም ልጅ" ከሆነው ከኩሽ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ህዝብ መሆኑን /Bruce J. 1868፡4 እና Blanc. H (1869፡291-298) ገልጸዋል።

ለክመንት ማህበረሰብ የተለያዩ እይታዎች ተሰጥተዋል። በመሆኑም ምን አመለካከትና ተአማኒነት መኖርና አለመኖር የሚለውን አፈ ታሪክም ለመግለጽ እሞክራለሁ።

የመጀመሪያው እይታ ክመንት የአብርሐም ህግ ተከታይ ናቸው። መነሻ ሀገራቸውም እየሩሳሌም ነው የሚል አተያይ አለ። በወቅቱ በነበረው ረሃብና ችግር ግብፅን አቋርጠው ቁጥራቸው ሰባት የሚሆነው በአባታቸው አይነር እና እንተላ መሪነት የዛፍ ፍሬን ምግብ አድርገው በኤርትራ በኩል ገብተው ወገራ ወረዳ ከርከር ከተባለው ተራራማና ደናማ ቦታ ሰፈሩ። በጊዜውም ካለጫካና የዱር እንስሳ በስተቀር ቀደም የነበረ ምንም አይነት ሰው /ህዝብ/ አልነበረም። ለዚህም ነው "ክመንት ቀደም ብሎ የኖረነው" የሚል ትርጉም የተሰጠው።

ዘመኑ በትክክል ባይታወቅም ክርስትናና ቤተ እስራኤል ወይም ሻንቅላ፣ ጉምዝ፣ ኩንፈል... የተባሉት ወደ ኢትዮጵያ ከመግባታቸው በፊት ክመንት የክመንት ማህበረሰብ እንደነበረ ይናገራሉ። (ቃለ መጠይቅ፣ ወንበር አማረ ሙሉነህ 18/06/2011)

የክመንት ማህበረሰብም ቀድመው ወደ ኢትዮጵያ ተሰደው ከመጡት ጥንታዊ ህዝቦች መካከል አንዱ ነው። ክመንቶችም ቁጥራቸው ሶስቱ ወደ ላስታ ወደተባለው የአገው ክልል ሄዱ። ሁለቱ

ደግሞ ጎጃም ውስጥ ወደሚገኘው አገው ምድር፣ ሁለቱ ደግሞ አሁን ከርከር እየተባለ ወደሚጠራው ወደ ጎንደር ምድር ሄዱ፡፡ እንደ አለቃ ታዬ አገላለጽ የክመንት ህዝብ ከጎንደር ስርወ መንግስት መመስረት አንስቶ በከርከር፣ በጋባ ጋላገር፣ በጭልጋ፣ በቦባ፣ ኮሰጌ፣ ጃኒፈንቅራና አካባቢያቸው ሰፍሮ ይገኝ ነበር፡፡ በአሁኑ ሰዓት እነዚህ ቦታዎች በአማራ ብሔራዊ ክልል በላይ አርማጭሆ፣ ጭልጋ፣ ወገራ፣ ጎንደር ዙሪያ ወረዳ አስተዳደሮች እንዲሁም በጎንደር ከተማ አስተዳደር ስር ይገኛሉ፡፡ (አለቃ ታዬ 1992)፡፡

> *አይነር እና እንተላ በስደት ሰዓት በጫካ ሲኖሩ አንዷት የዱር እንስሳ "ሰሳ" የምትባል ልጇን ጫካ ውስጥ ጥላት ሄዳ ስትቀር እንተላ የሰሳዋን ልጅ ሆዷ አልጨክን ብሏት አጥብታ አሳደገቻት፡፡ እንተላም ከእንግዲህ በኋላ የክመንት ልጅ የሆናችሁ "ሰሳ"ን የበላችሁ ከሆነ ሩም እርጉማን ሁኑ ብላ ተናግራለች፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ወንበር አማረ ሙሉነህ 17/06/2011/፡፡*

የክመንት ማህበረሰብ "ከእንጨት" እንደተገኙ እና የዘር ሀረጋቸውም እንጨት እንደሆነ በክመንት ማህበረሰብ አፈ-ታሪክ፡-

> *"አይነርና እንተላ" ተሰደው በከርከር በረሃ ሲኖሩ "ዲዛ" ከሚባል ትልቅ እንጨት በቁሙ ፈልፍለው ለአርባ ዓመት ቤት አርገው ሲኖሩ ምግባቸውንም የሚበሉት የእንጨት ፍሬ ነው፡፡ በመሆኑም ከዕለታት አንድ ቀን የእንጨት ፍሬ ለመልቀም ሁለቱ ከእንጨቱ ፍልፍል ውስጥ ብቅ ሲሉ፤ አንድ ሰው አያቸው እና እናንተ እነማን ናችሁ ሲላቸው "አይነርጋላ" እኛ እንደናንተ ሰዎች ነን አሉ" (ወንበር አማረ ሙሉነህ 17/06/2011)፡፡*

ሁለተኛው አመለካከት ስለ ክመንት ህዝብ ጥንት አመጣጥ የሚነገረው ከከነዓን ምድር የመጣ ሲሆን የክመንቶች አባት "አይነርና እንተላን" ይዞ ከከነዓን ምድር ከክርስቶስ ልደት በፊት ወደ ኢትዮጵያ እንደመጠና ሰው ሳያየው በከርከር ዱር በረሃ ፍራፍሬ እየለቀመና እያደነ መኖር እንደጀመረ /አለቃ ታዬ 1920፡9-11) ይገልጻሉ፡፡

የክመንቶች አባት አይነርና  እንተላ በኢትዮጵያ ምድር እንደገቡና እንደኖሩ ይነገራል፡፡ በመሆኑም የክመንት ማህበረሰብ በሰሜን ኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሰፋሪ ነው፡፡

*"the kemant people inhabit mainly Chilga and the surrounding area. The well-known places where one can get people who speak the language are. Seraba, Teber, Tembera, Chanchok and to same extent Ayele town (Zelalem Leyew 2002:10).*

ሦስተኛው አመለካከት ሰማልኝ ክንዴ አለቃ ወልደማርያምን ገልጸው እንደፃፉት ከሆነ ብሎ ያስቀመጠው የክመንት ህዝብ ከመካከለኛው ምስራቅ ኢትዮጵያ ወደ ኢትዮጵያ ፈልሶ በረሃብ ምክንያት ከማካከለኛው ምስራቅ ተነስተው "በባብ ኤልመንደብ" በኩል ወደ ኢትዮጵያ ተሻግረው የገቡ ናቸው፡፡

አራተኛው አተያይ በስደት ላይ የተመሰረተውን የክመንት ታሪክ እይታ የሚደግፈው ሌላው መረጃ ክመንት ንጉሰ ምኒሊክ አንደኛ ከእስራኤል ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ንጉሱን በሰራተኝነት እያገለገለ አብሮ የመጣ በብሉይ ኪዳን እንደጻፈው በኃጢያት ምክንያት ክመንት የእስራኤላውያን አገልጋይ እንዲሁም ከፈረዱበት "ከዳን ነገድ" የመጣ ነው (ቃለ መጠይቅ፣ *ወንበር አማረ ሙሉነህ 12/06/2011)፡፡*

አምስተኛው አተያይ ደግሞ ክመንት ከግብጽ ሀገር በመነሳት የጥቁር አባይን ፈለግ ተከትሎ ወደ ኢትዮጵያ የተሰደደና በጣና ሐይቅ ዙሪያ ሰፍሮ የኖረ ህዝብ እንደሆነ ይናገራሉ

ስድስተኛው አመለካከት የክመንት ማህበረሰብ ከጥንት ጀምሮ ስር መሰረቱና ነዋሪነቱ ከኢትዮጵያ ምድር የኖረ እንጂ ከየትም አልመጣም የሚል ነው፡፡ (ሰማልኝ ክንዴ፣ 2010፡1)

## 3.2 የክመንት ማህበረሰብ ቋንቋ

የክመንት ማህበረሰብ የሚናገረው ቋንቋ ክመንቲሳ ሲሆን ከማአከላዊ ኩሻዊ ወይም ከአገው ቋንቋ ቤተሰብ የሚመደብ ነው፡፡

*the kemant people speak adialect of "Agew" a Cushitic language. According to him, all of "Agew" speak mutually intelligible dialects of an "Agew language" and as far as their use of other language is concerned he says almost all "Agew" are bilingual in Amharic" (Zelalem Leyew, 2002:10).*

ከአገው ቋንቋዎች መካከል የክመንቲሳ ቋንቋ ለክመንት ማህበረሰብ የሚግባቡበት ነበር፡፡ Zelalem (2003) Hetzro (1969)ን ጠቅሰው እንደገለጹት የአገው ቋንቋ በሰሜን ምስራቅና

በሰሜን ምዕራብ በኢትዮጵያ ክፍል በአብዛኛው ይነገር ነበር፡፡ ምንም እንኳ በ1950ዎቹ ወዲህ የክመንቲሳ ቋንቋ ተናጋሪ የነበረው ወደ ክርስትና እምነት የተለወጠና የተናጋሪው ቁጥር እየቀነሰ ቢመጣም የክመንቲሳ ቋንቋ በአሁኑ ሰዓት ጮጮቅ፣ በጃልሽም፣ በድኩላጌ፣ ሰራግና፣ ሰራባ፣ ተምበራ እንዲሁም አይከል ዙሪያ በእነዚህ መንደሮች ይነገራል፡፡

ከ2006 እስከ 2011 ዓ.ም በነበረው የማንነት ጥያቄ መሰረት የክመንት ማህበረሰብ ቋንቋውን ለመማር ፍላጎት ስላለው የክመንት ሃይማኖት ኃላፊ በሆኑት ወንበር አማረ ሙሉነህ የክመንት ቄሶችን (ገላለካ) የሚባሉትን አጋዥ ቄሶችንና ዲያቆናትን ቋንቋው በሚነገርበት ቀበሌዎች በማደራጀት እንዲማሩ ተደረገ፡፡

በአካባቢውም በስፋት አማርኛ ቋንቋ የሚነገር ሲሆን፤ በውስን ሰዎች ደግሞ ለሃይማኖታዊ ተግባር ክመንቲሳ ይነገራል ቋንቋውን የሚናገሩት የክመንት ሃይማኖት ተከታዮች ብቻ አይደሉም ወደ ክርስትና ሃይማኖት የተሻገሩትም ቋንቋውን ለመናገር ወደ ኋላ አይሉም፡፡ ይህን ቄስ ቢምር አስናቀው በሚከተለው አፈ ታሪክ ያስረዳሉ፡፡

> *"አንድ ሰው ሶስት ልጆች ነበሩት፤ እነዚህን ልጆችም አንዲቱን ትግሬ ወሰዳት፤ አንዲቱን ክመንት ወሰዳት፣ አንዲቱን ደግሞ አማራ ወሰዳት፡፡ የእነዚህን ልጆች ቋንቋ በሙሉ እናቲቱ ታውቃለች፡፡ በዛን ጊዜ የአንዲቱን ልጅ ባል ቤት ሲሄድ ለቤተሰቡ በግ አርዶ የሚያበላው እራሱ ነው፡፡ በዚያ ሰዓት የልጅቱን ባል ክመንት ጀይዳ ነው ሲል፣ ትግሬ ለቆጣ ነው ሲል አማራ አቆማዳ ነው እየተባባሉ እርስ በራሳቸው ሲጣሉ እናቲቱ ኧይ! ልጆቼ ቋንቋችሁ ነው እንጂ ልባችሁ አንድ ነው ስትል ነገሩን አዳምጠው ተስማምተው በሉ ይባላል" (ቃለ መጠይቅ፣ ቄስ ቢምር አስናቀው 13/06/2011)፡፡*

በኢትዮጵያ ውስጥ ለመጥፋት በከባድ አደጋ ውስጥ ከሚገኙ ቋንቋዎች መካከል ክመንቲሳ ግንባር ቀደም እንደሆነ እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

> *Kemat Certainly is one of the most" endangered" languages in Ethiopia already considered "dead" by some linguistic. But it was only recently that a linguistic survey team has reported its continued existence /Zelalem Leyew, 2003:4).*

ዘላለም በጥናታቸው የክመንት ህዝብ በሚኖርባቸው ቦታዎች ውስጥ ክመንቲሳ ቋንቋን ቀላቅለው በመናገር እንጂ ብቻውን የሚናገር አንድ ክመንት እንኳን ማግኘት ከባድ እንደነበር አስፍረዋል፡፡ በራሱ ተናጋሪዎች እንኳ ቢሆን ብዙውን ጊዜ ክመንቲሳ ቋንቋ እንደማይነገር ነው፡፡ ቢነገርም ለውስን ተግባራት ለጸሎትና ሚስጥር ለማውራት ብቻ ነው፡፡ እንዲሁም አማርኛ ቋንቋ በክመንቶች ማህበረሰብ የዕለት ተዕለት ተግባራትና እንቅስቃሴዎች ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያለው ነው፡፡ የክመንቲሳ ቋንቋ ተናጋሪዎች በ50ዎቹ እና ከዚያ በላይ ዕድሜ ክልል የሆኑ በገጠር ቀበሌዎች ውስጥ የሚገኙ ቋንቋውን የሚናገሩ ሲሆን በከተማ የሚገኙት የክመንት ማህበረሰቦች ደግሞ ቋንቋውን የረሱት እንደሚመስል እና በንግግራቸውም አማርኛ ቋንቋን እንደሚቀላቀሉ ዘላለም ገልጸዋል፡፡

> *ለክመንት ቋንቋ መዳከም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ በርካታ የሆኑ ተፈጥሯዊና ታሪካዊ ክስተቶች አሉ፡፡ ለዚህ ክስተት አንዱ የሆነው የጭልጋና የጎንደር መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ነው፡፡ በ17ኛው እና በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ የኢትዮጵያ ነገስታት መገኛ ቦታቸውን ጎንደር ከተማ ያደረጉ በክመንተኛ ቋንቋና ባህል ላይ ከፍተኛ የሆነ ጫና እንዲደረግ ሆኗል፡፡ ጎንደር ከተማ ከ1630ዎቹ የኢትዮጵያ ዋና መናገሻ እንደነበረች ዘላለም Sasse (1992፣ 73)ን በመጥቀስ ለዚህም በጎንደር ከተማ ዙሪያ የነበሩት ክማንቶች የአማርኛ ቋንቋ ተፅዕኖ እንዲደረግባቸው ሆነ፡፡ ሌላው በኢትዮጵያና በሱዳን በተዘረጋው የንግድ ግንኙነት የአማራ ማህበረሰብ ወደ መተማ ጉዞ ሲያደርግ የጭልጋን መሬት አቋርጦ ሲጓዝ ሁለቱም ህዝቦች እንዲጣመሩ ከፍተኛ የሆነ ዕድል ከፍቷል (2003፡33-35)፡፡*

ቆይቶ ደግሞ ከጎንደር እስከ መተማ 183 ኪ.ሜ ርዝመት ያለውን ረጅም መንገድ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ሲያሰሩ ቋንቋውን ለመልመድ ያገዛቸው የመጀመሪያው መንገድ በሚሰራበት ወቅት ሲሆን በመቀጠል የመንገድ ስራው ካለቀ በኋላ ደግሞ ለንግድ ስራ ጉዞ በሚያደርጉበት ጊዜ በዚህ ሰዓት ሁለቱ ህዝቦች በመገናኘት የአማርኛ ቋንቋን መልመድ ቻሉ፡፡

ሌላው በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት በጭልጋ ምድር ዘመናዊ የትምህርት መስፋፋት ተጀመረ፡፡ በዘመኑም በርከት ያሉ የአንደኛ ደረጃና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተከፈቱ፡፡ በየትምህርት ቤቶችም የሚማሩት ወይም የመማር ማስተማሩ ሂደትም በአማርኛ ቋንቋ ነው፡፡ የዚህ ተፅዕኖም በክመንት ማህበረሰብ የአማርኛ ቋንቋ ሰርፆ የክመንቲሳ ቋንቋ እንዲጠፋ ተደርጓል (ዘላለም 2003፡38)፡፡

## 3.3 የክመንት ማህበረሰብ መተዳደሪያ

የማዕከላዊ ስታቲስቲካል በሰጠኝ መረጃ መሰረት በ1994 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሕዝብና ቤት ቆጠራ በተደረገው የክመንት ማህበረሰብ ቁጥር 172,291 ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 6,705 የከተማ ነዋሪዎች በንግድና በመንግስት ስራ የሚተዳደሩ ናቸው እንዲሁም 165,586 የሚሆኑት ሰዎች በገጠራማዋ አካባቢ በእርሻ ስራ የሚተዳደሩ ናቸው (CSA 1994)::

የወረዳው የቆዳ ስፋት 322,262 ካ.ሜ ነው፡፡ የወረዳው ወይናደጋ ክፍል 67 በመቶውን ሲይዝ ቆላማው ክፍል ደግሞ 33 በመቶውን የያዘ ነው፡፡ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጡም ወጣ ገባ እና ተራራማ ሲሆን  የቀረው ደግሞ ሜዳማ ክፍል ነው፡፡ 75 በመቶው የሚሆነው አርሶ አደር ሲሆን 25 በመቶው የሚሆነው የከተማ ነዋሪ ነው፡፡ በወረዳው የወይናደጋው ክፍል በግ አርቢ ሲሆን ቆላማው ክፍል ደግሞ የፍየል አርቢ ነው (ቃለ መጠይቅ፣ ኪዳነማርያም አበራ 06/06/2011)፡፡

> ዘላለም የክመንት ማህበረሰብ አርሶ አደርና ጠንካራ ገበሬ መሆኑን ሲገልጹ፡- "*Except for those who live in towns the kemant people by and large are farmers. Those who live in towns are traders, government employees, etc. like the Amhara of the area kemants do not have a unique occupation distinct from those of neighboring peoples. They own land, urban or rural and most of them lead their life as a farmers of traders" /Zelalem Leyew, 2003:6/.*

በወረዳው ጤፍ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ዘንጋዳ፣ ዳጉሳ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ ሽምብራ፣ ባቄላ፣ አተር፣ ድንች የመሳሰሉት ይመረታሉ፡፡ ሌላው ከቅመማ ቅመም ነጭ ሽንኩርት፣ ቀይ ሽንኩርት፣ ጥቁር አዝሙድ፣ ነጭ አዝሙድ፣ ዝንጅብል፣ ዝቃቅቤ /በሶብላ፣ ጤና አዳም፣ ጎመንዘር፣አብሽ እና በርበሬ የመሳሰሉት ይመረታሉ፡፡ ፕሮፌሰር ሲ..ጋምስት እንደጻፈው

> *የክመንት ኢኮኖሚ ከስር መሰረቱ የሚበሉ ሰብሎችን ማጣፈጫ ቅመሞችን በማምረት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ሙሉ ጊዜያቸውን በፖለቲካና በሃይማኖት ጉዳዮች ከሚያሳልፉት ወንበሩ እና በትርፍ ጊዜያቸው የእርሻ ስራ እያከናወኑ በቅስናና በቢሮ ስራ ከተጠመዱት የመንግስት ሰራተኞች በስተቀር ማንኛውም ክመንት የሙሉ ጊዜ ስራው ግብርና ነው /ትርጉም ባዩ ቦጋለ፡1993፡126/*

ከዛፍ ዘሮች ደግሞ በወይናደጋው ክፍል ብሳና፣ ባህርዛፍ፣ ወይራ፣ ችብሀ፣ ዋንዛ፣ ዋርካ፣ ደቅማ፣ ባንባ፣ እንዶድ፣ ሾላ፣ እሼ፣ አጣጥ… የመሳሰሉት ሲበቅሉ፤ ቆላው ክፍል ደግሞ ክክራ፣ ግማርዳ፣ ቁልቋል፣ ገመጣጤ፣ አጋም፣ ግራር፣ ሎሚ፣ እንኮይ፣ ኮሽም… የመሳሰሉት እሾህማ ዛፎች ይበቅላሉ።

በቆላማው ክፍል የሚኖሩ የዱር እንስሳት ደግሞ ጦጣ፣ ዝንጀሮ፣ ጉሬላ፣ ነብር፣ ጉሬዛ፣ ጅብ፣ ድኩላ፣ ሚዳቋ፣ ሰሳ፣ ፌቆ፣ እሽኮኮ ይገኙበታል (ቃለ መጠይቅ ኪ/ማርያም 07/06/2011)።

የአውራሪስ ጥርስ፣ የዝሆን ጥርስ፣ ጥንታዊ የአጥንት ቅሪት፣ የዘር ቅሪት፣ ያልታወቀ ቅሬት፣ የድንጋይ ከሰል፣ ጥናታዊ የጋርዮሽ ስርዓት መገልገያ መሳሪያ፣ ወደ ድንጋይ የተቀየረ የእንጨት ቅሬት፣ በድንጋይ ቅርጽ የተገኘ የቡና ቅጠል ሲሆኑ እነዚህም በወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ውስጥ እያንዳንዳቸው ቦታ ተሰጥቷቸው ለቅርስነት ይጎበኛሉ።

ሌሎች ደግሞ በወረዳው ውስጥ እና በወረዳው ዙሪያ የሚገኙ የአምልኮ ቦታዎች ናቸው። እነሱም አይከል ከከተማው በስተምስራቅ አንትራ ዋሻ ይገኛል፤ ከከተማው በስተምዕራብ አንዘይመርኩ ዋሻ (ፀበል) እና ጫካ ውስጥ የምትገኝ ቅድስት አርሴማ ገዳም ይገኛሉ (ቃለ መጠይቅ፣ ወ/ሮ አንጓች ካሳሁን 07/06/2011)።

አይከል ከከተማው ቀበሌ ሁለት ከፍርድ ቤቱ ጎን የምትገኘው ባህላዊ የአምልኮ ቦታ "እሜቴ አይከል" ትገኛለች። ሌላው ከከተማው  በስተምስራቅ በኩል ሦስት ኪሎ ሜትር ርቃ የምትገኝ "ጉልት ሀምሳ ፈጅ ማርያም" በውስጧ የተለያዩ የብራና ጽሁፎች፣ የወርቅ መስቀሎች እና የብር መስቀሎች ይገኙበታል።

## 3.4 የክመንት ማህበረሰብ ሃይማኖት

የክመንት ማህበረሰብ ሀይማኖት ህገ ልቦና በተፈጥሮ የተሰጠ በሰው አዕምሮ ውስጥ የሚገኝ ያልተጻፈ ህግ፣ መርሕ ወይም መመሪያ (የመጽሀፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ 2008 ዓ.ም)።

ሃይማኖት ማለት ቋሚ ሆኖ በተደጋጋሚ የሚደረግ ይሆንልኛል፣ ይደረግልኛል፣ ይፈፀምልኛል ተብሎ የታቀደበት ጉዳይ የማይለወጥ፣ የማይቀየር፣ ባለበት ቀጣይነት ሆኖ የሚሄድና ፀንቶ የሚኖር ማለት ነው።

በ1950ዎቹ ወዲህ የክመንት ማህበረሰብ ወደ ክርስትና ሃይማኖት መለወጥ የጀመረበት ጊዜ ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ቄስ ለአከ ማርያምን ልከው እንዲጠመቁ በማድረጋቸው አብዛኛው የማህበረሰቡ ክፍል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትናን ተከታይ

እንዲሆኑ የማህበረሰቡ ክፍል በግልጽ ያስረዳል፡፡ ምንም እንኳን የክመንት ማህበረሰብ የነበረው በይበልጥ የክርስትና ሃይማኖትን ተቀባይ ቢሆንም ጥቂቶቹ ደግሞ የህገ ልቦናን እምነት እንደጠበቁ ይገኛሉ፡፡

የክመንት ማህበረሰብም በዋናነት የሚመሩት ወንበሩ ናቸው፡፡ የክመንት ቀሳውስት የበላይ በሆነው የፍትህ የአመራር ስልጣን ባለው ሰው መመራት በክመንት ሃይማኖት ውስጥ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው “ክብር” ወይም “ከመዘና” በሚባለው ነው፡፡

የቡድን ተወያዮች እንደገለጹት ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ሲቆጠር ለክመንት ማህበረሰብ የቀለም አባቱ ህገ-ልቦና ነው፡፡ በዚህ ምክንያት አማራ፣ እስላም፣ ካይላና ክመንት ሆነው ለራሳቸው የሚሆን ህግ ለመቀበል ወደ አደራ ሄዱ፡፡ አደራም (እግዚአብሔር) ለአማራ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ለካይላ ኦሪት፣ ለእስላም ቁርዓን ሲሰጣቸው ለአንተስ ምን ልስጥህ ሲለው፤ “አይ አባቴ! እኔ በቃሌ አድራለሁ” ሲለው አደራም በቃልህ ብታድርም “እመነኝ እታመንህአለሁ፣ ለምነኝ እለመንሀለሁ፣ በሰማይ በምድር ቃል ገብቼልሀለሁ፡፡ “ኩም ጋው” (ቃል ኪዳን) ገባለት (የቡድን ተወያዮች 10/06/2011)፡፡

አደራም ደግሞ ለልጅህ ይሆናል ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ ለክመንት ሲሰጠው በልቤ ይዤዋለሁ “ይሊቬንልሲ” በማለት ለአደራው  መለሰለት፡፡ ይህም የሚያስረዳው የሃይማኖታቸውን ጽሑፍ አልባነት ሚስጢራቸውን የሚገልጹበት የቃል ታሪክ ነው፡፡

በህገ ልቦና እምነት ተከታዮች ውስጥ የሚፀልዩትም፣ የሚቀድሱትም፣ በቃል ያቀርባሉ እንጂ ጽሑፍ የሚባል ወይም መጽሐፍ ቅዱስ የሚባል አይጠቀሙም፡፡ በህገ ልቦና የፀሎት ስነ ስርዓታቸውን የሚያሳዩት በለቅሶ ስነ ስርዓት ላይ ሙት አመት ሲከበር፣ በሽታ ሲበዛ፣ ጦርነት ሲኖር እንዲሁም የተለያዩ ችግሮች ሲፈጠሩ ዘር በመቁጠር የህግ ልቦናውን የፀሎት ስነ ስርዓት ባወቁና በተመረጡ ሰዎች የሃይማኖቱን ሚስጢራዊ ሀሳብ በቃል የሚያቀርቡበት ነው /የቡድን ተወያዮች 10/06/2011)፡፡

በህገ ልቦና ሃይማኖት የፀሎት ስርዓትን የሚያከውነው ጥቅጥቅ ባለ ደን ወይም ዲቢት ውስጥ ነው፡፡ የሚፀልዩትም የህገ እግዚአብሔር ህግ በልባቸው ተመዝግቦና ታትሞ ስለተቀመጠ የፀሎት ስነ ስርዓቱን የሚያስተላልፉት በቃላቸው ነው፡፡

> *The followers of the kemant religion do not have any written materials to which they refer in prayers, sermons or other rites. They pray in the kemant language and they have distnict place for their prayers. The prayers called Adere wamber place of God (Zelalem Leyew 2002:8).*

በክመንት ማህበረሰብ የፀሎት ስነ ስርዓት ሲካሄድ አምስት ቄሶች ናቸው፡፡ ወንበሩም በፀሎት ስነ ስርዓት ቀን ሲያውጁ አምስቱም “ገላለካ” (አጋዥ ቄሶች) ምንም ገላቸው ንፁህ ቢሆንም ደግመው ታጥበው ንፁህ ነጭ ልብስ እስከ ጥምጣማቸው አድርገው መገኘት እንዳላባቸው የበላይ የሆኑት ወንበሩ ያሳስባሉ፡፡ እነዚህ አጋዥ ቄሶችም ወንበሩ /የሃይማኖት መሪው/ ወደ ፀሎት ቦታው ሲመጡ የሚቀመጡበት ወንበር አዘጋጅተው ይጠብቃሉ፡፡ የፀሎት ስነ ስርዓቱም በድግና ውስጥ ነው፡፡

ወንበሩም ከለበሱት ነጭ ቀሚስና ነጭ ሱሪ ላይ በቀይ ጥለት የተሰራ ጋቢ በላዩ ላይ ለብሰው ቀይ ጥለት ያለው ካባ በመደረብ በተዘጋጀላቸው ወንበር ላይ ይቀመጣሉ፡፡ አጋዥ ቄሶችም በጋቢያቸው በላይ እጃቸውን በማውጣት ዘንጋቸውን ይዘው ፊታቸውን ወደ ፀሐይ መውጫ በማድረግ ተሰልፈው ይቆማሉ፡፡

ይህን የሃይማኖት ስርዓት ካደረጉ በኋላ ከወንበሩ ጀምሮ እስከ ምዕመናት ድረስ ሁሉም ቦታውን ይይዛል፡፡ ከሃይማኖት መሪው በስተቀር ሁሉም ጥምጣማቸውን ፈትተው፤ ዘንጋቸውን ከጎናቸው ካስቀመጡ በኋላ ወደ ቅዳሲያቸው ገብተው በሃይማኖት መሪው መሰረት ስርዓቱን ያከናውናሉ፡ (የቡድን ተወያዮች 18/06/2011)፡፡

ሌላው “ክብር” ወይም “ከመዘና” የሚባለው ነው፡፡ ይህ በክመንት ሃይማኖት ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ሲሆን፤ የልሸና ቀይ ወይም ነጭ በግ፣ ያላጠቃ ቀይ ወይም ነጭ ወይፈን የሚያርደው ክብር ወይም ከመዘና ይባላል፡፡ መስዋዕቱ በሚቀርብበት ሰዓትም እግር ይዞ የሚያሳርደው ይተንቲ ወይም ገላለካ ይባላል፡፡ ከሁለቱም የዘር አቀጣጠር አይነቶች ትልቅ ቦታ የሚሰጠው “ክብር” ሲሆን፤ ይተንቲው ደግሞ የክብሩ ተላላኪና አጋዥ ነው፡፡ በሃይማኖቱ ክብር ወይም ይተንቲ መሆን የሚቻለው በፍላጎት ሳይሆን፤ በራሳቸው የዘር አቀጣጠር ስርዓት ነው፤ ዘሩን ቆጥረው የሚያሳውቁት የከመዝናው ሚስት “አንዛ” እንደምትባል የይተንቲው ወይም የገላላከው “ሰንክራ” ትባላለች፡፡ ሰንክራን፣ አንዛ፣ የተተራንዛ፣ እንተላ ማለት የሃይማኖት ቄሶች ለእመቤታችን የአክብሮት ስም የሚጠቀሙበት ነው፡፡

የክመንት ማህበረሰብ ስለ ሃይማኖቱ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ትስስር ያስቀመጠውን አፈ ታሪክ ወንበሩ ሲያስረዱ እንዲህ አሉ።

> *ክመንት የአደራ ዘር ሲሆን በሰማይ ብለጪታና ጉርምርምታ ገርገሪምስና ታንቴ የሚባሉ ሁለት ሰዎች ተፈጠሩ። በመቀጠልም ገርገሪምስና ታንቴም አብረው ሲኖሩ የተተራንዛ የምትባል ሴት ተፈጠረች። አደራ ታሪኩን ሊፈጥርባት ሲፈልግ የተተራንዛ እስከ 18 ዓመት አፏ የማይናገር፣ አይኗ የማያይ ቆንጆ መልከ መልካም ሴት አድርጎ አስቀመጣት። አደራም ከእለታት አንድ ቀን መጥቶ ምን ሆንሽ "ዳንኪናረው" ሲላት ዓይኗም አየ፣ አፏም ተናገረ አለ" (ቃለ መጠይቅ ወንበረ አማረ ሙሉነህ 06/06/2011)።*

የተተራንዛም እንዲህ ስትል ተናገረች።

> *ምዝቛና ከነናራቲስና ታኦትፈቲ ወርሰናያ ኪያበ አውት ፈቲ ደውል ከበከባ ወልሸቲ ሸበብታ እዝ ወለለገ ሸቢን ተጠባብታይ እታ እላ በላ ሳምበከ ኢትቛናስ ነበዝዮም ከለብት ወተርሸው ከለብትላ ስመው" /ወንበሩ/።*

የተተራንዛም በደስታ ብዛት አባቴ ገርገሪምስ እናቴ ታንቴም የት ሄዱ ብላ ስትየይቅና ስትጮህ ሰምተው በደስታ ብዛት እናትና አባቷ ገበያ ከሄዱበት መጥተው እልልታውን አቀለጡት። /ትርጉም አባ ወንበሩ/ አደራም ይህን ታምር ከፈጠረ በኋላ አንዛን አግብቶ ሲኖር፤ ከጭልጋ በስተምስራቅ በሚገኘው አንዘይ መርኩ ዋሻ ወይም ፀበል ወስዶ ሲሰውራት አንዘይ ወደ ሰማይ አረገች። ቆይቶም አደራ ወደ ሰማይ አረገ። አደራ፣/ አደረንኪ/፣ /አነይር/ ቂሶቹ ለእግዚአብሔር የክብር ስም የሚሰጡት ነው። በክመንት ሃይማኖት አንዘይ መርኩ ጸበል ዋሻ እየተባለ የሚጠራው የታመመ የሚድንበት፣ መሀን የሚወልድበት፣ በዓመት አራት ጊዜ እየተፀለየ በሰኔ ወር፣ በነሀሴ ወር፣ በጳጉሜና በጥቅምት ወር ማንኛውም ህዝብ ፀበሉን እየጠጣ የሚፈወስበት የሚድንበት ነው ።

> *"Anzaymerkum a well of mineral water which seems to be essential to the rites of the kemant religion. At anzaymerkum there is a small cave where the water springs oat, and it is surprising that people should go down the steep and slippery path which leads to this well, to reach the water" /Zelalem Leyew, 2002:8).*

ፀበሉን እየቀዱ የሚሰጡትም አጋዥ ቄሱ "ገላለከው" ቄስ ነው። ማህበረሰቡም ፀበሉን ጠጥቶ ተስሎ በዓመቱ መሀን የሆነው ወልዶ የታመመው ድኖ በደስታ ስለቱን አስገብቶ ይሄዳል። በክመንት ሃይማኖት በተለይ ሰው ሲሞት የሙት ዓመቱ ስርዓተ ቅዳሴ የሚደረገው ዘር በመቁጠር ነው። ለዚህም ማሳያ የክመንት የዘር ሀረግ ሲቆጠር ህገ ወንጌል ከሰማያ ሰማያት ወረደ ከድንግል ማርያም ተወለደ። የተወለደውም አደራ ነው፤ በማለት ከመጀመሪያው ወንበር እስከ አሁን ካለበት ወንበር ቆጥረው በቅደም ተከተል አስቀምጠዋል። እነሱም፦-

> *እግዚአብሔር አደረይኪን ወለደ፣ አደረይኪ ክብሯን ወለደ፣ ክብሯ ገድኙንን ወለደ፣ ገድኙን ልትኙንን ወለደ፣ ልትኙን ትግበግናን ወለደ፣ ትግባግና ገብተግናን ወለደ፣ ገብተግና አሸሚን ወለደ፣ አሸሚን ፍርድኙን ወለደ፣ ፍርድኙን አዚኻን ወለደ፣ አዚኻን ምዝግኒን ወለደ፣ ምዝግኒ ሸኺያን ወለደ፣ ሸኺያን ሙዞን ወለደ፣ ሙዞን ፍዛደርን ወለደ፣ ፍዘደር ወርቁን ወለደ፣ ወርቁ ዘውዱን ወለደ፣ ዘውዱ መርሻን ወለደ፣ መርሻ ሙሉነህን ወለደ፣ ሙሉነህ አማረን ወለደ (ቃለ መጠይቅ፣ ወንበር አማረ ሙሉነህ 06/06/2011)።*

በክመንት ሃይማኖት ምዝግና ብለው የሚያከብሩት ዓለምና በውስጧ ያሉ ፍጥረታት ሁሉ የተፈጠሩበት ነው ይላሉ። ከዚህ ቀደም እንደገለፅኩት ምዝግና የፈጣሪያቸው መጠሪያ ነው። ይህ ፈጣሪያቸውም በዓለም ላይ በውስጧ ያሉትን ነገሮች ሁሉ የፈጠረው ሀሙስ ቀን ነው ብለው ያምናሉ። በዚህም ምክንያት ሀሙስ ቀን ለክመንት ማህበረሰብ ትልቅ ቦታ ይሰጡታል። ይህንንም በክርስቲያኖች እሁድን እንደሚያከብሩት ማለት ነው።

ግበሩኸ "አብሳሪ መላእክት" የሚሉት ሲሆን የአደረይኪን እናት /የተተራንዘን/ ወርዶ ያናገረበት ሀሙስ ቀን ነው ይላሉ። በክመንት ሃይማኖት አደራን በተጠነሰሰ በሰባተኛው ቀን ሀሙስ ቀን ተወለደ ይላሉ።

ሰባቱን ቀንም እንደ ወር ይቆጥሩታል። ምክንያቱም በክመንት ማህበረሰብ አንድ ሰው በሰባተኛ ወሩ ከተወለደ ያድጋል፣ በስምንተኛው ወሩ የተወለዱ ግን ይሞታሉ ብለው አሁን ድረስ በእምነቱ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ።

መልስ ባለመሰጠቱ ምክንያት በዞኑ አመራር መሰረት እና የክመንት ማህበረሰብ ተወላጅ ሆነው "እኛ የማህበረሰቡን ተወላጅ አይደለንም" በማለት ወረዳውን ቁጥር አንድ የክመንት ማህበረሰብ ቁጥር ሁለት ደግሞ የአማራ ማህበረሰብ በማለት የክልሉ መንግስት ባላወቀው ጉዳይ ከፍለውታል (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ አብርሃም ጉበኛ 06/06/2011)።

ይህ በመሆኑም ለጭልጋ ወረዳ ማህበረሰብ ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊ ቀውስ ሲያጋጥመው በተለይ ደግሞ የግብርና ስራን በተመለከተ፣ የትምህርት ተቋማትን በተመለከተ፣ የጤና ተቋማት፣ ማህበራዊ ግንኙነት ለከፋ አደጋ ባይሰጥም ቀዝቃዛና ተዳክሞ ይኖር ነበር፡፡

በ2011 ዓ.ም በተፈጠረው የእርስ በርስ ግጭት ሁለቱም ማህበረሰቦች ወልደው ተዋልደው ብሎ ጠጡ ሲባባሉ በኖሩበት አካባቢ ሳያስቡት በተፈጠረው ክፍተት ከትዳራቸው በመፈናቀል የወለዱትን ልጅ አንተ የክመንት ልጅህን አንተ የአማራ ልጅ ነህ በመባባል በህይወታቸው ላይ ምስቅልቅል ፈጠረባቸው፡፡ በብሔር ምክንያት በህሊናቸው ጨለማ የሆነ እሽክርክሪት ፈጠረባቸው፤ ረሀቡ፣ ችግሩ፣ ስቃየቱ ሞቱ እጃቸውን በእጃቸው ቆረጡ፡፡

## 3.5 የክመንት ማህበረሰብ ባህላዊ አስተዳደር

በክመንት ማህበረሰብ አስተዳዳሪ ሲመረጥ “የክብር” ዘር ያለው ሆኖ በዕውቀት የላቀ፣ የመጠቀ፣ የዳኝነት ችሎታ ያለው ፍርድ አዋቂ፣ ለየት ያለ ጥበብን ያሳየ ሲሆን በህዝብ ተመርጦ በማህበረሰቡ ውስጥ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በበላይነት ሆኖ የሚመራና የሚያስተዳድር ከፍተኛ ኃላፊነት የተሰጠው ነው፡፡ አንድ ወንበር ከተመረጠ በኋላ በህዝቡ ይመረቃል፡፡ ነባሩ ወንበር በሞት ምክንያት ያልተተኩ ከሆነ ከህዝቡ ጋር ሆነው አዲሱን ወንበር ይባርካሉ፡፡ ወንበሩ የክመንት ቀሳውስት ወይም ኃላፊ ብቻ ሳይሆን የዳኝነት እና የአመራር ስልጣን ያለው ሰው ነው፡፡ በመካከለኛ ስልጣን ባላቸው ሊፈታ ያልቻለውን ከአቅም በላይ ከሆነ የበላይ ከሆነው ወንበር ያመራል፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ወንበር አማረ ሙሉነህ 15/06/2011)፡፡

ይህንንም Gamst (1967) በሦስት መንገዶች ከፍሎ አይቷቸዋል፡፡ አንደኛው ከታች የሚገኘው የትልልቆች ሸንጎ ሲሆን በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታየውን ችግር አስቀድሞ ለመፍታት ጥረት የሚደረገው እዚያው ስፍራ ላይ ነው፡፡ ሁለተኛው መንገድ ደግሞ የከፍተኛና የዝቅተኛ ቀሳውስት ስብሰባ ሲሆን ሦስተኛው አካሄድ ደግሞ የሃይማኖትና የፖለቲካ የበላይ የሆነው ወንበር ነው በማለት ከፍሏቸዋል፡፡

የበላይ የሆነው ዳኛ ከፍተኛ ጥፋት ያጠፉትን ሰዎች ከእሱ በታች ለሆኑት አለቆች ያጠፉትን ነገር እንዲመረምራቸው ይደረጋል፡፡ መርማሪው አለቃ ጥፋት ያጠፉት ሰዎች “ሸርህ” ከተባለ ቦታ እንጨት ማጭድ፣ እንጨት ያልገባበት መጥረቢያ መሀላ ከሚያስምለው ቄስ ይሄዳሉ፡፡ ሲሄዱም በማጭድ ይቁረጠኝ፣ በመጥረቢያ ይፍለጠኝ ብሎ መማሉን ስለሚያውቅ ካልማለ ሀቁን ይናገራል፡፡ የሚያስምለው ቄስም ለወንበሩ ወይም ለዳኛው ይናገራል፡፡ አምኗል ከተባለ

ግማሹን ዕዳ ለተበዳይ ይከፍላል፣ ግማሹን ደግሞ ይማርለታል (ቃለ መጠይቅ፣ ወንበር አማረ ሙሉነህ 18/06/2011)፡፡



**ፎቶ 1፡- የህገ ልቦና እምነት የበላይ ኃላፊ ወንበር አማረ ሙሉነህ (ፎቶ በአጥኚዋ)**

ወንበሩ በህዝብ እንደተመረጠው ሁሉ ከፍተኛ ቄስ ወይም ከመዘና የሚባል ቄስ በህዝብ ይመረጣል፡፡ ይህም የሚመረጠው ከ "ክብር" ዘር ሲሆን፤ አባጋሪያ" የተባለው ዝቅተኛ ቄስ የሚመረጠው ደግሞ ከየታንቲ ዘር ይመጣል፡፡ እንደ ወንበሩ ሁሉ ቀሳውስት የሚመረጡት ከጥንት ጀምሮ የሃይማኖት መሪዎች ከሚወጡበት የዘር ሀረግ ካላቸው ጎሳዎች ነው፡፡

ይህን ስርዓት ካገኘ በኋላ በጥንቃቄ መማር ያለበት ፈተናውን አልፎ ቄስ ስለሆነ፤ ማህበረሰቡን ሲያገለግል ወይም ሲያሳልም እንዲህ በማለት ነው፡፡

> *በመስቀል ሳይሆን በቃሉ ይፍታህ እያለ በእጁ መዳፍ ማሳለም እንዳለበት፤ የወር አበባ የሆነች ሴት ከቅዳሴውም ሆነ ከቤት እንዳትገባ፤ ቄስ ሆኖ ሚስቱ የወር አበባ ከሆነች እስከ ሰባት ቀን ቅዳሴ ውስጥ አይገባም፡፡ ከ8 ቀን በኋላ ቢገባም እንኳን እስከ 40 ቀን ገላውን እየታጠበ መሆን አለበት፡፡" የሚባሉትን ህጎች ቅስና ያገኘ ሰው ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት ይናገራሉ (ቃለ መጠይቅ፣ ወንበር አማረ ሙሉነህ 18/06/2011)፡፡*

ወንበሩም ቄሶችንም ሆነ ማህበረሰቡን ሲያስተዳድሩ ቅዳሴያቸውና ፀሎታቸው በስመአብ ሳይባል እግዚአብሔርን ብቻ ማገልገል ነው፡፡

## 3.6 የክመንት ባህላዊ እምነት የፀሎት ስነ ስርዓቶች

የፀሎት ስነ ስርዓቶች የሚደረጉባቸው ትልልቅ ድግናዎች፣ ታሪካዊ የጸሎት ስነ ስርዓት የሚቀርብባቸው ቦታዎች ናቸው፡፡ በእነዚህ ድግናዎችም የተለያዩ መስዋዕቶች የሚቀርቡባቸው ሲሆን በማህበረሰቡ የተለያዩ ችግሮች ሲፈጠሩ፣ በሽታ ሲበዛ፣ ሞት ሲበዛ፣ ረሃብ ሲኖር መፍትሄ ይሰጥባቸዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ እንዲህ ያሉ ችግሮች እንዳይፈጠሩ ከመዘና የሚባሉት ቄሶች የውግዘት ስነ ስርዓት ያደርጋሉ፡፡ ቀጥሎ የጸሎት ስነ ስርዓቶችን በዝርዝር እንመልከት፡፡

### 3.6.1 አዳሪ ፈርዳዳ (የጌታ ፈረስ ረገጠ) ታሪካዊ የጸሎት ቦታ

በክመንት ሃይማኖት ብዙ የፀሎት ቦታዎች አሉ፡፡ ቢኖሩም ግን የጌታ ፈረስ ረገጠ የተሰኘው ለየት ያለ ታሪካዊ ቦታ ነው፡፡ በዚህ ታሪካዊ ቦታም የጸሎት ስርዓቱ የሚቀርበው በዓመት ሁለት ጊዜ በሰኔ እና በጥቅምት ነው፡፡ የፀሎት ስርዓቱም

*"ዳንጂ ሊሻ ሊሻ*

*ዳንጂል መሹል መሹልሻ"*

*በማለት ይጀመራል፡፡ "ዳንጂ ሊሻ ሊሻ" በሰኔ የሚፀለየው ፀሎት እግዚአብሔር ከክረምቱ ዶፍ፣ ከመብረቁ ጉርምርምታ፣ በክረምቱ በሞት እንዳትለየን፣ በሰላም፣ አክርመህ በሰላም ለመስከረም ፀሐይ አድርሰን ብለው የሚፀለይበት ጊዜ ነው፡፡ "ዳንጂል መሹል መሹልሻ" በጥቅምት የሚጸለይ ጸሎት ሲሆን ሰላም ያከርምክ*

የጌታ ፈረስ ረገጣን ታሪክ ወንበር ሙሉነህ በአፈ ታሪክ ሲያስረዱ

*ልትሁ የሚባል የአደራ አራተኛ ልጅ ቤተ መንግስት ገብቶ ሲያገለግል አንድ ቀን በድንጉላ ፈረስ ጋልቦ የመጣውን አገር ሲያስታውስ ከቤተ መንግስት ውስጥ ነው ያለው፡፡ ከዚያም በድንጋጤ ሲጮህ ለምን ትጮኻለህ ሲለው በድንጉላ ፈረስ ረግጬ የመጣሁት አገሬን ስሮጥበት ታየኝ፣ "ልሂድ ይፈቀድልኝ" ባለጊዜ ንጉሱም "ወዲያውኑ እንድትመለስ!" በማለት በቂጣ ፈቀዱለት፡፡ ልትሁ ወደመጣበት ሀገር በፈረስ እየጋለበ ሲያሰግር የልትኹ ታናሽ ወንድም ለቤተሰቦቹ*

*ሦስተኛ ልጅ የሆነው ገድኹ ፀሐይን ዝዘተ እና ከልትኹ ጋር አብረው እየሩሳሌም ተነስተው በድንጉላ ፈረስ እየጋለቡ ሜዳማ ከሆነው ቦታ ደምቢያ ሲደርሱ በኃይል ፈረሱን ሲያገሩት አንዲት ትልቅ አዛውንት ሴት ረግጠው ሲገድሉ ኧይ! እኒህ "ደምብከውገን" የደም መንደር ሆነ ብለው ረግጠውት ሄዱ፡፡*

*ገድኹ የዝዘታትን ፀሐይ እያስታወሰ ደምቢያን አቋርጠው አማኑኤልን በመሀል ሰንጥቀው "ኹራ" ከምትባል ቦታ ሲደርሱ ቋራን አቋርጠው ሲመለሱ ልትኹ መጀመሪያ በድንጉላ ፈረስ በተፈጥሮ የተነጠፈውን ድንጋይ ረግጦ ያለፈውን የፈረስ ኮቴ ሲያይ ይህ "የጌታ ፈረስ ረገጠ" ይሁን (ቃለ መጠይቅ ወንበር አማረ ሙሉነህ 06/06/2011) በማለት ተናገሩ፡፡*

በዚህ የፀሎት ቦታም ወንበሩ፣ ቄሱ፣ ዲያቆናት፣ መስዋዕት በማቅረብ የጸሎት ስነ ስርዓት ያደርጋሉ፡፡ ገድኹም የልትኹንን ታሪክ ተመለከተና እኔም የዝዘትኳትን ፀሐይ ልልቀቃት እና በቃኝ መሬት ልሳም ሲል ቀድማ ፀሐይ ወዲያውኑ ሽርተት አለችና ወደ መሬት ገባች፡፡

ልትኹንም ቃል በገባው መሰረት ወደ መጣበት  ወደ ንጉሱ ቤት ፈረሱን እያስጋለበ ከንጉሱ ቤት ሲደርስ ንጉሱ የለም፡፡ የንጉሱን አገልጋይ ወፍጮ እየፈጨች ሲያገኛት ልትኹን ፈረሱን የት ልሰረው ሲላት በጓሮው እሰረው አለችው፤ ልትኹንም አሰረው እና ገብቶ ተኛ፡፡ ንጉሱም በማግስቱ መጥቶ የት አደርክ? ሲለው ልትኹን መጥቼ ነው ያደረኩት አለው፤ ንጉሱም ሳያምን ቀረ፡፡ ልትሁን ለንጉሱ ፈረሱ ያደረበትን ሃያ ክንድ በግራ፣ ሃያ ክንድ በቀኝ የቆፈረውን መሬት ሲያሳየው አሁንም ንጉሱ አላመነም፤ ወዲያውኑ የንጉሱ አገልጋይ ለልትኹ ስትመሰክርለት፡፡

*ባቱ ገራይ*

*ባቱ ገረይ*

*ይፈርኺዝኖ ኹልኻልሰኾይ ይኻሊስ*

*ባቱ ገረይ ባቱ ገረይ*

*ፈረስ ያደረው ይታይ አትልም ወይ? አለችው፡፡*

ንጉሱም የአገልጋዩን ወይም የገረዲቱን ቃል ግጥም ሲሰማ ልትኹንን አመንኩ አለው፡፡ ልትኹን እየዞረ በፈረስ የረገጣት ሀገርም የክመንት ሀገር በመባል ከርከር፣ ትክል ድንጋይ፣ ጋባ ጋላገር፣ ጭልጋ ነው ይባላል፡፡



**ፎቶ 2 የህገ ልቦና ታሪካዊ የፀሎት ቦታ (ፎቶ በአጥኚዋ)**

## 3.6.2 ለፀሎቱ ክዋኔ የሚውሉ ቁሳቁሶች

**ቆሎ/ታዝ/፡-** ፀሎቱ ከመጀመሩ በፊት መጀመሪያ ገብስ ቆሎ፣ ሽምብራ ቆሎ ተቆልቶ ከፀሎት በኋላ የሚበላና መስዋዕት ከመቅረቡ በፊትም አካባቢው ይረጫል፡፡ ለጌታ መላእክተኛ የሚደረግ ክንውን ለባህሉም ደንብ እና የሃይማኖቱ ስርዓት ነው በማለት ነው፡፡

**ቂጣ/ላላ/፡-** ቆሎው ከተቆላ በኋላ ቂጣው የሚጋገርበት ስርዓት ሲሆን እንደ ቆሎው ሁሉ ቂጣውም ከመስዋዕት በፊት ተቆርሶ በአካባቢው ተቆርሶ ጣል ጣል በማድረግ የጌታ መላእክተኛን ለማቋደስ (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ኖራ በሪሁን 17/06/2011)፡፡

**መስዋዕት፡-** (መሰዋት) ለመስዋዕትነት የሚያቀርቡት በግ ከሆነ ያልሸና ወይም ከእንስት በግ ጋር ግንኙነት ያላደረገ ሲሆን እንዲሁም ዶሮ እና ያልሸና ወይፈን ይቀርባሉ፡፡ ዶሮም የራሱ የሆነ ስርዓት አለው፤ የዶሮ ቀይ ድምድም፣ ነጭ ድምድም እና ከበሬ ደግሞ ወይፈን የሚባለው ላም ለማጥቃት ያልደረሰ መሆን አለበት፡፡

ለመስዋዕት የቀረበችው በግ እንስት ከሆነች ከእሷ በፊት ቀድሞ ቀይ ድምድም አውራ ዶሮ መታረድ አለበት፡፡ ተባዕት የሆነ እንስሳ ሳይቀድም እንስት እንስሳ ልትታረድ አትችልም፡፡ ለመስዋዕትነት በሙሉ ጥቁር የሆነ አይቀርብም፡፡ ነገር ግን በወርሃ ግንቦት ከሆነ ግን ፀሎት ሲደረግ ጥቁር በግም ሆነ ጥቁር ዶሮ እና ወይፈን ይታረዳል፡፡ የዚህ ተምሳሌትነትም በግንቦት ወር ዝናብ ለማምጣት ጥቁር ደመና ሰማዩን በሙሉ አቅፎ በመያዝ ዝናብ መምጣቱን እንዲያመላክት በማሰብ ነው፡፡ በጥቅምት ወር ደግሞ ቀይ በግ ሊሰዋ ይችላል፤ የዝናቡ ወቅት አልፎ የእህል አጨዳው ውቂያው ወይም የፀደይ ወቅት እንዲመጣ በማሰብ ነው / ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ኖራ በሪሁን 13/06/2011/፡፡

**ማርና ጠላ/ኻቪያቛና ስላቻ/፡-** ከእንስራ የሚዘጋጅ ገንቦ የሚባል ማርና ጠላውን በጥብጦ ብርዝ በማድረግ ፀሎት ቦታው ላይ ይቀርባል፡፡ ማርና ጠላውን የሚያቀርቡበትም ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የአባቶች ባህል ስለሆነ በመሆኑ ነው፡፡

**ወተት /ሸቭ/፡-** የፈለገ ሰው እንደ ግዴታ ሳይሆንበት ወተት ለመስዋዕት ሊያቀርብ ይችላል፡፡ መስዋዕት በቀረበበት ሰዓት እየተረጨ ይቀመሳል፡፡ ሁሉም ለጌታ መስዋዕትነት የሚቀርብ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ግን ከምግብና መጠጥ ባለፈ ቁሶቹ መቋሚያ ይይዛሉ፡፡ መስዋዕት የሚቆላበት እና የሚጋገርበት ብረት ምጣድ እና እንጨትም ያስፈልጋሉ፡፡

### 3.6.3 የፀሎት ስነ ስርዓት ህግና ደንብ

- የወር አበባ የሆነች ሴት በሰባተኛው ቀን ካልነፃች በስተቀር የስርዓቱ ተከፋይ አትሆንም ወይም ህልመ ሌሊት ካየች
- ከሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ያደረገ ወንድ ወይም ህልመ ሌሊት ካየ
- ለፀሎት ስነ ስርዓቱ ወይም ለቂጣ መጋገሪያው ውሃውን በጠዋት ከምንጭ ቀድተው ራሳቸው ቁሶች ማምጣት ይኖርባቸዋል
- የወር አበባ ያቆመች ሴት ቂጣ ከሚጋገሩት ቁሶች ቀርባ ማገዝ ትችላለች
- ከፀሎት ቦታው ጫማ መጠቀም በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡ ወይም ጫማ መውለቅ አለበት
- በፀሎት ስነ ስርዓት ሰዓት እንቅስቃሴ ማድረግ፣ ወሬ ማውራት በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡
- በፀሎት ሰዓት ለፀሎቱ የመጣው ማህበረሰብ በሙሉ ተጀምሮ እስከሚያልቅ ድረስ መቆም እንጂ መቀመጥ በጥብቅ የተከለከለ ነው
- ፀሎት ሲደረግ ቁሶችም፣ ታዳሚውም ነጭ ልብስ በመልበስ ሴቶች አርባ ክንድ በመራቅ ቆመው ማስደረስ አላባቸው፡፡

እነዚህ ህግጋቶች በሙሉ ከተፈፀሙ ፀሎቱ በቀጥታ ለእግዚአብሔር እንደሚደርስና ማህበረሰቡም በፀሎቱ ተስፋ ስለሚያደርጉ ሙሉ በሙሉ ይተማመኑበታል፡፡ (ቃለ መጠይቅ ቄስ ጌጡ አያሌው 12/06/2011)፡፡

### 3.6.4 የጸሎት ስነ ስርዓት ቅደም ተከተል

በክመንት ማህበረሰብ አራት የፀሎት ስነ ስርዓት ቅደም ተከተሎች አሉ፡፡ እነሱም ኪዱስ ምዝግና፣ ሽወን፣ ገወተን፣ ለኧዊላ ናቸው፡፡

አንደኛው "ኪዱስ ምዝሻና" ምስጋና ለእግዚአብሔር ይድረስ ማለት ሲሆን ኪዱስ መዝሻናው ንሻን በማለት አደረይኪን ሦስት ጊዜ ያመሰግናሉ፡፡ ፀሎታቸው እንዲህ የሚል ነው፡፡

> *በሰላም ላዋልከን ላሳደርከን እዚህ ለመድረስ ያበቃህን ጌታዬ ምስጋና ይድረስህ፣ ወደፊትም ያሰብነውን ዓላማችን እንድታሳካልን እንማጸንሀለን" በማለት (ቃለ መጠይቅ፣ ቄስ ጌጡ አያሌው 12/06/2011)፡፡*

ምን ጊዜም ቢሆን ፀሎት ሲያደርሱ ቶሎ መልስ እንዲሰጣቸው አድርገው የመለመን፣ የመማጸን፣ ባህርይ አላቸው፡፡ ለምሳሌ "ሰማይን ያለምሰሶ ምድርን ያለ ካስማ" ያቆምከው ጌታ ለአንተ ምን ይገባሃል? ምስጋና ነው እንጂ በማለት የፈጣሪን ስራውን ድንቅ አምላክ መሆኑን ውክልና ሰጥተው ያመልካሉ፡፡ ይህ የፀሎት ስርዓት የሚያሳየው የፈለጉት ተሳክቶ ሲገኝ የሚደረግ የፀሎት ስነ ስርዓት ነው፡፡

ሁለተኛው " ሽወን" ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የልመና ፀሎት ነው፡፡ ይህም "ገላለካ" የሚባል አጋዥ ቄስ የሚያቀርበው የፀሎት ስነ ስርዓት ቀድሞ የሚጀምረው ነው፡፡ ለአደራውም ምስጋና የሚቀርብበት የልመና ፀሎት ስነ ስርዓት ነው፡፡ ልመናውም ስለ ሀገር፣ ስለ ማህበረሰቡ በሙሉ የአስታራቂነት፣ የምልጃ የልመና ፀሎት ነው፡፡ በምልጃና በመማፀኛ ሰዓትም ቄሶቹ በሙሉ የያዙትን ዘንግ መሬት ላይ ያስቀምጣሉ፡፡ ጥምጣማቸውንም ይፈታሉ፡፡

የዚህን ትዕምርትም "በፀሐይ አብስሎ በዝናብ አብቅሎ የሚመግበን አምላክ" ስለሆነ፣ አናታችንን ፀሐይ እየመታን ወገባችን ድጋፍ ሳያገኝ ቆመን መለመን፣ መማፀን አለብን በማለት ይገልፁታል፡፡

"ኪዱስ ምዝግና" የሚለውን የጸሎት አዝማች ሰባት ጊዜ ካሉ በኋላ ጥምጣማቸውን ብቻ በመጠምጠም ወደ እግዚአብሔር እጃቸውን በመዘርጋት በቅብብሎሽ በሚያምር ድምፅ፣ ዜማና

ቃና ለአምስት በመሆን ፀልየው ከጨረሱ በኋላ ዘንጋቸውን ወይም መቋሚያቸውን ያነሳሉ፡፡ ፀሎቱም የሚከተለው ነው፡፡

| **ክመንቲሳ** | **አማርኛው** |
| --- | --- |
| አደራ ዋስነ | እግዛብሄር ስማን |
| እንት መለይት | አንተ ጠብቀን |
| ቲሰራግ ጋሻል | ያንተ ፍጡር ነን |
| ሰራሻሴ ሚስታ | ፈጥረህ አትርሳን |
| በራሻ ሚስታ | ሰርተህ አትርሳ |
| ጠዋራዝ ሚስታ | ጠዋሪ አትንሳን |
| ዳግፍ የንታ ሚስታ | ደጋፊ አትንሳን |
| እንዴው ሽዋሻና ሰራግ ሻቢን | አሟሟታችንን አሳምረው |

(የቡድን ተወያዮች 12/06/2011)፡፡

የጸሎቱ ልመናም ሰላም እንዲሰፍን፣ ፍቅር አንድነት እንዲበዛ፣ ረሃብ ድርቅ እንዲጠፋ፣ ህፃናት እንዲያድጉ፣ የወንዝ ውሃዎች በጊዜው እንዲሞሉ፣ እህል በሰላም ወደ ጎተራ እንዲገባ፣ ሌባ እንዲጠፋ፣ ደሃ ተበደለ የሚል አስተዋይ ዳኛ እንዲሰጠን ከብቶች እንዲረቡ አደራ ይለመናል፡፡

ሶስተኛው ምርቃት (ገወተን) ምርቃት በሚካሄድበት ሰዓት ለተራብ ላበሉ፣ ለተጠማ ላጠጡ፣ ለተራቆተ ላለበሱ፣ ለሞተ ፍትሀት ላደረጉ፣ የወለደን ለጠየቁ፣ የተጣላን ላስታረቁ፣ የታመመን ለጠየቁ፣ ቤት ለሌለው ቤት ለሰሩ፣ መሬት ለሌለው መሬት ለሰጡ በሬ፣ ላም ለሌለው ለሰጡ፣ ወንዝ ላሻገሩ በአጠቃላይ ፍትህንና ፍርድን ለሰጡ የምርቃት ስነ ስርዓት የሚከወንበት ነው (ቃለ መጠይቅ አዛጉ አደመ 10/06/2011)፡፡

አራተኛው እግዚኦመሃረነ /ለኧዊላ/ በክመንት ማህበረሰብ ያሉ የድግና ቦታዎች ወይም የመቀበሪያ ቦታዎች በጮጮቅ የሚገኙ ሲሆን የድሮ የክመንት ባላባቶች የተቀበሩበት ቦታ “እግዚኦመሐረነ” እየተባለ ስማቸው እየተነሳ በገነት እንዲኖሩ የሚፀለይ የፀሎት ስነ ስርዓት ነው እንዲሁም ለተዝካር ሲደረግ በዚህ የፀሎት ስነ ስርዓት ይካሄዳል፡፡ ከድግናዎች ወይም ከድቢቶች መካከል ክድሲቲ፣ ሽልም፣ አምላ፣ ጃኑዳ፣ ያረን፣ ማርጌ፣ አባይ፣ ዞጋ፣ ማውራ፣ ሸውናዛ

የሚባሉት ይጠሩበታል። በእነዚህ ድግናዎችም ከጥንት የቀደሙ የክመንቲሳ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሞቱበት ሰዎች የሚገኙበት መካነ መቃብራቸው ነው።

### 3.6.5 የማይፈለጉ ድርጊቶችን የፈፀሙ የሚወገዙበት ስርዓቶች

ማህበረሰቡ ወደማያስፈልጉ ድርጊቶች ከመሄዳቸው በፊት ሦስት የስብከት ቀናቶች አሉ። እነሱም እሁድ፣ ማክሰኞ እና ሀሙስ የሚባሉ ቀናቶችን ተመርጠዋል።

*ቅዳሜ አትረሱ ትታረሳላችሁ*

*ቅዳሜ አትፍጩ ትፈጫላችሁ*

*ቅዳሜን አትረሱ ትታረሳላችሁ*

*ቅዳሜ አትለንቅጡ ትለነቀጣላችሁ*

*ቅዳሜ አትውቀጡ ትወቀጣላችሁ*

*ቅዳሜ የቆላችሁ ትቆላላችሁ በማለት ትምህርት ይሰጣል።*

"ምዝሻና" (ገርጊ) ማለት በሀምሌ ሁለት ሀሙስ ቀን የሚውል በዓል ሲሆን፤ "ግበሩኽ" በነሀሴ ሁለት የሚውል በዓል ነው። ሌላው ከእነዚህ በተጨማሪ እነዚህ በዓላቶችም ስራ ለመስራት ከተጠቀሙባቸው የውችንፍር መዓት፣ የበረዶ መዓት የሚያመጡ ናቸው። በማህበረሰቡ የሚፈሩ በዓላቶች ናቸው። ምክንያቱም አዝርዕት ይጠፋሉ፣ እንስሳት ይሞታሉ አጠቃላይ ተፈጥሮ ትወድማለች ብለው የሚያስቡበት ነው።

"ግበሩኽና" "ምዝግና" ተጨማሪ ተግባራቸው ገርጊስንኩና፣ ግበሩኽ ለበኩና ምዝሻና ኽረመይኪ፣ ኽርብኩና፣ ዲባስኩና፣ ሰባብተኽርብኩና፣ ይራተብትለይ ኽርብኩና ይባላሉ። እነዚህ መብረቅን የሚስቡ፣ ከሚስቱ ጋር ግብረ ስጋ ግንኙነት ያደረገ የወለደው የማይባረክ፣ የሰው ነብስ የሚያጠ፣ ለእናት ለአባቱ የሚታዘዝ፣ በቃሉ የማይጸና፣ ለሃይማኖቱ የማይቆረቆር ለቄስና ለወንበር የሚያገለግሉ ይሆናሉ። እነዚህን ህግጋቶች ያከበረ የወለደው ያድጋል፣ የዘራው ይበቅላል፣ ምርቱ ከጎተራው ይሞላል ይተረፈረፋል በአጠቃላይ ኑሮው የተስተካከለ ይሆናል/ (የቡድን ውይይት 10/06/2011)።

እነዚህን በዓላቶች የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮችም ያምኑበታል በተወገዙት ቀናቶች የዝናብ መዓት፣ ጭቅጭቅ/ ቀኑን ሙሉ ዝናብ ከዋለ፣ በረዶ ከወረደ፣ መብረቅ ከጣለ "ዛሬ እኮ" ግበሩኽ ወይም ምዝሻና" ናቸው ለምን አረሳችሁ፣ ለምን አረማችሁ ተባብለው ይነጋገራሉ፤ አይሰሩም።

በክርስትና ሃይማኖት ይህ ችግር ደግሞ ከተፈጠረ ለክመንት ቄሶች ይቅርታ አድርጉልን የተወገዙትን በዓላቶች ሰርተን ነበር በረዶውም ዝናቡም አለቀቀንም እና ፀሎት አድርጉልን ብሎ ማህበረሰቡ ብር በማዋጣት ሦስት ቄሶችን ወደ አካባቢያቸው ይወስዷቸዋል፡፡

የክርስትና እምነት ተከታይም ድሮ የክመንት ሃይማኖት ተከታይ በነበሩበት ሰዓት ህግና ደንቡን ጠንቅቀው ስለሚያውቁት ለፀሎቱ ስነ ስርዓት የሚቀርቡትን መስዋዕቶች ማለትም ዶሮ፣ ቆሎ፣ ማርብርዝ፣ ቂጣ፣ ጠላ፣ ንፁህ በሆነ ዛፍ ስር ዳስ ጥለው የፀሎት ስነ ስርዓቱን ያስደርሳሉ፤ በማህበረሰቡ የነበረው ችግርም ይቀረፋል፡፡

ስርዓቱ ጀምሮ ባሉት ስርዓቶች አማካኝነት በሰው ህይወት ውስጥ ሊኖር የሚገባውን መመሪያ ያንፀባርቃል፡፡ ሰው በራሱ መብትና ጉልበት ተጠቅሞ ትዕዛዛትን ማፍረስ፤ ከዚህ ባሻገር አስነዋሪ የሆኑትን ድርጊቶች እንዳይተገበር የራሱን ሚና ይጫወታል፡፡

የፀሎቱ ስነ ስርዓትም ሰው አሜን ብሎ እንዲቀበላቸው የሚያደርግ በራሱ መልስ ሰጪ ሆኖ የሚታይ ነው፡፡ የሚፀለየው ፀሎትም የቀደሙ የክመንት ሃይማኖት አባቶቻቸውን እየጠሩ ጸሎትም ሆነ ቅዳሴ ሲያደርሱም ለማህበረሰቡ ከየት መጣነት የራሱን መልስ ሰጥቶ ይታያል፡፡

# 4 የክመንት ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ

## 4.1 በክመንት ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ምንነት

በክመንት ማህበረሰብ ሞት የሚከሰተው በአደጋ ወይም በበሽታ ምክንያት እንጂ በእርጅና ምክንያት ይመጣል ብለው አያስቡም፡፡ ለምሳሌ እንደ ዛር፣ ሰይጣን፣ ክፉ ዓይነ ቡዳ በመሳሰሉት ይመጣሉ ብለው ያስባሉ፡፡

ባዩ (1993፡179) እንደገለጹት አንድ ራሱን የገደለ ሰው ሞትን ያለቀኑ እንዲመጣ በማድረጉ በቅዱስ ቦታዎች ቀብር አይደረግም፡፡ የለቅሶና የተዝካር ስነ ስርዓቶችም አይካሄዱለትም፡፡ እራስን በራስ መግደል ማለት ይህችን የተቀደሰች ህይወት መጥላትና ከተሰጠው ማህበራዊ ግዴታና ኃላፊነት መሸሽ ስለሆነ ክመንቶች ከሁሉም የከፋ ፀረ ማህበራዊ ድርጊት መሆኑን ያምናሉ፡፡ አንዲት ሴት በወር አበባ ጊዜ ከሞተች ቅዱስ ድግናዎችን ታረክሳለች ስለሚባል ከተባረከው የመቃብር ቦታ ክልል ውጭ /በድግናው ዙሪያ የሚች አስክሬን እንዲቀበር ይደረጋል፡፡

በዚህ ክፍል በክመንት ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔን የሚያሳዩ መረጃዎች ይተነተናሉ፡፡ የትንታኔው ትኩረትም በዋናነት የህጻናት ሞትና የትልቅ ሰው ሞት ናቸው፡፡ ቅድመ ሞት ክዋኔ፣ ጊዜ ሞት ክዋኔ፣ ቅድመ ቀብር ክዋኔ ጊዜ ቀብር ክዋኔ እና ድህረ ቀብር ክዋኔ ስርዓቶች ናቸው፡፡

በክመንት ማህበረሰብ "የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ" የተለያዩ ገፅታዎች አሉት፡፡ በማህበረሰቡ አንድ ሰው ሲሞት ቀድሞ በተነገረለት መሰረት ከለቅሶው ስነ-ስርዓት ላይ መገኘት ግድ ይለዋል፡፡ ምክንያቱም በማህበረሰቡ ሰው ሲሞት ብዙ ድምቀት ስለሌለው አጃቢን የሚፈልግ ስለሆነ ነው፡፡ በለቅሶ ስርዓት ላይ ታዳሚዎች ካልተገኙ ቀነ ቀጠሮ በመያዝ ከሦስተኛው ከለቅሶ ስርዓቱ ላይ መገኘት አለባቸው (የቡድን ተወያዮች፣ 16/06/2011)

በክመንት ማህበረሰብ ያለው የለቅሶ ስነ ስርዓት እኩል ቢሆንም የህፃናትና የትልቅ ሰው ከመቀበሪያ ቦታው እስከ አከፋፈን ስርዓቱ ይለያያል፡፡

## 4.2 የክመንት የመርዶ ለቅሶ ስርዓት

ይህ የሞት ክስተት ሲፈጠር ሟች በሞተበት አካባቢ የቀብር ስነ ስርዓቱ ይከናወናል። ለሟች ቤተሰቦች የለቅሶ መርዶ ቀድሞ ሳለመንገር ራቅ ሳለ ዘመድ ወይም ጎረቤት ይነገራል። መርዶውን የሰሙ ሰዎችም ለሟች ቤተሰብ ለማርዳት ይጨነቃሉ፣ ከቤታቸው ይወጣሉ ይገባሉ፣ ይርበተበታሉ፣ የሟችን ቤተሰቦች ቤታቸው ድረስ በመሄድ የተለያየ ጨዋታ ማጫወት፣ ማውራት የሟች ቤተሰቦች ወደ ስራ የሚሄዱ ከሆነ አትሂዱ ቡና ላፈላ ነው፣ ጠላም ልበጠብጥ ነው በማለት እያሳሳቁ እያዘናጉ ይቆያሉ።

በመቀጠልም የሟችን ቤተሰቦች ቤታቸው በመውሰድ ምግብ ያበላሉ፣ ቡና አፍልተው ይጠጣሉ፣ ጠላም ይጠጣሉ… የመሳሰሉትን ግብዣ አድርገው ያስተናግዳሉ። ይህ ሲሆን የሟች ቤተሰቦችም "ዛሬ ምን አላቸው" በማለት ይጠራጠራሉ።

"በባህሉ ከአንድ ሰው ቤት አንድ ችግር የሚፈጠር ከሆነ ህልም አየሁ ይባላል፤ ሞት ሊከሰት ከሆነም አፌን ደም ደም አለኝ፣ ምግብ አልበላሽ አለኝ፣ አያ እገሌን ፀጉሩን ተላጭቶ፣ እርቃኑን ቆሞ አየሁት… የመሳሰሉት ህልሞች ይታያሉ። ይህ ህልም ሲተረጎም በመጥፎ ነገር እንጂ በጥሩ ሲተረጉሙት አይታይም" /ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ማሩ ክፍሌ፣ 18/06/2011/

የሟች ቤተሰቦችም ከተጨናነቁ በኋላ ተረጋግተው ከተቀመጡት ያበሉት ያጠጡት ጎረቤቶች ወደ ሟች ሄደው ያረዳሉ። የሟች ቤተሰቦችም ግማሹ ደንግጦ ሲቆም፣ ግማሹ "እኔ አልሞት ምን እሆናለሁ እስከ ደሙ ታበሉኛላችሁ፣ታጠጡኛላችሁ" በማለት ያለቅሳሉ። በእርግጥ በክመንት ማህበረሰብ ምርር ተብሎ ባይለቀስም ሟች ከቤተሰብ ብዙ ጊዜ ተለያይቶ ኖሮ መርዶ ሲለቀስ የሟች ቤተሰቦች ለሶስት ቀን ድረስ እያለቀሱ እርማቸውን ያወጣሉ።

በሦስተኛው ቀንም "ደመር" የሚባል ልክ አስክሬን ከቤት እንደወጣ ተደርጎ የሚዘጋጅ የለቅሶ ስነ ስርዓት አለ። ይህ ደመር ለአንድ ወር ቀጠሮ ይሰጠዋል። ይህ የቀጠሮ ስነ ስርዓትም በአካባቢው አዲስ የቀብር ስነ ስርኣት ካለው እየተሄደ የአያ እገሌ ልጅ ወይም ባለቤት ለስራ ሄዶ ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለየን በዚህ ወር በዚህ ቀን የሟች ቤተሰቦች አላቅሱኝ ብለዋል ተብሎ በለቅሶ ቦታው ይነገራል (የቡድን ተወያዮች፣ 18/06/2011)።

የሟች ቤተሰቦች የተለመደውን አልባሳት /ሰይሻ/፣ ቁሳቁስ /ወፊርወፊር/ ወይም በሌላ መልኩ ካገ /ሽመነብስ ሼይን/፣ ዋንጫ /ክመንጃ/፣ ጌጣጌጥ እንደሚቹ ሁኔታ ይዘው ያለቅሳሉ። የመንግስት ሰራተኛ የለቅሶ መርዶ ከሆነ የሚያለቅሱ ያለቅሳሉ እንጂ ቁሳቁስ አይያዝም።

በመርዶ የለቅሶ ስርዓት ለቀስተኞች ከተለያየ አቅጣጫ ሲመጡ ፈረስ ያላቸው በተለያየ ጌጣጌጥ አልብሰው ጥሩምባ እየነፉ፣ ባንዲራ ይዘው ከመገናኛ መንገድ ተቀጣጥረው በአንድ ላይ ወደ ደመሩ ቦታ ይደርሳሉ፡፡

የሟች ቤተሰብም ጋቢውን አጣጥፈው በአራት መዓዘን ከጭንቅላት ላይ አድርገው እያለቀሱ የመጣውን ለቀስተኛ በቀኝ እጃቸው ትከሻቸውን በመደዳ እየነኩ ያለቅሳሉ፡፡ ለቀስተኛውም ጋቢ የተሸከሙትን የሟች ቤተሰቦች ፈረሱን ፊት ለፊት በማዞር ያለቅሳሉ፡፡ ይህም የሚያሳየው ትዕምርት የአስክሬኑ እንዳለ ለማስመሰል እና ሀዘንተኞች አይተው ሆዳቸው እንዲቆርጥ የሚደረግ ነው፡፡ የለቅሶው ስነ ስርዓት ከ4፡00 ሰዓት እስከ 7፡00 ሰዓት ከተጠናቀቀ በኋላ ከ 7፡30 ጀምሮ የተዘጋጀውን እህል ውሃ ለመጣው ለቀስተኛ እስከ 9፡00 ሰዓት አብልተው አጠጥተው ይሸኛሉ፡፡

የሟች ቤተሰቦችና የቅርብ ቤተ ዘመድ በሙሉ በድጋሚ የተዘጋጀውን ምግብ እስከ ሰባት ቀን በልተው ጠጥተው የተሰራውን ዳስ አፍርሰው ከሩቅ የመጡት የሟች ቤተሰብን አፅናንተው መክረው አካባቢውን አፀዳድተው ወደመጡበት ተሰነባብተው ይሄዳሉ፡፡

## 4.3 የህጻናት ቅድመ ሞት ክዋኔ (ክዳም ሼው)

በማህበረሰቡ አንዲት እናት እንደወለደች በሰባተኛ ቀኑ ከአንገቱ ማተብ ግርዛት እና ቁርባን ከተደረገለት ሟች ህፃን ድግናው (መቅበሪያ ቦታ) ውስጥ መቀበር ይችላል፡፡ የወለደችው አራስም ከቤት ውጭ ስትሆን በተለያየ ምክንያት በድንገት ህፃኑን ልትነጠቅ ትችላለች፡፡ በድንገት የተነጠቀችውን ህፃንም ድግና ውስጥ አይቀበርም፡፡

በባህሉ እነዚህን ስርዓቶች ሳያደርግ የሞተ ህፃን ድግና ውስጥ ወይም ድቢት ውስጥ ከተቀበረ ለማህበረሰቡ ከፍተኛ ችግር አለው ተብሎ ይታሰባል፡፡ የሟች ህጻን ቤተሰቦች ፍቅር፣ ሰላም፣ አንድነትን ያጣሉ ይባላል፡፡ ለማህበረሰቡ ችግር አለው የተባለው ሟች ህፃን የአንገት ማተብ ባለማድረጉ ምክንያት ነው እንጂ ጨቅላ ህፃናት እድገትን ያላገኙ መጥፎውንም፣ ጥሩውንም፣ ደጉንም ያለዩ እንዲሁም ሰምተውም አይተውም ያልጠገቡ ገና በለጋ እድሜያቸው የተቀጠፉ ስለሆነ የሚቀበሩበት ድግና ለብቻ የሆነው ሌላው ምክንያት ነው፡፡

ጨቅላ ህፃናት ሲሞቱ እግዚአብሔር የወርቅ ወንበር አዘጋጅቶ፣ የወርቅ መቀመጫዎች አዘጋጅቶ፣ የወርቅ ጫማዎችን አዘጋጅቶ መልካም አትክልት ቦታን እየጎበኙ መንግስተ ሰማያት ገብተው በኤደም ገነት ከሚፈሰው ውሃ እየጠጡ እየተዝናኑ ይኖራሉ ተብሎ ይታመናል፡፡

በማህበረሰቡም ህፃን ልጅም ይሁን ትልቅ ሰው ሲሞት የመቀበሪያ ቦታው ይለያይ እንጂ ያለቃቀስ ስርዓቱ አንድ ነው፡፡ ለህፃናት ሞት ሀዘን የሚገለጸው በጣም በለሁሳስ ድምፅ ቀስ ብሎ ነው፡፡

> *ይህ ስነ ስርዓት ከተከናወነ በኋላ ቀብር አስፈጻሚዎቹ ወደ መቃብር ስፍራው እንዲሄዱ ይደረጋል፡፡ በዚህ ሰዓትም ወላጅ እናት አብራ መሄድ አትችልም ምክንያቱም ጨቅላ ህፃኑ ሲቀበር አንጀቷ ስለማይችል ምርር ብላ ልታለቅስ ትችላለች፡፡ ስለዚህ አስክሬን ከወጣበት ቤት አንዲት ሴትና ሁለት ወንዶች በመሆን ቤቱን ስለሚጠብቁ እና ስለሚያፀዱ በዚህ ሰዓትም አብራ ያለችው ሴት የወር አበባ ያቆመች ካስ ወይም ቁርባን ያላት የሟችን እናት ፀጉሯን አዙራ ክብ በመስራት እና ከመቀመጫዋ ቀሚስ የህፃኑን ልብስ በመቅደድ ሰፍታ እያፅናናች ወንዶችም አብረው በማፅናናት ይጠባበቃሉ፡፡ ካስ ወይም ቁርባን ያገኙት ትልቅ ሴት ቀብረው ለሚመጡት ዳቦ ጋግራ፣ ወተት፣ ማር አዘጋጅታ ትጠብቃቸዋለች (ቃለ መጠይቅ፣ እማሆይ በተሃ ደመቀ 10/06/2011)፡፡*

## 4.4 የህጻናት የቀብር ጊዜ ክዋኔ (ጊዛ ግቬው)

የጨቅላ ህፃኑን የቀብር ስነ ስርዓት ቀባሪዎች ፈጽመው እንደመጡ የሟች እናት ከቀብሩ ቦታ ስለልሄደች የባለቤቷን አንገትና የቀባሪዎችን አንገት በመያዝ አልቅሳ እርሟን ታወጣለች፡፡ ከቀብር መልስ የተዘጋጀውን ምግብና መጠጥ የጨቅላው አስክሬን ከወጣበት አመናውን /መቋደሻውን/ ከመዘናው ቁስ ከቤቱ ጓሮ ከረጨና ዳቦውን ቆራርሶ ከጣለ በኋላ ለሀዘንተኞችና ለታዳሚዎች በመስጠት ይበላሉ፤ይጠጣሉ፡፡

ማር፣ ወተቱና ዳቦውን የህፃኑ ልጅነት በህፃንነቱ የመሞቱ ምሳሌ በመንግስተ ሰማይም የሚበሉትን፣ የሚጠጡትን ለማሳየት ነው፡፡ ከሟች እናት ቀሚስ በስተኋላ ላይ የህፃኑ ልብስ ተቀዶ ይሰፋል፡፡ የዚህ ተምሳሌት በድንጋጤ ልጇን ስላጣች መሀን እንዳትሆን መልሳ ልጅ እንድትወልድ /እንድትተካ/ ነው፡፡ የፀጉር ክብ አሰራሯ እናት ዘጠኝ ወር አርግዛ እንደወለደች ሲሞትባት/ስትሞትባት የራስ ህመምና የራስ ማዞርን፣ የማሰብን፣ የመጨነቅን የሚገልፅ ነው፡፡ ሌላው የጨቅላ ሀዘን ለማንም አይስጠው የሚል መልእክት አለው፡፡

በአጠቃላይ ለጨቅላ ህጻን ሞት ወደ ሌላ ሰው መልእክት አይላክም፡፡ ለማህበረሰቡ መልእክተኛ የሚሆነው የህፃኗ አባት ለሶስት ቀን ከቤት አለመውጣቱ እና የሟች እናት የፀጉር አሰራር

እንደሁም ከልብሷ በስተኋላ ላይ የተሰፋው ጨርቅ በራሱ መልእክተኛ ነው (የቡድን ተወያዮች 10/06/2011)።

ከመዘና ቂሶችም የሚችን እናት ደግመሽ ውለጅ ዓይንሽን በዓይንሽ እይ፤ ይደግልሽ ዳሪ ኳይ በድማ ወራሽ ያርግልሻ፣ የምታርሱት በሬ፣ የምታልቡት ላም ይስጣችሁ፤ እግዚአብሔር የዕድሜ ባለፀጋ ያድርጋችሁ በማለት ምርቃታቸውን ያከናውናሉ።

## 4.5 ለአዋቂዎች የሚደረግ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ

በክመንት ማህበረሰብ የሚደረጉ የለቅሶ ስርዓት የሚች ቤተሰቦች የቤታቸውን አቅም መሰረት ባደረገ ሚች በህይወት እያለ የሰበሰባቸው ሀብት፣ ንብረት እንዲሁም ለእዝን ተብሎ የተቀመጠ ከሆነ ወዲያውኑ ለሚች ከፍተኛ የሆነ ድግስ ይደገሳል። ግን ሚች በዚሁ ልክ ደግሞ የሌለው እና ዝቅተኛ ገቢ ያለው ከሆነ ዝግጅቱ አናሳ ይሆናል።

ሚች በህይወት እያለ ከማህበረሰቡ ጋር ቀረቤታና ግንኙነት ካልነበረው ቢታመምም ቢሞትም ገንዘብ እገዛም አይደረግለትም። የለቅሶ ስርዓቱ ግን ነብስ አንድ ስለሆነች እንደሁሉም ይከወናል።

የክመንት ሃይማኖት ተከታይ ሆነው የነበሩት ወደ ክርስትና ሃይማኖት የተቀየሩት ሲሞቱ ህግና ደንቡ የክመንት ሃይማኖት ተከታዮችን ገፅታ የተጎናጸፈ ነው። ምክንያቱም በሞት ሰዓት የአምልኮት ስርዓቱ እውነት ነው የሚያስብል ጉዳይ ያለው ነው (ቃለ መጠይቅ፣ እማሆይ አዛጉ አደመ 10/06/2011)።

በክመንት ማህበረሰብ የሞት ስርዓት ብዙውን ጊዜ በፀሎት ስነ ስርዓት ነው የሚከናወነው። አምልኮታቸውንም ብዙውን ጊዜ ሰውተው ከማቋደስ ጋር ያያይዛሉ። ብዙ ጊዜ አይለቀስም የታመመው ሰው ነብሱ ሲወጣ፣ ከኖረበት ቤት አስክሬኑ ሲወጣ እና ግብዓተ መሬት ሲሆን ብቻ ነው።

እኔ የተመለከትኩት ቀደም ብየ ከጥናቱ ዳራ ላይ እንደገለጽኩት ቁርባን /ካስ/ ያገኙ የእማሆይ አዋጋሽ አበራን የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ነው። ቀጥዬ ቅድመ ሞት፣ ጊዜ ሞት፣ ቅድመ ቀብር፣ ጊዜ ቀብር እና ድህረ ቀብር የታዩትን ክዋኔዎች እተነትናለሁ።

### 4.5.1 ቅድመ ሞት ክዋኔ (ክዳም ሼው)

በክመንት ማህበረሰብ አንድ ሰው ሲታመም በመጀመሪያ በባህላዊ መድሃኒት ብዙ ጥረት ይደረጋል፡፡ የአካባቢው ሰዎችም የታመመውን ሰው እየተመላለሱ ይጠይቃሉ፡፡ ሁሉም በየራሳቸው ለታማሚው የመሰላቸውን የተለያየ መፍትሄ የባህል መድኃኒት እንዲሰጠው ይጠቁማሉ፡፡ በሽታው ዓይነት የታማሚው ቤተሰቦችም "አዎ እገሌ" ያለውን መድኃኒት እንጥመቀው፣ እንተኩሰው፣ እንጠነው፣ እንቀበለው፣ እናጠጣው፣ እናሳስረው እያሉ ከተወያዩ በኋላ ለበሽታው የሚሆነውን ባህላዊ መድኃኒት ያደርጋሉ፡፡ አቶ ብርሃኑ አወቀ ነገሩን እንደሚከተለው ያብራሩታል

> *ሰው ሲታመም በቅድሚያ የሚደረገው ባህላዊ መድኃኒት ነው እንጂ ዘመናዊ የህክምና መድኃኒት በአብዛኛው አይሰጥም፡፡ ምክንያቱም የዘመናዊ የህክምና መድኃኒት የሚቀመመው ከተፈጥሮ እፅዋት ስለሆነ እኛም የተፈጥሮን እፅዋት ነው እኛም ለመድኃኒትነት የምንጠቀመው ያው የተፈጥሮ እንስሳት ነው፡፡ ከቀንድ ከብቶች ወይም ከቤት እንስሳዎችም ነው፡፡ ከዱር አውሬዎችም ባህላዊ መድኃኒት ይሰራል፡፡ የታመመው ሰው እንደ አጋጣሚ ሆኖ ከሞት አፋፍ የደረሰው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ ይድናል፡፡ ከሞተ ደግሞ ከእግዚአብሔር በታች በእሱ እፅዋት ለፍተናል ደክመናል "እሱ ሰራው፤ እሱ ወሰደው" አደራን እግዚአብሔርን አንጋፋም በማለት (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ብርሃኑ አወቀ 04/06/2011)፡፡*

አንድ ሰው በጠና ከታመመ ነብሱ ለመውጣት ሲጣጣር በአስቸኳይ በደቦ ጤፍ ተበጥሮ ይፈጫል፡፡ በርበሬ ለአዋዜ ይፈጫል፡፡ ለእንግዳ መቀበያ ዳስ ይሰራል፣ አካባቢው ይጸዳል፣ እንጨት ይፈለጣል፣ ውሃ በደቦ ወጣቶች ተሰባስበው ሩቅ ቦታ ከምንጭ ቀድተው ያመጣሉ፡፡ ከዚህ ክንውን በኋላ የታመመው ሰው ያለበትን ሁኔታ በማየት የኑዛዜ ስርዓት ይካሄዳል፡፡ የንስሀ አባት የሚኖረው ቄስ የሆነ ሳይሆን የታንቲ ዘር እንዲሆን ተቆጥሮ ነው፡፡ ዝምድናውም እስከ ሰባት ትውልድ በመቁጠር እስከ አስራ አምስተኛው ትውልድ ባለው ነው፡፡

የንስሀ አባቱ የኑዛዜውን ስርዓት ሲጀምሩ "የክመንት ልጅ" ይላሉ በምድር ላይ ሲኖር የሰው አደራ የማይበላ፣ የማይዋሽ፣ የሰው ሚስት የማይደፍር፣ በቃሉ የሚጸና ታማኝ ነው ይላሉ፡፡ የንስሀ አባቱም የታመመውን ሰው ሲያናዝዙ ትልልቅ ልጆች ቁጭ ብለው ይሰማሉ፡፡

ተናዛዡም አባታችን አደረይኪ የተናገረው ቃል የሰው ገንዘብ ወድቆ ካገኛችሁ ከሃብት ንብረታችሁ ሳትቀላቀሉ የገንዘቡ ባለቤት እስኪመጣ ጣራ ላይ አስቀምጣችሁ በማቆየት ለባለቤቱ መልስ" ያለውን ቃል አክብሬአለሁ በማለት ለንስሀ አባታቸው ይገልፃሉ፡፡ ቀጥለውም "በሉ እንግዲህ አባ ልጆቼ እንዳይጣሉ ያለውን ገንዘብ ሲካፈሉ አብረው ከልጆቼ ጎን እንዲቆሙ" በማለት ይገልጻሉ፡፡ የንስሀ አባትም ልጂ ቃሉን ሰምቻለሁ አንተ ደህና ሁን በማለት ይጨርሳሉ፡፡

ተናዛዡ እኔ ጥሪ መጥቶብኛል ስሞት ሙት ዓመት አድርጉልኝ የተረፈውን ሀብት ንብረትም በፍቅር በሰላም በአንድነት በመተሳሰብ ተካፈሉ ለንስሀ አባቴም ተናግሬያለሁ "ከተጣላችሁ አጥንቼ እሾህ ሆኖ ይውጋችሁ" በማለት ይናዘዛሉ፡፡

ይህን የሰሙ የተናዛዥ ልጆችም በሰዓቱ ዓምነው በመቀበል የአባታቸውን ጉልበት ይስማሉ፡፡ ልጆቼ "ከምንም በላይ ፍቅር ነው፤ ፍቅር ይስጣችሁ" በማለት ይጨርሳሉ፡፡ የንስሀ አባትም በሰዓቱ ይህን በመስማት ለልጆችም ለተናዛዡም የምርቃት ስነ ስርዓት ያደርጋሉ፡፡ የምርቃት ስነ ስርዓቱም እንደሚከተለው ነው፡፡

"የቅጠሉን ያህል ሲሳይ የአውራ ጎዳናውን የሚያክል መንገድ ይስጣችሁ" "መልካችሁ የማይጠይም ይሁን አልጋችሁ የማይሰበር ይሁን" በማለት ይመርቃሉ (የቡድን ተወያዮች 6/06/2011)

በዚህ ምርቃት ሲሳይ ከዛፍ ቅጠል ጋር ተመሳስሎ መቅረቡ ቅጠልን ያክል የበዛና የተትረፈረፈ ሀብት ንብረት የሚያመለክተው ከመንገድ ጋር ተወዳድሮ ቀርቧል፡፡ "መልካችሁ የማይጠም ይሁን አልጋችሁ የማይሰበር ይሁን የሚለው ምርቃት ደግሞ የመልክ መጥመም ቀጥታ መከፋትን፣ ማዘንን፣ ከመተከዝን ያመለክታል፡፡ "አልጋ መሰበር" ደግሞ ከሚስት ወይም ከባል መሞት ጋር የተያያዘ ነው፡፡

ከዚህ በኋላ የንስሀ አባትም በቃላቸው የደገሙበት የንስሀ ጸበል ታማሚውንም ቤቱንም ረጭተው ወደቤታቸው በመሄድና በመምጣት ታማሚውን ይጠይቃሉ፤ ከታማሚ ጎንም ትልልቅ አዛውንት ሰዎች እንዲቀመጡ ያደርጋል፡፡ የታማሚውን ዓይን ዓይን በማየት ዓይናቸው እንባ እያቀረረ የልብ ሀዘን እየተሰማቸው ይጠባበቃሉ፡፡ እነዚህ ጠባቂዎች ታማሚው ነብሱ ሲያልፍ "ያፈሰሰውን ልጋግ ጠራጊዎች" ይባላሉ፡፡ ሟች ከቤት እስኪወጣ ይጠብቃሉ፤ አስክሬኑ ከቤት ከወጣ በኋላም ቤት ጠባቂዎች ናቸው፡፡ ሦስቱ አስታማሚዎችም ከቤት ሲቀሩ ወጣቱ አስክሬኑ የወጣበትን ቤት ይጠራርጋል፤ አልጋውን ያስተካክላል፡፡ ሁለቱ ደግሞ የንስሀ

አባት የቃል ጸሎት ያደረሰበትን ጸበል ቤቱን፣ ጓሮውን ይረጫሉ (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ እንዳሻው ጠጋው 18/06/2011)።

በክመንት (በህገ ልቦና) እምነት መሰረት “ሰው የተሰራው ከጭቃ ነው፣ ስንሞት ወደዛው ነን” ስለዚህ “ሳጥን አያስፈልግም” ለቃሬዛ /ለአጎበር/ የሚሆን ከድግናው /ከዲቢቱ ውስጥ አዛ ወይም ብሳና፣ ጠንበለል (ተንበለል)፣ ሰንኪሳር ወይም ቀረጥ፣ ገተም ከሚባሉ ቀጫጭን እንጨቶች ቆርጠው ካመጡ በኋላ ከጠፍር አልጋ በተሰራው ከአራቱ መዓዘን ቀዳዳ እነዚህን ቀጫጭን እንጨቶች በመሰካት አያይዘው አጎበሩን/ ቃሬዛውን/ ይወጥራሉ። ይህ ቃሬዛ ወይም አጎበር ከህፃናት ውጭ ለሁሉም ይዘጋጃል። የሚችን የለቅሶ ስነ ስርዓት ከተመለከትኩ በኋላ አስክሬኑን ተሸክመው ወደ ድግና ቦታው የወሰዱት ቀብር ፈፃሚም ራሳቸው መሆናቸውን ተመልክቻለሁ።

## 4.5.2 ጊዜ ሞት /ጊዛ ሼው/

ጠባቂዎች የታማሚውን ነብስ ማለፏን ሲያውቁ ወዲያውኑ ወጣቱ መጋረጃ ይጋርዳል፤ ሁለቱ አዛውንቶች “ካስ” ያላቸው ስለሆኑ “ልጋጉን” ይጠራርጋሉ። ወጣቱ ለቤተሰቦች የሚችን ነብስ መውጣት ያረዳል። ቤተሰቡም በድንጋጤ በማልቀስ ለጎረቤት ያሰማሉ።

በሚች እማሆይ አዋጋሽ አበራ ለቅሶ ላይ ተገኝቼ ለአስክሬን መከፈኛ አቡጀዲውንና ሰሌኑን የፀሎት ስነ ስርዓት ሲያደርጉበት ተመልክቻለሁ።



**ፎቶ 3፡- ለአስክሬኑ መከፈኛ የሚሆኑ ቁሳቁሶች ላይ ፀሎት ሲያደርጉ (ፎቶ በአጥኚዋ)**

አስክሬን የሚታጠበው በብሳና ቅጠል ሲሆን፤ አስክሬን ከመታጠቡ በፊት ሦስት ገናዥች ሚች መሞቱን ሲገነዘቡ ውሃ አምጥተው ድፍን የነበረውን “ቅል” ቆርጠው ፍሬውን ካወጡ በኋላ የብሳናውን ቅጠል ውሃ ይዘፈዝፋሉ። የተዘፈዘፈውን ብሳና ቅጠል “ከመዘናው” ወይም አጋዥ

ቁሱ "ኪ-ኪ-ኪ ኪዱስ" በማለት ሲጀምሩት አንደኛው "ካስ" ቁርባን ያገኘው እና ወጣቱ አብረው አንድ ላይ በመሆን  አስክሬኑን ሶስት ጊዜ ደጋግመው ያጥቡታል፡፡

የብሳና ቅጠል ለክመንት ማህበረሰብ ቅዳሴ መቀደሻ፣ አመና መቋደሻ መጣያ፣ ለተዝካር አቆልቋይ /የምግብ ማቅረቢያ/፣ ለጠላ መጥመቂያ የሚውል ብቅል መደብደቢያ /መርገጫ/ ከቀብር በኂላ ለነብስ ይማር እንጀራ ለአልቃሽ ማቅረቢያ ይገልጹበታል፡፡

በተጨማሪም ሰው በአጋንንት በሽታ፣ በልክፍት በሽታ፣ በመብረቅ ከተመታ ከብሳናው ዛፍ ሦስት ጊዜ ከቀኝ ወደ ግራ በማዞር ከበሽታው መፈወሻ ይሆናል፡፡ የወለደች ላም ልጇን አላጠባም ስትል የብሳናውን ልጣጭ ከጭራዋ ሲያስሩት ወዲያውኑ ልጇን ታጠባለች፣ ትታለባለች ከያዛት ልክፍት በሽታም ትድናለች፡፡ አስክሬኑ በብሳና ቅጠል የሚታጠበው ከቀብር ስነ ስርዓት በኂላ ከመቃብር ቦታ ሰይጣን /አጋንንት/ እንዳይደርስ የሚደረግ መከላከያ ነው፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ሲሳይ ጣው 18/06/2011)፡፡

የገናገኖች ሦስት መሆን እነዚህን የለቅሶ ደረጃዎች ለማሳየት ነው (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ እንደሻው ጠጋው 15/06/2011)፡፡

ከዚህ ውጪ በክመንት ማህበረሰብ የበላይ የሆነው ወንበር ሲገነዝ በሁሉም ተመሳሳይ ሆኖ የሚለይበት ግን በግራ እጁ ፊቱን ይሸፍናል በቀኝ እጁ ደግሞ ብልቱን ይሸፍናል፡፡ ይህም አደራን /እግዚአብሔርን/ ይሁዳ ፊቱን ሸፍነው ምራቅ እየተፉ በጥፊ የመቱትን የሚወክል ነው፡፡

የአከፋፈን ስርዓቱም በመጀመሪያ ከበሬ ቆዳ በተሰራ ነጭ /ቀይ/ ጀንዴ አስክሬኑ ይጠቀለላል፡፡ ይህ መጠቅለያ ጀንዴ ሟች ለብዙ ጊዜ ተኝተውበት ላባቸውን ሲጠጣ የቆየና የለሰለሰ በመሆኑ ነው፡፡  በመቀጠልም ለከፈን የተዘጋጀውን በቁመቱ ልክ የተሰፋው ከአቡጀዴ ጨርቅ ውስጥ ይከቱታል፡፡ በተጨማሪም በሰው እጅ በተሰራ ነጭ ሰሌን ተጠቅልሎ አስክሬኑ ከሰባት ቦታ ይታሰራል፡፡



**ፎቶ 4፡- ገናዦች አስክሬኑን በአቡጀዴ ውስጥ ከተው በሰሌን ሲጠቀልሉት (ፎቶ በአጥኚዋ)**

የአቡጀዴ ተምሳሌት በክመንት ማህበረሰብ ሰው ሲሞት ነፍሱን ተቀብለው ተንከባክበው የሚወስዱት መላእክት ነጭ ለብሰውና ተጎናፅፈው ነው ተብሎ ስለሚታመን ይህን የመላእክት አለባበስ ለመመሰል ነው፡፡ ሌላው የጀንዴው ውክልና ለታመመው ሰው ለቅዝቃዜ፣ ለሚያስጮህ፣ ለዓይነ ጥላ (ለአይነ ቁራኛ) ለተላላፊ በሽታ፣ ለዛር ቡዳ፣ ለሰው ውለት… የመሳሰሉትን የሚያድን ነው፡፡ ጀንዴው ለዚህ አገልግሎት የሚውለው ከብዙ ዓመታት በኋላ የመቃብሩን ድንጋይ ድንጋይ አንስተው አስተካክለው አትክልት ለመትከል ሲፈልጉ ቆዳውንም አውጥተው ጥቅም ላይ ያውሉታል፡፡

ሰሌኑ "ካስ" የቆረበ ሰውን የሚገልጽ ሲሆን ሁሉን ነገር ትቶ ዓይኑ መጥፎ በማየት፣ ጆሮው ክፉ ከመስማት፣ ልቡ ክፉ ከማሰብ፣ እጁን የሰበሰበ …. ሁሉን ነገር ወደ ኋላ ትቶ ካስ ወይም ቁርባን ያገኘ ሰው ቀጥታ ነብሲቱ በገነት እንደዘንባባ ለምልማና ሰፍታ ትኖራለች የሚል ትርጓሜ ይሰጡታል፡፡ አስክሬኑም ከተከፈነ በኋላ በውል ክፉ ልጥ (ዳንጉራ) በሚባለው ሰባት ቦታ የሚታሰረው በህገ ልቦና ህግ ፀንቶ የኖረ መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡

ሰባት ቦታ የታሰረው እና ሰባት ቦታ ያረፈው ምሳሌ አደረይኪ የተተራንዛን ደምሽ ሰባት ዓመት ይንጠፍጠፍ ሲላት መልሳ ሰባት ቀን ስትለው እንዳልሽው ይሁን ማለቱን የሚገልጽ ነው፡፡ ሌላው እናት ልጅ ወልዳ በሰባተኛው ቀን የአንገት ማተብ፣ ቁርባን፣ ግርዛት ማስደረጓን፣ የሚያመለክት ነው፡፡ በሰባተኛው ወር የተወለደ ልጅ እንደሚያድግ በስምንተኛው ወር የተወለደ እንደሚሞት ነው፡፡  በዚህ መልኩ አስክሬኑ ሰባት ቦታ መታሰሩን በህገ ልቦና ማህበረሰብ ይህንን ውክልና ያሳያል፡፡



**ፎቶ 5፡- አስክሬኑ ከተከፈነ በኋላ ሰባት ቦታ ታስሮ (ፎቶ በአጥኚዋ)**

ይህ አከፋፈን /ግበርግበር/ ግን ለሁሉም አይደለም ለምሳሌ ህፃናት በሚሞቱበት ጊዜ ግንዛቱ አንድ ሲሆን የአከፋፈን ስርዓቱ ግን ህፃናት በአቡጀዴ ብቻ ይከፈናሉ፡፡ ምክንያቱም እንደተወለዱ ምንም ነገር ሳይሰሩ መሞታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቡጀዴውና ሰሌኑ ደግሞ ካስ /ቁርባን/ ላገኙ ሰዎች ብቻ የሚካሄድ ስነ ስርዓት ሲሆን ይህም የሚያሳየው ከመሞት ወደ ድህነት ስለተለወጡ ወይም ከኃጢያት መስራት ወደ ድህነት የመመለሳቸውን ሁኔታ የሚገልጽ ነው (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ እንደሻው ጠጋው 15/06/2011)፡፡

የሚች አዋጋሽ አበራን የአስክሬን ግንዛት "ሸውኖ" እና የአስተጣጠብ "ሻሸኖ" ስርዓተ ክዋኔውን የተከለከልኩበት ምክንያት የአስክሬን እርቃን ከከፋኞች ውጪ ሌላ ሰው መመልከት ስለማይችል ነው፡፡  የሚች አስከሬን በቅደም ተከተል ሲከፈን አቡጀዲውን፣ ጀንዴውን፣ ሰሌሉን ካደረጉ በኋላ ከጥጥ የተሰራ ጋቢና ዥንጉርጉር ቀይ የበዛበት የአልጋ ልብስ አልብሰው ከአልጋው የነበረውን አስክሬን ከቤቱ ወለል አውርደው የቆየ ደረቅ ሳር ብቻ ነስነስ አድርገው አስተኝተው በወይራ ቅጠል፣ በጡንጁት ቅጠል፣ በክትክታ ቅጠል አንድ ላይ በማድረግ እያጠኑ የፀሎት ስነ ስርዓት አካሄዱ፡፡



**ፎቶ 6፡- የሟች አስክሬን ከመኖሪያ ቤታቸው ወለል ላይ ሆኖ እጣን እየታጠነ ፍትሃት ሲደረግ**

ከክንውኑ በኂላ አቶ እንዳሻው ጠጋውን ስጠይቀው የቀብር ስርዓተ ክንውኑ ዛሬ ነው፡፡ ምክንያቱም በ16/01/2011 ከለሊቱ 10፡00 ሰዓት ነብሷ ከስጋዋ ስትለያ በሩቅ ላለው ቤተዘመድ በሙሉ ስልክ በመደወል ስለነገርን ዛሬ በ17/06/2011 የቀብር ስነ ስርዓቱ ይፈፀማል፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ እንዳሻው ጠጋው 17/06/2011/፡፡

ሟች አዋጋሽ አበራ ከኖሩበት፣ የልጅ ልጅ ካዩበት ቤት ሲወጡ፤ ሁሉም በመጠባበቅ ላይ የነበረው አልቃሽ ከፍያለ የጩኸት ድምጽ በማሰማት የሀዘን ስሜታቸውን ገለጹ፡፡ አስክሬኑም ከቤት ከወጣ በኂላ 5፡00 እስከ 5፡30 የሟች ልጆች፣ እህቶች፣ አክስቶች ቀይ ጥለት የበዛበት ካባ፣ የተጠለፈ ባህላዊ ቀሚስ እና የተለያዩ ጌጣጌጦችን በመልበስና በመያዝ ሴቶች ብቻ ክብ ሰርተው የለቅሶ ሀሰዘናቸውን ሲገልጹ ተመልክቻለሁ፡፡

የሟች ወንድ ልጆች ደግሞ ዋንጫውን በሻሽ ጨርቅ ሸፍነው በመያዝ ወንዶችንም ሴቶችንም በሰልፍ ትከሻቸውን በመንካት ሲያለቅሱ ተመልክቻለሁ፡፡

ከድህረ ቀብር በኂላ ያለው ስርዓት የቀበረው ቤተ ዘመድ በሙሉ ከቤት እንደተመለሱ ያልሸና ወይፈን (በግ) መስዋዕት ተደርጎ ጎረቤቱ እንጀራ (ጠላ) እያመጡ እስከ ሶስቱ ቀን ሀዘንተኞችን ያጽናናሉ የንስሀ አባት፣ "ኪዱስ ምዝቫናውንቫን" ወይም ይድረስ ለእግዚአብሔር ምስጋና በማለት የቃል ፀሎት ያደርሳሉ፡፡

ለሟች የፍትሃት ስርዓት ሲደረግ ነጭ ጤፍ ከአገልግል ውስጥ ተደርጎ ማር ብርዝ እና ወተት በብርሌ ውስጥ ተደርጎ፤ ከአገልግሉ ጤፍ ላይ ብርሌው ይቀመጣል፡፡ አስክሬኑ ከቤት ከመውጣቱ በፊት የሟች ስም ሰባት ጊዜ እየተጠራ ፍትሃት ይደረጋል፡፡ ፍትሀቱም እንዲህ

*ሰባት ጊዜ* *"ሣጎቶንማን ሸቢው ናንድ*

*ሰባት ጊዜ* *ቊንምንፋን ቶንማ*

*ሰባት ጊዜ* *ከምኵም ጋለቲውዛ*

የሚል ነው፡፡

ይህም እግዚአብሔር ማርልን ማርልን የመጣውን ነብስ ተቀብለህ ማርልን አትውቀስብን ወደ ገነት አስገባልን፣ ሰርተኸናል፣ ፈጥረኸናል ለሌላ አሳልፈህ እንዳትሰጠን በማለት የፍትሃቱ ስነ ስርዓት ይከናወናል፡፡ አስክሬኑም ከስነ ስርዓቱ ጥንቅር በኋላ ከወለል የነበረው አስክሬን ከተዘጋጀው ቃሬዛ ውስጥ ገብቶ ከተቀመጠ በኋላ የተለያዩ ዝግጅቶች በማከናወን እና ዘመዱ እስኪመጣ ይጠባበቃሉ፡፡

በክመንት ሃይማኖት አንድ ሰው በሞት ሲለይ ማዋል ማሳደር አይፈቀድም፡፡ ነገር ግን የሃይማኖቱ ግዴታ የሆነ ስነ ስርዓት አላቸው፡፡ ግዴታውም ሙሉ ቀናቶች በሚባሉ ለምሳሌ ቅዳሜ ነብሱ ከወጣ እሁድ መቀበር አለበት፣ ሰኞ ነብሱ ከወጣ ማክሰኞ መቀበር አለበት፡፡ ሌላው ረቡዕ ነብሱ ከወጣ ሀሙስ መቀበር አለበት፡፡ እነዚህ ቀናቶች ለክመንት ማህበረሰብ ሙሉ ቀናት የተቀደሱ ቀናቶች ተብለው እና መንግስተ ሰማያት ያስገባሉ ተብለው የሚታመኑ ናቸው፡፡

### 4.5.3 ቅድመ ቀብር ክዋኔ /ደቬው ሰኟቬው/

አቶ እንደሻው ጠጋው ሟች በሕይወት እያሉ ማህበራዊ ጉዳይ ላይ ተግባቦት እንዳላቸው እና ግቡ፣ ብሉ፣ ጠጡ ባይ መሆናቸውን ገልጸውልኛል፡፡ ማህበረሰቡም የሟችን ሁኔታ በማስታወስ ለለቀስተኛው የሚሆን የሚበላ የሚጠጣ ምግብ አዘጋጅተው ያመጣሉ፣ ለሟች ቤተሰብም የስራ እገዛ ያደርጋሉ (18/06/2011)፡፡

ከቀብር በፊት የሚዘጋጁ ቅድመ ሁኔታዎች የምግብና የመጠጥ ዝግጅቶች፣ ለቅሶ የሚያረዱ ማመቻቸት፣ አካባቢውን የሚያጸዱ እና ለለቀስተኛው ዳስ የሚያዘጋጁ /የሚሰሩ/፣ ለመቅበሪያ

ቤት ጉድጓድ ማዘጋጀት፣ አስክሬን ተሸካሚ ማዘጋጀት፣ አልባሳትና ቁሳቁሶችን ማስተካከል መሆናቸውን የቡድን ተወያዮች ገልጸዋል 18/06/2011)፡፡

በሟች ቤተሰብም ለሚመጣው ቀባሪ እንጀራ በደቦ ይጋገራል፣ "ካስ" /ቁርባን ባላት ሴት ቀይ አዋዜ ይዘጋጃል፣ የሚጠጣ ለስለስ ያለ ከገብስ ብቻ የሚዘጋጅ ኮረፌ፣ ጠላ፣ ሽምብራ ይቀቀላል፣ በግ ይሰዋል ወይም ይታረዳል፡፡ እነዚህ በመጠኑ ከተዘጋጁ በኋላ ለቀባሪዎች የሚቀርቡ ናቸው፡፡



## ፎቶ 7፡-ለሀዘንተኛው የተዘጋጀ እንጀራ እና አዋዜ

ለቅሶ የሚያረዱ ወይም ነጋሪዎች ሁለት ጤነኛ ወጣቶች ከተመረጡ በኋላ የሟች ቤተሰቦች ለነጋሪዎች የት አካባቢ መሄድና መናገር እንዳለባቸው በዝርዝር ይነገራቸዋል፡፡ ከአያ እገሌ እያሉ ዘር በመቁጠር /ዝምድና/ በመቁጠር ከለቅሶው መቅረት የሌለባቸው ቁርጠኛ ዘመዶች የቀብሩ ስነ ስርዓት መቼ እንደሚከወን ነጋሪዎች የሄዱበትን አካባቢ ሰው እርስ በራሱ ስልክ ካለም እየተደዋወሉ እንዲናገሩ በማድረግ ወደ መንደራቸው ውለው ይመለሳሉ (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ሲሳይ ጣው 18/06/2011)፡፡

በቀብሩ ቀን በተለያየ አቅጣጫ የመጣው ቤተዘመድ እንደ አዘገጃጀቱ ዓይነት ከመቃብር ቦታው የምግብ ስነ ስርዓቱ ይካሄዳል፡፡ ሰው ያለበት ቦታ የራቀና ከቀብር ቦታው በትኩሱ መድረስ ካልቻለ በሰልስቱ ስነ ስርዓት የግድ መገኘት አለበት፡፡ በዚህ ሰዓትም ለማስተዛዘኛ ይዞት የመጣው ከአምስት ብር እስከ አስር ብር ስሙ እየተፃፈ ይሰጣል፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት በዋናው የለቅሶ ስነ ስርዓት ቀን የሟች ቤተሰብን አለመምጣቱ እንዲታወቅ ነው፡፡ በለቅሶ ስነ ስርዓቱ ቀን የሟች ቤተሰብን ትከሻ በእጅ መንካት አይቀሬ ነው፡፡ ይህም መምጣቱን

ለማመላከት ሲሆን ሀዘንተኞች ማን መጣ፣ ማን ቀረ ብለው በጥብቅ የዓይን ቁጥጥር ስለሚያደርጉ ነው፡፡

**የአስክሬን መሄጃውን መንገድ ማፅዳት፡-** የአስክሬን መሄጃው ቦታ ከመንደር በጣም ርቀት ስላለው እንዲሁም ዳገት ስላለው ጉልበት ያላቸው ወጣቶች ተመርጠው ሀረግና የተለያዩ እንጨቶችን ይመነጥራሉ፡፡ በመንገድ ያለውን ድንጋይ ይለቃቅማሉ፤ ያነሳሳሉ፡፡ ተመልሰው ቀደም ተብሎ እንደተገለጸው በተሰራው ዳስ ውስጥ የብሳና ቅጠል ቆራርጠው ይጎዘጉዛሉ፣ ለሀዘንተኛው እና ለሚመጣው የቅርብ ዘመድ በጎረቤት ቤት እየዞሩ ወንበር በማምጣት ያስቀምጣሉ ያዘጋጃሉ፡፡

**የሩቅ ቤተ ዘመድ፡-** ለለቅሶው የሚመጡት ቤተዘመድ ወንዶች ቀኝ እጃቸውን ከጋቢያቸው በላይ በማውጣት ጥሩምባ እየነፉ ቁርጠኛ ዘመድ መሆናቸውን ይገልፃሉ፡፡ የሴት ዘመዶችም እንዲሁ ቀይ ጥለት ያለው ካባ ወይም "ሽመነብስ ሼይን" እና ነጠላቸውን ከወገባቸው አዙረው በወፍራሙ ይታጠቃሉ፡፡ ይህም ቁርጠኛ ዘመድ መሆናቸውን ለመግለጽ ነው፡፡

**የጉድጓድ አቆፋፈር ስነ ስርዓት፡-** የከመዘናው ቁስ የሚችን ቤተሰቦች በመያዝ ወደ ድግናው ቦታ ልዩ ስሙም "እንኩርድባ" ይባላል ትርጉሙ ተራራ የሚል ሲሆን ከመዘናው ቁስም ወደዚህ ቦታ በመሄድ የመቃብር ቦታውን ይባርክላቸዋል፡፡ በመቀጠልም ጉድጓድ የሚቆፍሩት ሰባት ቤተ ዘመድ ወጣቶች ከመረጡ በኂላ ከሚች ቤት አዷማ፣ አንካሴ፣ ምሳር፣ አካፋ፣ ማጭድ የመሳሰሉትን ቁሳቁሶች እያንዳንዳቸው በየግላቸው ሳይደራረቡ አንድ አንድ በመያዝ ወደ ድግና ቦታው ያመራሉ፡፡

ቁሳቁሱን በየግላቸው የያዙት መልእክት ሞት በአካባቢው ተደራርቦ እንዳይመጣ የሚል ነው፡፡ የጉድጓዱ የአቆፋፈር ስርዓትም ከመዘናው ቁስ ከምዕራብ ወደ ምስራቅ እንዲቆፍሩ ያሳያቸዋል፡፡ ቆፋሪዎችም ብዙ ጫካ ቆራርጠውና መንጥረው ድንጋይ ለቃቅመው ካዘጋጁ በኂላ ይቆፍራሉ፡፡ ጉድጓዱን እንደጨረሱ በጠፍጣፋ ድንጋይ "ምርግብ" ሰርተው ያጠናቅቃሉ፡፡ ምርግብ የሚሰሩበት ምክንያት በክመንት ማህበረሰብ የእንጨት ሳጥን ማዘጋጀት በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡ እንደተመለከትኩት ሚች እማሆይ አዋጋሽ አበራ በዚህ መልኩ ነው የተዘጋጀላቸው፡፡ /የቡድን ተወያዮች፣ 18/06/2011/፡፡

ጉድጓዱ ከምዕራብ ወደ ምስራቅ የሚቆፈረው ሚች በህይወት እያለ ሲተኛም በዚህ መልኩ ነው፤ ሲፀልይም ወደ ምስራቅ ፊታቸውን በማዞር ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር የሚመጣው በምፅአት ጊዜ በምስራቅ በኩል ነው ተብሎ ይገመታል፡፡

### 4.5.4 የቀብር ጊዜ /ጊዛ ሼው/

አስክሬኑ ወደ መቃብር ቦታው ሲሄድ ቁርባን ያላቸው አራት ሰዎች ተሸክመውት በወንበሩ፣ በከመዘና ቁሶች ታጅቦ ነው፡፡ ፍትሀት የተደረገበትን ጤፍና በብርሌ የተሞላውን ማር ብርዝና ወተት ቆራቢ ሴት በአገልግል ተሸክማ አስክሬኑን ጎን ለጎን እያጀቡ ይሄዳሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ አስክሬኑን ሳይጠጉ ራቅ ብለው በመከተል ሀዘንተኞችን እያጽናኑ ረጅሙን መንገድ ይጓዛሉ፡፡

የማርና የወተት ሚስጥር ነፍሲቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትሄድ ማርና ወተት ከሚፈሰው ከኤዶም ገነት ያስቀምጠው፣ የዘላለም ህይወት ያግኝ፣ ህብስተ መና ይመግበው የሚል መልእክት አለው፡፡ ሌላው ከሞተው ሰው ቤት ማርና ወተት የማይለየው ሀብታም መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡

የአገልግሉ ውክልና ደግሞ “የተተራንዛን” ወይም እመቤታችንን የሚገልጽ ነው፡፡ የጤፉ ውክልና ደግሞ የአደረይኪ ተላላኪዎች ጀከረንታው፤ ግርግሊዩ እንደ ጤፍ በዝተው ነፍሲቱን በቀኝም በግራም በክንፋቸው አጎናፅፈው ከእግዚአብሔር ደጅ እንዲያደርሱ የሚያደርግ መልዕክት አለው፡፡

የሟች አስክሬን ከኖረበት ቤት ወጥቶ ከቤቱ በር ፊት ለፊት ሲያርፍ የሚከተለው ቃል ግጥም ተደረደረ፡፡

ሀ. አዋጋሽ አበራ ቤትሽ ይሰናዳ
ሳይበላ ወጣልሽ የመጣው እንግዳ

ለ. የላሞችሽ ጌታ የበሮችሽ ጌታ
ወዴት ወረድ ወረድ የመሬት መኘታ

ሐ. እንኳን አበላሽው እንኳን አጠጣሽው አልሽው ግባ ግባ
መፈታቱ አይቀርም ቤትና ገበያ፡፡

መ. ሀዘናችሁ ገና እኔ ልንገራችሁ
ወልዳችሁ ስተኙ ማነው ሚያርሳችሁ፡፡

/የሟች ወንድም እንግዳው አበራ እና ወ/ሮ ገቢያነሽ አራጋው 17/06/2011/

ሙሾው አስክሬኑ ከቤት እንደወጣ ለማህበረሰቡ የሆድን ትዝታ የሚቀሰቅስ የሚያባብስ ነው፡፡ ሟች በህይወት እያለች ሁልጊዜም ቤቷ የሞላ የተትረፈረፈና ያላት መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡ “ሳይበላ ወጣልሽ የመጣው እንግዳ” ሟችን ብሎ የመጣ ሁል ጊዜም ቢሆን በልቶ ስቆ ተዝናንቶ እና የራበው የጠማው ቋጥሮና ይዞ ወደ ቤቱ እንደሚሄድ ነው፡፡ የበላ የጠጣ ሰው የሟችን ቤት እየተመለከተ የሆዱን ብሶት በእንባ የሚገልፅበትን ያሳያል፡፡ ከሟች ቤት ሁልጊዜም የሚመጣው፣ ዘመድ፣ ጎረቤት፣ ብሉ ጠጡ ተብለው ሲዘረጋ የነበረው እጅ ተሰብስቦ ሲያገኘው በእንግዳው ላይ የሆድ ብሶትን ያጭራል፡፡

በእነዚህ ስንኞች ሟችን በህይወት እንዳለች እና ተነስታ መልስ እንድትሰጥ አድርጎ በመጥራት እና የመጣውን እንግዳ እንደምታወራ ተደርጎ ተገልጿል፡፡ ስንኞቹ አልቃሽ በሟች ሀዘን ምርር ብሎ እንባውን እንዲያፈስ እና እንዲጮህ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ሟች በህይወት እያሉ ይለፍ የተባለ ሙያ እንዳላቸው እና አዋቂ፣ ጥበበኛ፣ መለኛ ሴት መሆናቸውን ይመለከታሉ፡፡

በ “ለ” ስር ያሉትን ስንኞች ስንመለከት ሟች በህይወት እያሉ ችግርን የማያውቁ፣ የሞላላቸው፣ የደላቸው፣ ሙሉ መሬት ያላቸው በበሬ አሳርሰው፣ ከአውድማ አሳፍሰው ጎተራ ሞልተው ያላቸው መሆናቸውን ያንፀባርቃሉ፡፡ “የመሬት መኘታ” የሚለው የስንኝ ሀረግ ደግሞ ሟችን ቤተሰብ አይቶ ሳይጠግባት ዓለም በቃኝ ብላ “እንቅልፍ መተኛቷን” የዚህን አለም ኑሮ እንደጠላች፣ መሞትን የፈለገች መምሰሉን የሚያሳይ ነው፡፡

“ሐ”ን በምንመለከትበት ጊዜ ሙሾ አቅራቢ ሟችን ሲገልፅ ሰው የተፈጠረው የተቸገረን እንዲረዳ፣ የራበውን እንዲያበላ፣ እንዲያጠጣ ረሀቡን ችግሩን፣ ብሶቱን እንዲመለከት የእግዚአብሔርን እንግዳ በማክበር የእሱን ትዕዛዝ በማዳመጥ ተባብሮ መኖርን ያንፀባርቃል፡፡

ሰው ጤነኛ ሆኖ ቤት ኖሮት ወደ ኋላ መሸሽ እንደማያስፈልግ ያመለክታል፡፡ ሟች በቤቷ ውስጥ የነበረውን ደስታና ፈንጠዚያ፣ ድምቀት፣ ዝነኛ መሆንን የሚገልጽ ነው፡፡ ሟች በህይወት እያለች ማብላት፣ ማጠጣቷን ይገልፃል፡፡

በዚህ ግጥም ውስጥ “መፈታቱ አይቀርም ቤትና ገበያ” የሚለው ስንኝ ሰው በዚህ ምድር ላይ ሲኖር ተዝናንቶ፣ ተደስቶ፣ ስቆ፣ ተጫውቶ፣ ይኖራል፡፡ ነገር ግን ቢኖርም ሞት እንዳለ ማሰብ እንዳለበት ይነግራል፡፡ “ዞሮ ከቤት ኖሮ ኖሮ ከመሬት” የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ሰው ቢኖርም መሞቱ አይቀርም የሚለውን እሳቤ ያንፀባርቃል፡፡

“መ”ን ስንመለከት እናት ለልጇ ደብቃ የምታበላ የረሃብ መድኃኒት የሆነችው እናት ስትሞት የወለደች አራስ በረሃብ እንደምትጎዳ የሚያሳይ ገፅታን ያሳያል።

የሙሾ ግጥሙ የሟች ልጆች ወልደው ሲተኙ የእናት ጉርሻ፣ የእናት እንጎቻ፣ እናት ሮጣ መድረሷን፣ ለልጅ መርገብገቧን፣ ማዘኗን፣ ወልደው ከተኙት ሲርባቸው ይህን ሁሉ በምናባቸው እየሳሉ እያስታወሱ እንዲያለቅሱ የሚያደርግ ትዝታ አጫሪ ነው።

በሌላ መልኩ ደግሞ እናት በህይወት ስትኖር የማንረሳት፣ የምናስታውሳት፣ ሁሌም አይዞሽ እያልን እንዳትክልት የምንከባከባት መሆኑን ያሳየናል። እናትን በህይወት ስትኖር ቀለል አድርጎ የማየትን ጉዳይ ወደ ኋላ ተመልሰን እንድናስታውስ የሚያደርግ ግጥም ነው።

በእነዚህ አራት የሙሾ ድርደራዎች የተመለከትኩት ሟች በህይወት ዘመኗ ሰለቸኝ፣ ደከመኝ፣ ሳትል ለራበው ስታበላ፣ ስታጠጣ፣ ፊቷን ሳታጠቁር ስቃ፣ ተጫውታ ፣መኖሯን የሚያንፀባርቅ ነው። በተጨማሪም ለተተኪው ትውልድ “አርአያ” መሆንን የሚያሳይና ማህበረሰቡ ግንዛቤን ጨብጦ አብሮ መኖርን የሚያመላክት መልእክት አለው።

### አልባሳት እና የሚያዙ ቁሳቁሶች

አልባሳት “ሰይኝ” ይባላል። አልባሳት በአለማዊም፣ በመንፈሳዊም ማሳመሪያ፣ ማስዋቢያ ናቸው። ሳቢና ማራኪ አድርጎ የሠውን ልጅ ውበት ይገልጻሉ። በተጨማሪም ለደስታም ለሀዘንም እንደ ባህሉና እንደ አካባቢው ሁኔታ ይላበሳሉ።

በክመንት ማህበረሰብ ሴትም ይሁን ወንድ ሲሞት የሟች ቤተሰብም ይሁኑ ዘመድ የሚያደርጉት አልባሳት የሟችን ቀረቤታ፣ ዝምድና ጓደኝነት የሚያመለክት ነው።

በለቅሶ ስርዓቱ ላይ ወንዶች ነጭ ቀሚስ ለብሰው ጃኖ ወይም ቀይ ጥለት የገባበት ጋቢ በመደረብ ስርዓቱን ያከናውናሉ። ጥለቱ የሚያሳየው ሰው ሲሞት መገነቻ ሲሆን፤ ፀሎት ሲደረግ መስዋዕት የሚቀርበው ቀይ በግ፣ ቀይ ወይፈን፣ ቀይ ዶሮ፣ ነጭ ዶሮ፣ ነጭ በግ መሆኑንም ነው።

መስዋዕትነቱም ከእግዚአብሔር የሚደርስ የውቃቢ አስታራቂ ነው የሚሉትን ያንጸባርቃል። ጥቁር መስዋዕት ከታረደ መላእክት አይቀበሉም ብለው ያምኑበታል። /የቡድን ተወያዮች 18/06/2011/።

**ካባ (ሸመነብስ ሼይን/፡-** በክመንት ማህበረሰብ ካባ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው በሀዘንም በደስታም ጊዜ የሚደረግ ባህላዊ ተደራቢ ልብስ ነው፡፡ በሀዘን ጊዜ ሴቶች ብቻ ሲለብሱት፣ በደስታ ጊዜ ደግሞ ከመዘና ቄሶችም ሆኑ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች የሆኑ ቄሶችም ያጌጡበታል፡፡ ካባውን በሀዘን ጊዜ ክብ ሰርተው የሚያለቅሱበት እናት፣ እህት፣ አክስት፣ የልጅ ሚስት ሲሆኑ ለልጅ፣ ለዘመድ፣ ለጎረቤት ውስጣዊ ምስጢር ተካፋይና አዋቂ የሠውን ችግር የምትረዳ፣ የሰውን ፊት በማየት ብሶቱን አይታ ያላትን የምታካፍል፣ "ክፍትፍቱ ፊቱ" እንደሚባለው በፊቷ ፈገግታ ሰውን የምታጠግብ፣ ለችግር መፍትሄ የምታፈላልግ አጋዥ ረዳት እንደነበራት የሚያሳይ ነው፡፡



**ፎቶ 8፡- የሚች ቤተዘመዶች ካባ ለብሰው ሲያለቅሱ (ፎቶ በአጥኚዋ)**

ይህ እናታችን ስትሞት መዝናናቱን፣ መደሰቱን፣ ችግራችን፣ ረሃባችን፣ ብሶታችን ታውቀ፣ ተገለፀ፣ ሚስጢር ደባቂ የነበረችው እናት ችግሩ በገሀድ ወጥቶ ታየ የሚል ትዕምርት አለው፡፡

**ባህላዊ ጥልፍ ቀሚስ፡-** ይህ በእጅ የተጠለፈ ባህላዊ ቀሚስ በጀርባ ተደርጎ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚደረገው ከጥጥ የተፈተለ በሸማ አምሮ ተውቦ የተሰራ ሲሆን በባህላዊ የእጅ ጥልፍ ተጠለፈ ነው፡፡ ሚች በህይወት ዘመኗ ከተጠለፈው ባህላዊ ቀሚስ ውጪ ሌላ ልብስ እንደማትለብስ የሚያሳይ ነው፡፡ ይህን ባህላዊ ቀሚስ በጀርባዋ ያደረገችው የሚች ታናሽ እህት ናት፡፡

ይህም ያላት የቤት እመቤት ጥጥ ፈታይ ባለሙያ መሆኗን እና ጥበበኛ፣ ተመራማሪ፣ አንዱን ከአንዱ የምትተካ አዋቂ ብልሀተኛ ሴት መሆኗን የሚገልፅ ትዕምርት አለው፡፡



**ፎቶ 9፡- የሚቿ ታናሽ እህት ባህላዊ ጥልፍ ቀሚስ ለብሳ ሀዘኗን ስትገልጽ (ፎቶ በአጥኚዋ)**

***የወገብ መቀነት፡-*** በክመንት ማህበረሰብ ሁልጊዜም ባህላዊ ቀሚስ ስለሚለበስ የወገብ መታጠቂያ ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡ ይህም ቀሚሱ በሽማ ሲሰራ እናትና ልጅ ሆኖ የሚዘጋጅ ቀሚስና መቀነት ነው፡፡ በመሆኑም የሚች የመጨረሻ ልጅ የእናቷን መቀነት ከአንገቷ ስታደርግ እናት ለልጇ ህይወቷን የምትሰጥ መጠሪያ የሆነች፣ ወገቧን ታጥቃ ሰርታ ለፍታ ደክማ ልጆቿን አባት ሳያግዝ ትልቅ ደረጃ መቀነቷን ያጠበቀች ጀግንነቷን የሚገልጽ ትዕምርት ነው፡፡



**ፎቶ 10፡- የሚች የመጨረሻ ልጅ የእናቷን የወገብ መቀነት ለብሳ ስታለቅስ (ፎቶ በአጥኚዋ)**

**የባሏን ሱሪ ማዘቅዘቅ፡-** ቀደም ብሎ ባሏ የሞተባት ከሟች አዋጋሽ አበራ የለቅሶ ስርዓት ላይ እንደ አዲስ የባሏን ሱሪ በአንገት አዘቅዝቃ ስታለቅስ ተመልክቻለሁ፡፡



**ፎቶ 11፡- የሟች ሚስት የባሏን ሱሪ ዘቅዝቃ እና ፎቶውን ይዛ ስታለቅስ (ፎቶ በአጥኚዋ)**

የሟች ሱሪ ተዘቅዝቆ መለበሱ የሚያሳየው አንደኛዋ ሴት ከአዳም ግራ ጎን ከአጥንት የተገኘች መሆኗን ሁለተኛው ባልና ሚስት ቤት መስርተው ልጅ ወልደው ሲታመም ታማ፣ ስትታመም ታሞ፣ ሲከፋ ተከፍታ፣ ሲከፋት ተከፍቶ… የመሳሰሉትን ለአልቃሽ ለማሳየት ነው፡፡

ሦስተኛው ባልና ሚስት በህይወት ዘመን አብረው ሲኖሩ "ባልና ሚስት አንድ አካል አንድ አምሳል" የሚለውን የሚገልጽ ነው፡፡ አራተኛው ሟችን በወሬ ብቻ ሆኖ ሳይታወቅ ኖሮ ሲሞት ሚስት ያለው መሆኑን የሚያውቁበት ትእምርት ነው፡፡

ሌላው "ኮት" ሟች በህይወት እያለ በማህበራዊ ጉዳይ ላይ ብዙ ተግባቦት ካለው ቤተዘመዱ፣ ጎረቤቱ፣ እህቶቹ በሙሉ በለቅሶው ስርዓት ላይ ለብሰው ያለቅሳሉ፡፡ በዚህ ሰዓትም ኮቱን የደረቡት

*"ኮትህን ደርበኝ፣ ጋቢህን ደርበኝ*

*ትዳሬን ፈታሁኝ ማን አስታራቂ አለኝ፡፡"*

በማለት ኮቱን የደረቡት ሴቶች በሙሉ ያነባሉ፣ ይተክዛሉ፡፡ ይህ ቃል ግጥም የሚያሳየው ሟች በህይወት እያለ ለበረደው የሚያለብስ፣ በዓይን አይቶ የሠውን ችግር የሚረዳ፣ አዛኝ፣ ሩህሩህ፣ ደግ፣ ቸር፣ መሆኑን ነው፡፡ "ትዳሬን ፈታሁኝ" የሚለው ሀረግ ሟችበአካባቢውየተጣላንአስታራቂ፣ ፈጥኖ ደራሽ፣ ጥቂት የማይወድ፣ አላፊ ወይም ራሱን

አሳልፎ የሚሰጥ ነው፡፡ ሴት ልጅ አግብታ ከትዳሯ ስትፈናቀል የተለያዩ ምክንያቶችን አፈላልጎ ባልና ሚስትን እንደሚያስማማ፣ እንደሚያስታርቅ የሚያመለክት ትዕምርት አለው፡፡

**ቁሳቁሶች /ወፊር ወፊር/፦** ሚች በህይወት ዘመኗ ስትኖር ብዙ ጌጣጌጦችን ትጠቀማለች፡፡ እነዚህ ጌጣጌጦችም ከአንገት ተደርጎ በደረቷ ወርዶ መቀነቷ ስር የምታደርገው ጎንብሳ ድሪ፣ ሦስት መንታ ድሪ ይባላል፡፡ ሌላው በአጭር ጥቁር ክር የጣሊያን ጠፍጣፋ ብር መስቀል፣ የብር ቀለበት፣ የጆሮ ጌጥ፣ የእጅ አንባር፣ የእግር አልቦ ያላት መሆኑን ስታጌጥበት የኖረችው ነው፡፡ ይህ ጌጥ ደግሞ ለሴት ብቻ የሚደረግ ነው ጌጡን ይዛ የምታለቅሰውም የሚች የመጀመሪያ ልጅ ዋንጫ ይዞ የሚያለቅሰው ሚስት ናት፡፡

የዚህ ትዕምርት ሀብታም ያላት፣ ታዋቂ በአካባቢው ቀዳሚ መሆኗን የሚያሳይ ነው፡፡ ጌጣጌጦችም አንድ ላይ በአንድ እንጨት ጠቅልላ የመጀመሪያ ወንድ ልጅ ሚስት ለተመልካች እያሳየች ይለቀስበታል፡፡ የሚች ሁኔታ በሙሾ እንደዚህ ይገለጻል፡፡



**ፎቶ 12፦ የልጅ ሚስት የሚችን ጌጣጌጥ ይዛ ስታስለቅስ (ፎቶ በአጥኚዋ)**

**ዋንጫ /ሽምንጃ/፡-** ይህ ከበሬ ቀንድ የሚሰራ ለብዙ ጥቅም የሚውል ነው፡፡ የመጀመሪያው በለቅሶ ስነ ስርዓት ጊዜ የሚያዝ ሲሆን፤ በስርዓቱ ጊዜ በነጭ (በአቡጀዲ) ጨርቅ ተጠቅልሎ የሟች የመጀመሪያ ወንድ ልጅ ቀኝ እጁን በጋቢው በላይ አውጥቶ የተሸፈነውን ዋንጫ ይዞ በግራ እጁ ለቀብር የመጣውን ሰው ትከሻ በመያዝ የእናቱን ሀዘን ሲገልፅ ይታያል፡፡



**ፎቶ 13፡- የሟች ታላቅ ልጅ ዋንጫ ይዞ ሲያለቅስ (ፎቶ በአጥኝዋ/**

የዚህ ትዕምርት ሟች በህይወት እያለች ዋንጫውን በቀኝ እጇ ይዛ በባህሉ "አፈር ሲሆን" የሚባለውን አገላለፅ እየገለጸች የማር ብርዙን፣ ጠላውን በማቅረብ ጠጡ ያለችበትን የሚገልፅ ነው፡፡ ከሚጠጣው ጠላ ጋር በባህላዊ ሰፌ "መሶብ" ምግቡን ሞልታ ብሉ ጠጡ እያለች በባህላዊ ሸክላ በተሰራ "ገንቦ" ጠላውን በማጀት በማምጣት በዋንጫ እየሞላች የምታጠጣውን የሚያመለክት ነው፡፡

### የሟች /ለጋሽነትን/ የሚገልፁ ቃል ግጥሞች

ሀ ላይለቀስ ነው ወይ ወትሮስ ላበላ ሰው
ላይለቀስ ነው ወይ ወትሮስ ላጠጣ ሰው
እጁ ወንፊት ሆኖ ሰጥቶ ለጨረሰው፡፡

ለ ከሁሉም ከሁሉም እናት ትሞታለች
ከማጀት አብልታ አልበላም ትላለች፡፡

ሐ   ስጡኝ ያንን ዋንጫ በእምባ እሞላዋለሁ
በሞቴ እየተባልኩ ጠጥቼበታለሁ፡፡

መ   ያንን ጥሩ ጠጅ ጠጥቼበታለሁ
ያንን ጥሩ ጮማ በልቼበታለሁ
በራሴ ሀዘን ይገፔ በዓይኔ እቀዳዋለሁ፡፡

/ቤተ ዘመድ በቅብብሎሽ 17/06/2011/፡፡ሟች አዋጋሽ አበራ በህይወት ለማህበረሰቡም ለአካባቢውም የሚያበሉ የሚያጠጡ የነበሩ ሰው መሆናቸውን ነው፡፡ ሟች ከማህበረሰቡ ላቅ ብለው የሚታዩ ሀብታም የሆኑ እና ላቅ ያለ ደረጃ እንዳላቸው የሚያሳይ ነው፡፡ ይህም ብሉ ጠጡ የተባለበትን ሊለቀስላቸው የሚገባ ትርጉምን የያዘ ነው፡፡ "ወንፊት" የሚለው ቃል ለሁሉም ተደራሽ መሆንን፣ ለጋሽ ሰጪነትን ያንፀባርቃል፡፡

ሟች ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም ሁልጊዜም የፊታቸውን ፈገግታ በማሳየት ለቸገረው በመስጠት ለእኔ ይትረፍ ሳይሉ ያላቸውን ደግነት በማሳየት ነው፡፡ በለቅሶው ስርዓት ላይም የበላ የጠጣው፣ የተሰጠው በሙሉ አልቃሽ አልቅሶ ምስክርነትን እንዲሰጥ ጋብዞታል፡፡



**ፎቶ፡ 14 አስክሬኑ ከመውጣቱ በፊት የሟች ቤተዘመዶች በማልቀስ ላይ (ፎቶ በአጥኚዋ)**

"ለ"ን ስንመለከት "እናት" ሁልጊዜም ሞት እንደማይገባት በህይወት እንድትኖር፣ እናት የማትጠገብ፣ የማትሰለች የዓለም ሁሉ መድኃኒት መሆኗን የሚያንፀባርቅ ትርጉም ያለው ነው፡፡ በተለይ ደግሞ "ከማጀት አብልታ አልበላም ትላለች" የሚለው ስንኝ እናት ሚስጢራዊ፣ እናትን ተመራምረን ውለታዋን የማናገኝለት ድብቅ ሚስጢራዊ የሆነች መሆኗን የሚነግር ነው፡፡ በጥቅሉ የእናት ሚስጢር "ኃይል" መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡

ሌላው "ሐ"ን ስንመለከት ደግሞ ሟች በህይወት ዘመናቸው ለቸገረው ማብላት ማጠጣትን የሚገልፅ ነው፡፡ ሟች በ "ዋንጫ" ይህ ማለት በትንሽ መጠጫ ጠላውን ሰጥተው እንደማይረኩ፣ እጃቸው በሰፊ መስጠትን የለመደ መሆኑን ያሳያል፡፡ ለዚህም በሰፊው ዋንጫ የጠጣ ሰው ለሟች ከአቅም በላይ በመሆን እንባን ማፍሰስ እንዳለበት ያመለክታል፡፡

በክመንት ማህበረሰብ "ዋንጫ" በደስታ ጊዜ ሰርግ፣ ክርስትና፣ ልደት፣ የተለያዩ በዓላት ሲኖሩ ትልልቅ አዛውንት ሰዎች ጠላ የሚጠጡበት ነው፡፡ በዋንጫ የሚጠጡትም ወንዶች ሲሆን፤ ሰጪዎች ደግሞ የቤቱ "እማውራ" የሆኑ እናቶች ናቸው፡፡ ለዚህም ነው በሰፊው ደግሳ እንደምታበላ፣ እንደምታጠጣ "ዋንጫ" ተይዞ የሚለቀስላት፡፡ ዋንጫ የደጋጎች፣ የመኳንንቶች፣ የንጉሶች መጠጫ የሆነ የክብር መግለጫ ነው፡፡ ከቅል የተሰራው ማውራው ደግሞ በቅዳሴ ሰዓት፣ በፀሎት ሰዓት የክመንት ሃይማኖት ኃላፊ የሆኑት ወንበሩ፣ ከመዘና ቄሶች፣ ዲያቆናት ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱ በአኮፋዳ ይዘው በመሄድ የሚጠጡበት ነው፡፡

የመጨረሻው "መ"ን ስንመለከት ማብላት ማጠጣትን የሚገልፅ ሲሆን ለየት የሚያደርገው በዚህ ግጥም ውስጥ "በራሴ ሀዘን ይገፔ በዓይኔ እቀዳዋለሁ" የሚለው ስንኝ የሟች ልጅ፣ ቤተሰብ፣ ዘመድ፣ ጎረቤት የልባቸውን ሀዘንና ስብራት፣ በውስጣቸው መጎዳታቸውን፣ ምርር ያለ የሀዘን ስሜት እንደገጠማቸው፣ የእራስ ህመም እንደሆናቸው የሚያሳይ እና የሆድ ብሶትን የሚጨምር መሆኑ ነው፡፡ በሟች እጅ ጥሩ "ጮማ" እየበላ የኖረው  በዓይኑ እንባውን እያቀረረ፣ ያወርዳል፣ ያፈሳል፣ ብሶቱን ያሰማል የሚልም አሳብ ይዟል፡፡

አስክሬኑ ወደ ቀብር ቦታው ሲሄድ መንገድ ላይ አምስት ጊዜ ሲያርፍ ሁለቱ ደግሞ አስክሬኑ ከቤት ሲወጣና ከድግናው ቦታ ሲደርስ ነው ሰባት ቦታ ያረፈው፡፡ በዚህም ሰዓት ሙሾ ደርዳሪ አዳዲስ ግጥሞችን ሲያቀርብና ሲደረድር አልሰማሁም፡፡ ከተለያየ ቦታ ሲያርፍ በፊት የተባለውን ሌላኛው አስለቃሽ ከመድገም ውጪ አዲስ ስንኞችን አልሰማሁም፡፡

የአስክሬኑን ግብዓተ መሬት ካጠናቀቁ በኂላ ከመቃብሩ ላይ ቁልቋል ቆርጠው ሲተክሉም ተመልክቻለሁ፡፡ ይህንም የቀብር ፈፃሚ ከሆኑት ውስጥ አቶ እንደሻው ጠጋውን ስለ ቁልቋሉ ስጠይቃቸው የሰጡኝ መልስ ሟች በህይወት ዘመናቸው ሲኖሩ የሰሩት መጥፎ ስራ ካለ ይህ የተተከለው ቁልቋል በሰላሳ ቀን ውስጥ ሉል ቅጠል ከጫፍ ካልታየ ሟች ኃጢያተኛ ናቸው ብለው ይተረጉሙታል፡፡



**ፎቶ፡ 15 የሟች መቃብር ስፍ /ፎቶ በአጥኚዋ /**

የመቃብር ስፍራ/ፎቶ በአጥኚዋ- ከዚህበተቃራኒ ደግሞ ቁልቋሉ በዚህ ቀን ውስጥ ሉል ቅጠል ይዞ እና "አቆጥቁጦ" ከታየ ሟች በህይወት ዘመናቸው ጥሩ ስራ እንደሰሩ እና ከኃጢአት ነፃ መሆናቸውን ያሳያል (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ እንደሻው ጠጋው 18/06/2011)፡፡

## 4.5.5 ድህረ ቀብር /ድዝና ግቬው/

በለቅሶ ስርዓቱ ክዋኔ ላይ ስነ ስርዓቱ ካለቀ በኂላ ከመጀመሪያው ቀን እስከ ሰልስቱ ድረስ ሀዘንተኞችን ለማፅናናት በተዘጋጀው ዳስ ውስጥ የተለያዩ ምግቦች ለምሳሌ፡- እንጀራ፣ ወጥ፣ ጠላ በማቅረብ የሟች ቤተሰቦችን እና ለራሳቸው ጎረቤቶች ያመጡትን ምግብ በመብላት በመጠጣት ራሳቸውንም እያዝናኑ ሀዘንተኞችንም ይመግባሉ፡፡

ለማፅናናት የመጣው ሰው ሀዘንተኞችን የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ለምሳሌ፡- ቀልዶችን፣ ተረቶችን፣ አፈ ታሪኮችን እንዲሁም አፅናኝ የሆኑ ምሳሌያዊ ንግግሮችን የመሳሰሉትን በመግለጽ ያዝናናሉ፡፡ በክመንት ማህበረሰብ አንድ ሰው ሲሞት ነፍሲቱ እስከ ሶስት ቀን በአጥር ዙሪያ ትቆያለች ተብሎ ይታመናል፡፡

የከመዘናው ቄስ አንድ ቀይ ያልሸና በግ እና ለማጥቃት ያልደረሰ አንድ ወይፈን ያርዳሉ፡፡ በመጨረሻም የበግ እና የወይፈኑን ምላስ ተቆራርጦ በጓሮ በብሳና ቅጠል ተጠቅልሎ ይጣላል፡፡ የሃይማኖቱ ተከታይ የሆኑት ሀዘንተኞችና ምዕመናን ነፍስ ይማር እያሉ የተረፈውን ይበላሉ፡፡

> *ይህ በብሳና ቅጠል ተጠቅልሎ የሚጣለው አመና ወይም መቋደሻ ለተሳላኪዎች ወይም ለጀከረንታው፣ ለግርግሊዮ ለሚባሉት መላእክት የሚደረግ ነው፡፡ እነሱም በቤቱ ጓሮ ለሦስት ቀን ለቆየችው ነብስ ካቀመሱ በኂላ ተንከባክበው ወደ እግዚአብሔር ያደርሷታል ይባላል" (ቃለ መጠይቅ፣ ወንበር አማረ ሙሉነህ 06/06/2011 ዓ.ም)፡፡*

### 4.5.6 የማሳረጊያ /የምርቃት/ ስርዓት

የማሳረጊያ ምርቃት ስርዓት ወንበር አማረ ሙሉነህ ለቀብር ስነ ስርዓት የመጣውን ዘመድ የሚመርቁበትና እና የሟችን ነብስ ይማር የሚሉበት ጊዜ ነው። ምርቃቱንም በአዋጋሽ አበራ ቀብር ላይ እንደተመለከትኩ የሚከተለውን ይመስላል።

> "በክመንቲሳ" *"ኪዱስ ስምዘኛናውንኛን (3) ኪዱስ ስምዝኛናን፣ ምንስምዝኛትና ሲውዝ ምዝኛትና ኒክረዝ ኒኛንዝ አውኛዝ ጣይ ሰማይ ወይኒ ትርንን ብኵኒ ወረስኧ ብኵኒ ወርስ ቲምስ ዳኽስ ኒማር ዋኒና ሽንተኒዝዝ ሽንተሲሳይ ሸሺዝ ስሊኻ ይሸቢን። ይደረለቢኩስቭ ሽቢን። ይደረለቢኩስቭ ለኩሽ ካጋስ ሽቢን። ይደረ ኸርስ ጋሻ ሽቢን" እስርዓቱ ላይ የመጣው ታዳሚ ቋንቋውን ሙሉ በሙሉ ስለማይሰማ የቅመንት ሃይማኖት ሃላፊ የሆኑት* ወንበር አማረ ሙሉነህ እንዲህ በማለት ተርጉመውታል፡-
>
> *"ለማፅናናት የመጣችሁትን ዘመድ ወገን ዕድሜና ጤና ይስጣችሁ። እንጀራውን ያብዛልን፣ ፍቅሩን ያብዛልን፣ ከብክባችሁ የቀበራችሁ ዘመዶች ወገኖች ቀባሪ አትጡ። "ወይኒ ትርንን ብኵኒ" ሀገሩ ወይንና ትርንን ይበቀልበት። "ሸሺዝ ሰሊኻ ሸቢን" ወተትና እርጎ የሚገልቅበት የሚፈስበት ይሁን።*
>
> *የሟችን ነብስ ይማርልን፣ "ልኩስ ካጋስ ሸቢን" ሟችን እግረ ደረቅ ያድርግልን፣ ሞት እንዳታስከትል ያድርግልን፣ እሷ በሄደችው ትቅር፣ ሰው የማይሞት ይሁን። የሞተችውን ነብሷን በገነት ያኑርልን፣ መንግስተ ሰማያት ያስገባልን። "ሰሊኻ ሻቢን" ሀገሩን ሀገረ ህይወት ሀገረ ገነት ያድርግልን (ቃለ መጠይቅ አማረ ሙሉነህ 17/06/2011)።*



**ፎቶ 16፡ በወንበሩ ከድግናው ቦታ የማሳረጊያ የምርቃት ስነ ስርዓት ሲደረግ (ፎቶ በአጥኚዋ)**

ከዚህ በኋላ ደግሞ ወንበሩ ቆመው "እኛን ለማፅናናት የመጣችሁ ቤተ-ዘመዶች በሙሉ ነብስ ይማር ብላችሁ እንድትሄዱ የመጣውን እህል ውሃ ቅመሱልን በማለት ለቀስተኛው የተዘጋጀውን የነፍስ ይማር ምግብ እንዲመገቡ ጋበዙ።



**ፎቶ 17 የነፍስ ይማር እንጀራ ከቀብር ስነ ስርዓት በኋላ ሲበሉ (ፎቶ በአጥኚዋ)**

ቆይቶም በአስተባባሪዎች አማካኝነት ወንድ ለብቻ ሰባት ሰባት ሰው በመሆን፣ ሴቶችም እንዲሁ ሰባት ሰባት በመሆን የብሳና ቅጠል ተጎዝጉዞ በዚያ ላይ አንድ እንጀራ በአዋዜ ቀርቦ ያን ምግብ እየበሉ ነብስ ይማር እያሉ ሄዱ።

## 4.5.7 ተዝካር (የሙት ዓመት) አከባበር ስነ ስርዓት

በክመንት ማህበረሰብ "ሙት ዓመት" ሲከበር በባህሉ መሰረት የሁለተኛ የቀብር ስነ ስርዓት ተብሎ ይታመናል። ይህ የሁለተኛ የሙት ዓመት መታሰቢያ የለቅሶ ስነ ስርዓት ሟች ከቀብር ስነ ስርዓት በኋላ በአስራ ሁለተኛው ወር ላይ የሚደረግ ስነ ስርዓት ነው። ይህን በዓመት አንድ ጊዜ የሚደረግ ስነ ስርዓት የሟች ባለቤት ወይም ልጆች የሚያከናውኑት ነው። የቡድን ተወያይ እንደገለጹልኝ ይህ የሁለተኛ የለቅሶ ስርዓት ግን ለሁሉም አይደረግም። ከህጻናት ጀምሮ እስከ አላገቡት ድረስ የማይደረግ ስነ ስርዓት ነው። ይህ የሁለተኛ የለቅሶ ስነ ስርዓት ካገቡት ጀምሮ እስከ አዛውንት ወይም "ካስ" ቁርባን ላላቸው የሚከወን ስርዓት ነው። ለህፃናት እና ላላገቡት የማይደረግበትም ምክንያት "ህፃናት" እንደተወለዱ ያሉ እና ኃጢአት የላቸውም በማለት ሲሆን

ለወጣቶች/ላላገቡ/ ደግሞ ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሄዋን አልደረሱም በማለት ነው፡፡ በዕድሜያቸው ሲገለጽ ከ8-17 ዓመት ያሉት ናቸው /የቡድን ተወያዮች፣ 18/06/2011/፡፡

ይህ ሙት ዓመትም ሟችን ላለመርሳትና ግብዓተ መሬት ከተፈፀመ በኂላ ነፍሱ ወደ መንግስተ ሰማያት ይገባል ተብሎ ሙሉ በሙሉ ይታመናል፡፡ በክመንት እምነት የሙት ዓመት ፍትሃት ስነ ስርዓት እስከ አሁን ድረስ ያልተረሳና ያልቀረ መሆኑን /የቡድን ተኮር ተወያዮች 10/06/2011) ገልፀውልኛል፡፡

በክመንት እምነት የሙት ዓመት የሚከበርባቸው ቀናቶች እሁድ፣ ማክሰኞ እና ሀሙስ ናቸው፡፡ በእነዚህ ከሦስቱ አንድ ቀን ታስቦ ፍትሃት /ቀዳሴ/ ይደረጋል፡፡ ከእነዚህ ውጪ በአራቱ ቀናቶች "ቅዳሜ፣ ሰኞ፣ ረቡዕ እና አርብ" ከተቀደሰ በማህበረሰቡ ላይ ከፍተኛ የሆነ ረሃብ፣ ጦርነት፣ በሽታ፣ ሞት ይመጣል ተብሎ ይታመናል፡፡ እነዚህ ቀናቶች በአፈ ታሪክ ደረጃ "ሙሉ ያልሆኑ ጎዶሎ ቀናቶች" ናቸው ይባላል፡፡ ሌላው በእነዚህ ቀናቶች ላም፣ በሬ፣ በግ ባለቤቱ እያየ ፊት ለፊት በገመድ ተጠልፈው እንኳን ቢሞቱ "ኪዱስ" ተብሎ ስላልታረደ ጠቅልሎ ከመጣል ውጪ ሥጋቸው አይበላም፤ በአደረይኪ ዘንድም ውግዝ ነው /ቃለ መጠይቅ፣ ወንበር አማረ ሙሉነህ 10/06/2011/ በማለት ገልጸውልኛል፡፡

ይህ የሚደረገው የሙት ዓመት ፍትሃትም "ምዝገና ዝቆኔ" ይባላል፡፡ ይህም በዓመት ሦስቱን ቀን ጠብቆ የሚደረግ የፍትሃት ስርዓት ነው፡፡ ይህም የሟች ቤተሰቦች ቀድመው ለሚበላውም፣ ለሚታረደውም እና ለሚጠጣው በጀት ያስቀምጣሉ፡፡

ሌላው በተለይ ጠላውን "ካስ" የቆረበች ሴት ያዘጋጃሉ፡፡ እኚህ ቆራቢ ሴትም ጠላውን ለማዘጋጀት ከአንድ ወር በፊት ያቅዳሉ፤ ሲያቅዱም ገላቸውን በጠዋት ተነስተው እንደታጠቡ ወፍ ሳይቀምሰው በተቀዳ የምንጭ ውሃ ለብቅል የሚሆነውን ገብስ ይዘፈዝፋሉ፡፡ የሚዘፈዘፈው ብቅልም እሁድ ከሆነ ማክሰኞ ያጠላሉ /ውሃውን ያወጣሉ/፤ ማክሰኞ ከተዘፈዘፈ ሀሙስ ያጠላሉ /ውሃውን ያወጣሉ/፡፡

በቀሩት ቀናቶች ቅዳሜ፣ ሰኞ፣ ረቡዕ እና አርብ ቀን ሰው እንኳን ቢሞት መዋል ማደር የሚባል የለም፤ ፍትሃትም አይደረግላትም፡፡ እነዚህ ቀናቶች በህገ ልቦና መሰረት ጎደሎ ወይም ሙሉ ቀናቶች የማይባሉ ቀናቶች ናቸው ተብለው ይታመናሉ፡፡

ካስ ወይም ቁርባን ያገኘችው ሴት የበቀለውን ገብስ በመፍጨት "ዲና" አትኳሮ የተባለውን ቅጠል ከብቅሉ ጋር በማዋሀድ ለቁሶች፣ ማጅም" (በሽማግሌዎች) ይመረቃል፡፡ እነዚህ ለጌታ

መላእክታን ለጀከረንታው ለገርግሊዮ ላይከብሮ ብለው ከፍትሀቱ ስርዓት ላይ የሚደፉ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ሽምብራ ቂጣ፣ በቅቤ የተዘጋጀ በሶቲን፣ እልበት፣ ወተት ይጥላሉ፡፡ ለጌታ መላእክታን ካስቀመሱ በኋላ አደረይኪ ከሰማይ ወርዶ ሲመጣ የወርቅ ጭልፋ "ሚስኪዮን" ቅል ይዞ በመጣው የተዘጋጀውን ጠላ ይጠጣሉ፡፡ የኋላ ልጅ አዳፋ ነው እቃየን ያሳድፋል ብሎ "ምስግድባ" ወርቅ ለቅል ውስጥ ከሰማይ ያመጣውን ቅል ወይም መራራ በአመት አንድ ጊዜ ሙት ዓመት ሲደረግ ምትጠጡት በመራራ ቅል ነው ብሎ አደረይኪ (እግዚአብሔር) ባዘዘው መሰረት ድርጊቱን ያከናውናሉ፡፡

ሀሙስ ሀሙስ በሁለት ሳምንት አንድ ጊዜ "ምዝቛና" ይውላል፡፡ ምዝገና በክርስቲያን "ባለእግዚአብሔር" ወሩ በገባ በ29 ቀን የሚከበር የእግዚአብሔር በዓል እንደሚባለው ቄስ ቢምር አስናቀው "ምዝቛና" በማይውልበት ሀሙስ ግበሩኽ የሚባል በዓል እንዳላቸው አስረድተውኛል፡፡ በወርሃ ሀምሌ የመጀመሪያው ማክሰኞ ዕለት "ክብር" የሚባሉት የዘር ሀረጎች በደማቅ ሁኔታ እንደሚያከብሩት ገልፀዋል፡፡ ከቀኖች መካከል ለምን እሁድ፣ ማክሰኞ፣ ሀሙስ ለምን እንደተመረጡ ቄስ ጌቱ አያሌው በቃለ መጠይቁ እንዳሳወቁኝ "ከአያት ቅድመ አያታችን ሲወርድ ሲዋረው የወረስነውና ይዘነው የመጣነው ነው፡፡ የድሮ ሰው የጋብቻ ስርዓት ሲያደርግ እና እህል ከአውድማ ወቅቶ ወደ ጎተራ ሲያስገባ በሦስቱ ቀናት ብቻ ነበር ሲሉ ገልጸውልኛል /ቃለ መጠይቅ፣ /18/06/2011/፡፡

ይህም የተዝካሩ ስነ ስርዓት እሁድ ሲሆን ሀሙስ ቀድመው የከመዘና ቄሶች የተገዙትን በጎች ካረዱ በኋላ ምላሳቸውን ቆርጠው የአስክሬኑ ነፍስ ከወጣበት ቤት ኋሮ ቆራርጠው በብሳና ቅጠል ጠቅልለው ይጥላሉ፡፡ ይህ ማለት ነፍሲቱ የሚደረገው የሙት ዓመት ስነ ስርዓት ስለምታውቅ ከሦስት ቀን በፊት ትመጣለች ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ በብሳና ቅጠል ተጠቅልሎ የሚጣለው አመና /መቋደሻ/ የአደይረኪ መላዕክቶች ጀከረንታው፣ ግርግሊዮ፣ ይከብሮ… የመሳሰሉት ተላላኪዎች ለነብሲቱ ያቀምሷታል /ቃለ መጠይቅ፣ ቄስ ቢምር አስናቀው 18/06/2011)፡፡

ከመዘና ቄሶችም ይህን ካደረጉ በኋላ ለሟች ቤተሰቦች የበጉን ዋና ዋና ብልቶችን አንስተው ከሰጡ በኋላ ሌሎች ጨጓራ፣ ጉበት፣ ታልማ ወይም አንጀት የመሳሰሉትን ይጥላሉ፡፡ የበጎቹ ስጋም ለምዕመን እና ለቄሶቹ ለየብቻ ይሰራል፡፡ ወጡን የምትሰራ ታዋቂ የሆነች የቆረበች ሴት ነች፡፡ ምክንያቱም በግ ቀለል ያለ ስለሆነ ሴት እንድትሰራ ይፈቀዳል፡፡ ለለቀስተኛው ወይም ለዋናው ተዝካር የሚሰሩት ደግሞ ጎልማሳ ቆራቢ ወንዶች ናቸው፡፡

ይህን የተዘጋጀ ምግብ ወንበሩ፣ ከመዘና ቄሶች፣ ዲያቆናት፣ የንስሀ አባት እና ቁርባን ያላቸው የክመንት ባላባት የሆኑ አባቶች አብረው ይመገባሉ፡፡ የሚመገቡበት መሶብም ከመሬት ደረቅ ሳር ከተጎዘጎዘ በኋላ በላዩ ላይ ሰፋፊ የብሳና ቅጠል አስቀምጠው እንደ መሶብ ይገለገሉበታል፡፡ የሚበሉትም ለሰባት ለበሳት በመሆን ነው፡፡ በመቀጠልም የሚጠጣ ጠላ፣ ማር ብርዝ፣ ወተት ይቀርብላቸዋል፡፡ ይህንንም እንደተለመደው በቤቱ ጓሮ ከረጩ በኋላ ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀው ቅል ወይም በማውራ ይጠጣሉ፡፡

ሰባት  ጊዜ  ሳጊቶንማን ሽቢው ናድ

ሰባት ጊዜ  ቊንምንፋን ቶንማ

ሰባት ጊዜ  ከምከም ጋለቲውዛ

በመጥራት አምላክ ነብስ ከአንተ ጋር ናት ማርልን ማርልን /ሰባት/ ጊዜ ይባላል ሰርተኸዋል፣ ፈጥረኸዋል እና ለተቀናቃኝ አሳልፈኽ አንዳትሰጠው ይቅር በለው በማለት ሲፈቱ አድረው፤ ስርዓቱን ካከናወኑ በኋላ ደግሞ እሁድ በሬ ታርዶ የተጠራውን ማህበረሰብ "የክብር ልጆች፣ የይተንቲ ልጆች ብሉ ጠጡ ተብላችኋል" ሲባል ህዝቡ እግዚአብሔር ይመስገን ብሎ ይቀመጣል፤ የተዘጋጀው እህል ውሃ ይበላል ይጠጣል፡፡ የመስዋዕቱን አስፈላጊነት ቄስ ቢምር አስናቀው እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡

> *በቀድሞ ጊዜ አንድ ሰው አምላክ እድሜህ አርባ አመት ነው ቢለው፤ ዶሮ አርዶ አምሳ ሆነለት፡፡ አምሳ  ሲሞላው ደግሞ አሁንም ዶሮ ሰውቶ አምላክ ወይም አደረንኪ ስልሳ ሆኖልሀል አለው፤ ስልሳው ሲሞላም የተለመደውን መስዋዕት ሳያቀርብ ቀረ፤ "በዘጠና የለም ጤና" ብሎ ዶሮውንም ሳያርድ እግዚአብሔርንም ሳይለምን ሲቀር ያንኑ አመት ሞተ፡፡ ስለዚህ መስዋዕት ዕድሜ የሚያስረዝም ፀሎታችንና መስዋዕታችን የሞቱትን ነብስ ይማር ለማለት የሞተው በእግዚአብሔር ይቅር እንዲባል፤ የተረገዘው እንዲወለድ፣ የተወለደው እንዲያድግ፣ ሀገሩ ሁሉ ሰላም ውሎ ሰላም እንዲያድር፣ የተዘራው እንዲበቅል፣ እንዲያፈራልን፣ የታጨደው እንዲከወን፣ የታመመው እንዲድን፣ የተጣላው እንዲታረቅ፣ ያዘነው ሀዘኑ እንዲቀልለት፣ አምላክን ወይም አይረንኪን የምንለምንበት ሂደት ነው (ቃለ መጠይቅ፣ ቄስ ጌጡ ኢያሴው 12/06/2011)፡፡*

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው በብሳና ቅጠል ተጠቅልሎ የሚጣለው አመና ወይም መስዋዕት በመንፈስ ያለው አምላክ ወይም አደረንኪ በክብር መጥቶ መስዋዕቱን ይቀበላል ብለዋል የሚል እምነት አላቸው፡፡ በብዙ ጥንቃቄና ዝግጅት የሚያደርጉትም ይህን መስዋዕት እንዲቀበል ነው፡፡ በመጨረሻም ፍትሀቱን ላከናወኑት ቤተሰቦች ምርቃት /ገወተን/ ይደረግላቸዋል፡፡

የፍትሃት ስነ ስርዓቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የክመንት ግለሰቦች /ካስ/ ቁርባን ያላቸው ስድስት ያልሸኑ ወይፈኖችን ሰውተው ለምዕመናን ወይም ሟችን መጥቶ ለቀበረው በሙሉ ቀድመው ፍትሃቱን ስለሚነገሩ ወጣቶች ወጡን በበርሜል ሰርተው እሁድ ከ7፡00 እስከ 12፡00 ሰዓት ወንዱ ለብቻ ሴቶች ለብቻ በተለያየ ዳስ ለሰባት፣ ለሰባት በማድረግ ከስር ደረቅ ሳር በመነስነስ በላዩ ላይ የብሳና ቅጠል በመጎዝጎዝ የተዘጋጀውን ምግብ ይመገባሉ፡፡

ቄስ ጌጡ አያሌው በዚህ ስነ ስርዓትም ሀዘንተኞችን ያፅናኑ በሙሉ ሁለተኛውን ዙር የቀብር ስነ ስርዓት ተካፋይ እንደሚሆኑ ገልፀውልኛል፡፡ በስነ ስርዓቱ ላይ የተገኘው የክመንት ማህበረሰብም የሟች ቤተሰቦች ያዘጋጁት ድግስ ይበላሉ ይጠጣሉ፡፡

ቄሶች በስነ ስርዓቱ ላይ የሟች ነብስ ወደ ገነት እንድትገባ ለእግዚአብሔር ጸሎት ያደርሳሉ፡፡ ህብረተሰቡ የሟችን ነብስ ወደ ሌላው ዓለም የሚሸጋገር መሆኑን በማመመን "ነብሱን አደራ ይማረው" ይላሉ (ቃለ መጠይቅ፣ ቄስ ቢምር አስናቀው12/06/2011)፡፡

> *የክመንት ማህበረሰብ በእምነታቸው ላይ አንድ ሰው ከሞት ስነ ስርዓት ጀምሮ እስከ ሁለተኛው የቀብር ስነ ስርዓት የሚያደርጉት ክንውኖች ላይ ነው፡፡ በአንድ እግዚአብሔር ነው የምናምነው ይሉና ሃይማኖታቸው የተለያዩ መለኮታዊ እምነቶች የታከሉበት በመሆኑ አማልክት ነበሯቸው ለማለት ያስደፍራል፡፡ አማልክቶቻቸው የሰማዩን እግዚአብሔርን፣ ቅዱሳን የባህል ጀግኖችን፣ ሌሎች ቅዱሳንን እና ቆሌዎችን ያካትታሉ" ይላሉ፡፡*

ስለዚህ በክመንት እምንት የሚሰሙት እንስሳቶች ለአምልኮተ ስነ ስርዓት እንደሚውሉ ያመለክታል፡፡ በመጨረሻም በሁለተኛው የለቅሶ ስነ ስርዓት ላይ የተሳተፉት ምዕመናን ከእሁድ 7 ሰዓት ጀምሮ እስከ 12፡00 ሰዓት ሲበሉ፣ ሲጠጡ ከዋሉ በኋላ ማታ ደግሞ በድጋሚ የዕራት ዝግጅት ከሁለት ሰዓት እስከ ለሊት 4፡00 ሰዓት ይበላሉ ይጠጣሉ፡፡

በመጨረሻም ፍትሀቱን ላከናወኑ ቤተሰቦች ምርቃት (ገወተን) ስነ ስርዓት ይደረግላቸዋል፡፡

| ክመንቲሳ | አማርኛ |
| --- | --- |
| ቲኑረስ ጋሻ ሸቢን፣ ቲኑረስ ኀበብ | ልጆቻችሁ የሚታዘዙ፣ የሚያድጉ ይሁኑ |
| ከብትስ ይተረ ኸብዘ ከበንታሊያ ሸቢብ | ከብቶቻችሁ የሚረቡ ያድርጋቸው |
| ከመት ኸበብዛ ሸቢን | ላሞቻችሁ የሚታለቡ ያድርጋቸው |
| ቢርስ ከብታ ሸቢን | ከብቶቻችሁ የሚባረክ ያድርገው |
| ቢንርስ ስበስን ስረሳ ሸቢን | ንብረታችሁ የሚባረክ ያድርገው |
| አሸስ ከመግብትዮን ሸቢን | የቅጠሉን ያህል ሲሳይ |
| ጉሮኳ ዕድሜ ዮም ሸቢን [2] | የአውራ ጎዳናውን ያክል ዕድሜ ይስጣችሁ |

በምርቃት ስርዓቱ ላይ የተነሱት ዋና ጭብጦች ሰዋዊ ጉዳዮችን አብዝተው የያዙ ናቸው፡፡ ህፃናት ተወልደው እንዲያድጉ፣ ለገበሬው ህይወት ወሳኝ የሆኑት ከብቶች በጤና እንዲረቡና እንዲታለቡ፣ በሰው ልጆች ህይወት ሰላም እንዲሰፍን፣ ሀዘን እንዲርቅና ሰው እንዳይከፋ፣ አርሶ አደሩ ምርቱን አምርቶ ገበያው ጥጋብና ተድላ እንዲሆን ይለመናል፡፡ ይህ ደግሞ በክመንት ማህበረሰብ ማህበረሰቡ እርስ በርስ በመተሳሰብ ላይ የተመሰረተ እና አዎንታዊ አስተሳሰብ የነገሰበት አካባቢ እንዲፈጠር ትልቅ ሚና ያለው ነው፡፡ መልካም የማይባሉ እሴቶች ከማህበረሰቡ እንዲርቁ በተቃራኒው ደግሞ መልካም የሚባሉት እንዲበራከቱና እንዲስፋፉ ያግዛል፡፡

በአጠቃላይ የሙት ዓመቱ ስነ ስርዓት የሚከናወነው ራሱን ችሎ በወንዝ ዳር ነው፡፡ በወንዝ ዳር የሚደረገውም ለውሃው እንዲቀርብና ለአደራ መስዋዕትነቱ እንዲደርሰው እንዲሁም ነፍሲቱም በዓመቱ ስትመጣ የፈለገችው ተዘጋጅቶ ሲኖር ለቤተሰብም፣ ለጎረቤትም፣ ከባድማውም ልጅ ይኖርበታል የተመቻቸ ኑሮም ይኖራሉ ተብሎ ውክልና ይሰጠዋል፡፡

ከላይ ለተጠቀሰው የፀሎት ስነ ስርዓት ወ/ሮ አዛኑ አደም እንዲህ በማለት አስረድተውኛል፡፡

> *ፀሎቱን ሲያደርሱ ያለው ወይም የቆመው ማህበረሰብ መልስ ሰጪ ይምሰል እንጂ፣ መልስ ተቀባዮች በዓይን የማይታዩ የይደራ (የእግዚአብሔር) መልእክተኞች እንደሆኑ እሳቤ ያደርጋሉ፡፡ ሁልጊዜም ቢሆን የህገ ልቦና ቁሶች ፀሎትም ይሁን ምርቃት ሲያደርሱ በዙሪያው የሌሉ ግን ቶሎ መልስ እንዲሰጣቸው አድርገው አዘውትረው ይጠቀማሉ፡፡ ጥያቄያቸውም መልስ ሲያገኝ እና ሲከናወንላቸው ይታያል በማለት የፀሎቱን ትርጉም ገልፀውልኛ(10/06/20/፡፡*

[2] ከዚህ የሚቀጥለው ምርቃት በአባሪ ሁለት ላይ ተካቷል፡፡

# 5 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በክመንት ማህበረሰብ "በለቅሶ ስርዓት ክዋኔ" ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህም የለቅሶ ስርዓቱ ክዋኔ ምን ይመስላል? በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚያዙ ቁሶች ትዕምርት ምንድን ነው? በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሙሾ ቃል ግጥሞች ምን ያህል ያተኩራል? ከለቅሶ ስርዓቱ ጋር ተያይዘው የሚታዩ አምልኮት ምን ምን ናቸው የሚሉትን በመመልከት መልስ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ በክመንት ማህበረሰብ ለህፃናት የሚደረግ ከቅድመ ሞት እስከ ድህረ ቀብር የለቅሶ ስርዓትና ለአዋቂዎች የሚደረግ የለቅሶ ስርዓትን ከቅድመ ሞት እስከ ሙት ዓመት ወይም ተዝካር በምዕራፍ አራት ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

በህገ ልቦና እምነት ተከታዮች አንድ ሰው የተለያየ ህመም ሲገጥማቸው የሚጠቀሙበት ባህላዊ መድኃኒቶችን ከቀንድ ከብቶች እና ከእጽዋቶች በተዘጋጀው እንደሆነ ከጥናቱ መረዳት ተችሏል፡፡

በህገ-ልቦና አንድ ሰው ሲሞት የአከፋፈን ስርዓቱ ይለያይ እንጂ የለቅሶ ስርዓቱ ግን ለሁሉም የተሰጠው ትንሽ፣ ትልቅ፣ ወንድ፣ ሴት ሳይለይ እኩል ነበስ የተቸረ መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ በማህበረሰቡ በህይወት እያሉ መተዛዘን፣ መረዳዳት፣ መተጋገዝ እንጂ ከሞቱ በኋላ ማልቀስ አደራን /እግዚአብሔርን/ መፈታተን ነው የሚል ጥቁምታ ከጥናቱ መመልከት ተችሏል፡፡

በክመንት ሃይማኖት ሰው ሲሞት ሁለት ትልልቅ ቁርባን ያላቸው እና አንድ ወጣት ሆነው አስክሬኑን በቀይ ክር ገንዘው በብሳና ቅጠል አጥበው በቀይ ክር ገንዘው በጀንዴ፣ በአቡጀዴና በሰሌን እንደሚከፍኑ ጥናቱ ያሳያል፡፡ በባህሉ ሰው ሲሞት ፀጉር መላጨት፣ ፊት መቧጠጥ፣ ደረት መምታት የሚባል የላቸውም፡፡ ይህን ማድረግ በሰማይ በምድር ኃጢያት እንደሚያስገባቸው በጥናቱ ተገልጿል፡፡ የቀብር ስነ ስርዓታቸውም በአንድ ቦታ በተሰበሰበ ደን/ድግና/ በሚባል ቦታ የቀብር ስነ ስርዓቱ እንደሚከናወን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ በህገ-ልቦና እምነት አስክሬንኑን ገንዘው ከአልጋው ወደ መሬት ደረቅ ሳር ጎዝጉዘው ካስተኙት በኋላ በጥንጁት ቅጠል፣ በክትክታ ቅጠል በወይራ ቅጠል በማጤስ አስክሬኑን እያጠነ ፍትሃት ሲያከናውኑ ጥናቱ ተመልክቷል፡፡

በለቅሶው ስነ ስርዓት ላይ አስክሬኑን የሚሸከሙት "ካስ" /ቁርባን/ ያላቸው ጎልማሳ ወንዶች እንደሆኑ በጥናቱ ተገልጿል፡፡ በህገ ልቦና ለለቅሶ ስነ ስርዓትም ይሁን ለሌላ ፀሎት ስነ ስርዓት ሲታሰብ የሚቀርበው መስዋዕት ያላጠቃ ቀይ /ነጭ/ ወይፈን፣ ቀይ/ ነጭ/ በግ እንደሆነ በጥናቱ

ተረጋግጧል። በሟች በለቅሶ ስነ ስርዓት ላይ የሟች ወንድ ልጅ በነጭ ጨርቅ ጠቅልሎ በመያዝ ሲያለቅስ፣ ሴቶች ደግሞ ካባ ለብሰው፣ የሟችን የወገብ ሙቀት ከአንገት በማድረግ እና የተለያዩ ጌጣጌጦችን በመያዝ ሲያለቅሱ ተስተውሏል።

በክመንት ባህል ከቀብር ስነ ስርዓት በኋላ የሟች ነብስ እስከ ሰለስቱ በቤቱ ጓሮ ዙሪያ ስለምትቆይ የከመዘናው ቄስ /አጋኘር ቄሱ/ ቀይ በግ ወይም ያላጠቃ ወይፈን ቀድሞ ምላሱን በመቁረጥ በብሳና ቅጠል ጠቅልሎ አመናውን በመጣል እንደሚያቋድስ በጥናቱ ታይቷል። ሀዘንተኞችም ሰባት እንጀራ በአዋዜ ቀብተው ለሰልስቱ የቀቀለ ንፍሮ ይዘው በመሄድ የሟችን ስም ለነዲያን በመናገር የሟችን ነፍስ ይማር እንደሚያስብሉ በጥናቱ ታይቷል።

በህገ ልቦና እምነት አንድ ሰው ሲሞት ነፍስ ሲያልፍ ይለቀሳል፣ አስክሬን ከኖረበት ቤት ሲወጣ ይለቀሳል። ግብዓተ መሬት ሲፈፀም እንደሚለቀስ በጥናቱ ተስተውሏል። በክመንት ባህል መሰረት ትኩረት የሚሰጠው "በሰው አዕምሮ ውስጥ የሚገኝ ተፈጥሯዊ ህግ መሆኑንና ምንም ዓይነት ህግ ሳይኖር በህሊናቸው የሚዳኙ መሆናቸውን ጥናቱ ተመልክቷል።

በማህበረሰቡ ሙት ዓመት /ተዝካር/ ሲደረግ ጠላውን ባለሙያ ቆራቢ ሴት እንደምታዘጋጅ እና የጠላውን ቅደም ተከተል ጠብቃ በተቀደሱት ሦስት ቀናቶች እሁድ፣ ማክሰኞ እና ሀሙስ እንደምታዘጋጅ በጥናቱ ተገልጿል።

የቀሩት ቀናቶች ቅዳሜ፣ ሰኞ፣ ረቡዕ እና አርብ ቀን ሰው እንኳን ቢሞት አስክሬኑ ወዲያውኑ እንደሚቀበር፤ ፍትሃትም እንደማይደረግለት "በአደራ" ትዕዛዝ የተላለፈበት ነው። አራቱ ቀናቶችም በህገ-ልቦና እምነት፣ ችግር፣ የሚበዛባቸው ጎደሎ ቀናቶች ናቸው የሚል እሳቤ በጥናቱ ተረጋግጧል።

ቆራቢዋም ከብቅልና ከአትኳሮ ቅጠል ያዘጋጀችውን ጠላ ለ"ማጅም" /ለሽማግሌዎች/ ካስመረቀች በኋላ አደረይኪ ከሰማይ ወደ ምድር ሲመጣ ይዟት በመጣው "ምሰኛድባ" /ወርቅ ሰቀል/ በአመት አንድ ጊዜ የሚደረገው ሙት ዓመት በቅል በተዘጋጀ ማውራ እንደሚጠጣ በጥናቱ ተገልጿል። የሙት ዓመቱ ስርዓት ሲካሄድ የከመዘና ቄሶች ከሟች መቃብር ላይ እሁድ በጠዋት ሄደው ደሙን አፍስሰው እንደሚያመለሱ ነው የተነገረው። ከመዘና ቄሶችም ከተመለሱ በኋላ የተዘጋጀላቸውን ምግብ በልተው ጠጥተው ከዳስ ውስጥ ሆነው የሟችን ስም በመጥራት የፍትሃቱን ስነ ስርዓት እሁድ እስከ ስድስት ሰዓት ነብሲቱን ማርልን ማርልን.... የመሳሰሉትን በማለት ፍትሃቱን እንደሚያከናወኑ ተገልጿል።

የሙት ዓመቱ ስነ ስርዓትም ወንዝ ዳር እንደሚከናወንና ለሟች መስዋዕትነቱ እንዲደርስና ለቀሪው ማህበረሰብ ምቹ የሆነ የኑሮ ሁኔታ እንዲፈጥርለት፣ ከባድማው ልጅ እንዲኖርበት በመጨረሻም የሙት ዓመቱን ላዘጋጁት ቤተ ዘመዶች የምርቃት ሥነ ስርዓት /ገወተን/ ይደረጋል፡፡ ከዚህ ክውን በኋላ የመጣው ለቀስተኛ "ፈርስ ረግጦ ይውጣ" በማለት የተዘጋጀውን ምግብ እና መጠጥ ካበሉ ካጠጡ በኋላ ከመዘናው ቁስ የተረፈውን ስጋ ለእያንዳንዱ ሰው በብሳና ቅጠል ጠቅልሎ ከሰጠ በኋላ ሁሉንም ታዳሚ "በእጃቸው መዳፍ ኪዱስ ምንስሻናውንሻን" /እግዚአብሔር ምስጋና ይገባህል/ በማለት እያሳለሙ እንደሚሸኙ ጥናቱ ያስረዳል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ለማ ንጋቱ (PhD)፡፡ "በደቡብ ጎንደር ዞን የለቅሶ ስርዓት ክወና"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለሦስተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ፣ 2006፡፡

ማህሌት ሁነኛው፡፡ "ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በክመንት ማህበረሰብ የቀረበ፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለሦስተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ፣ 2005፡፡

ማናዬ እንግዳወርቅ፡፡ "በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ንጽጽራዊ ጥናት፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ዲማጽ፣ 2005፡፡

ሞገስ ሚካኤል፡፡ "በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ስነ ስርዓት፣ በስርዓቱ ላይ የሚካሄድ ቀረርቶ፣ ፉከራ፣ ክዋኔው፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፣ 2002፡፡

ሰለሞን ተሾመ፡፡ *ፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ፡፡* አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ.የተ.የግ.ማ፣ 2007፡፡

ሰማልኝ ክንዴ፡፡ *ክመንቲሳ-ብላሺሳ-እንግሊሳ መዝገበ ካልክ፡፡* ጎንደር፣ በፍሬሽ አይል ማተሚያ ቤት የታተመ፣ 2010፡፡

በሪሁን መንግስቱ፡፡ "በደብረ ታቦር ከተማ የወዮታና የፉከራ ግጥሞች ክዋኔና የይዘት ትንተና፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች፣ ስነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ዲማጽ፣ 2004፡፡

ባዩ ቦጋለ/ ተርጓሚ/፡፡ *ቅመንት-አረማዊ-አሪታዊ- ኢትዮጵያዊ ገበሬ፡፡* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ፣ 1993፡፡

ነጋ ጌጤ፡፡ *የቅማንት ህዝብ ታሪክ፡፡*ጎንደር ዳሽን ማተሚያ ቤት፣1993፡፡

አለቃ ታዬ፡፡ *የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ በአጭር ቃል የወጣ፡* አስመራ፣ ወንጌያት ማህበር ማተሚያ፣ 1920፡፡

አብነት ሰሎሞን፡፡ “የቅማንት ማህበረሰብ ማንነት በዝርው የቃል ተረኮቻቸው፡፡” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች፣ ስነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ዲማጽ፣ 2005፡፡

የዝና ወርቁ፡፡ “በሰሜን ጎንደር ዞን በጭልጋ ወረዳ በአይከል ከተማ በምትገኘው የ “እሜቴ አይከል” እምነትና ስርዓተ ከበራ” ላይ ነው፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 2007፡፡

የመጽሐፍ ቅዱስ መዝበ ቃላት፡፡ *የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር 11ኛ ዕትም፣* 2008 ዓ.ም፡፡

ያለው እንዳወቀ (ፕሮፌሰር) *የምርምር መሰረታዊ መርሆዎች እና አተገባበር፡፡ ሦስተኛ* እትም አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡

ደስታ ተ/ወልድ፡፡ *አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡* አዲስ አበባ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ *የሥነ-ቃል መምሪያ፡፡* ኢንተርናሽናል ጀርመናዊ የጎልማሶች ትምህርት መረዳጃ ተቋም *ታተመ*፡፡ 1991፡፡

Bauman, Richard, ed. *Folklore cultural performances and popular Entertainment.* New York: Oxford University Press, 1992.

_________________ Story, *Performance, p.77 and Event.* Contextual Studies of Oral Narrative. 1986. USA: Cambridge University Press, 1988

_________________. *Verbal Art as performance*. American Anthropologist, Association, University of Texas at Austin New Serires, vol. 1975. P.293.

Blanc. H (1968). *The Native races of Abyssinia*. Transaction of the Ethological Society of London.

Bruce. J. (1868). *Travel to discover the source of Nile.* Edinburgh: G. and J. Robinson, 1970.

CSA. (1994). *Population and housing Census of Ethiopia,* Results at Country Level vol. 1, Statistical Report, Addis Ababa: central Statistical Office.

Finnegan, Ruth. *Oral Poetry, its Nature, Significance and Social Context.* New York: Cambridge University Press, 1977.

___________ *Oral Traditions and Verbal Arts*. London and New York, Routlege, 1992.

Goldstin, Kenneth. S.A *Guide for Filed Workers In Folklore.* Pennsylvania Folklore Associates Inc, 1964.

Gamst, F.C. *The Qemant Agaw of Ethiopia: A study in culture Change of A pagan Hebraic culture*. Unpublished PhD Dissertation, 1967.

___________. *The Qemant: A pagam- Hebraic Peasantry of Ethiopia. Cases studies in cultural Anthropology*. New York: Holt Rinehart and Wilson, 1969.

Gray. E. David. *Doing research in the real world.* Sage publications, London. Thousand oaks, New Delhi; 2004.

Hertiz, Robert. *Death and the Right Hand*. Trans. Rodney and Need ham, Claudia. Aberdeen: Aberdeen University Press. 1960.

Sims, Martha C. and Stephens, Martine. *Living Folklore*. An Introduction to the study of people and their Traditions. USA, Utah State University Press, 2005.

Zelalem Leyew. *The Kemantey Language: A Sociolinguist and Grammatical study of rang vage Replacement*. PhD. Dissertation. Rudiger koppe veriag kerlag. Loin, 2003.

___________ *Socio Linguistic Survey Report of the Kemant Language in Ethiopia*. SiL International PhD isertation. 2002.

## አባሪ አንድ፡

**የሙሾ ግጥሞች**

1. ስጡኝ ያንን ዋንጫ በእምባ እሞላዋለሁ
   በሞቴ እየተባልኩ ጠጥቼበታለሁ፡፡
2. ላይለቀስ ነው ወይ ወትሮስ ላበላ ሰው
   ላይለቀስ ነው ወይ ወትሮስ ላጠጣ ሰው
   እጁ ወንፊት ሆኖ ሰጥቶ ለጨረሰው፡፡
3. እንኳን አበላሽው እንኳን አጠጣሽው
   አልሽው ግባ ግባ
   መፈታቱ አይቀርም ቤትና ገበያ፡፡
4. ከወንድም ከእህት ጋር ብሉ ጠጡ ቀረ
   ከእናት ከአባት ጋር መገናኘት ቀረ
   ያላሰብነው መጥቶ ተበታትኖ ቀረ፡፡
5. አዋጋሽ አበራ ቤትሽ ይሰናዳ
   ሳይበላ ወጣልሽ የመጣው እንግዳ፡፡
6. የላሞችሽ ጌታ የበሮችሽ ጌታ
   ወዴት ወረድ ወረድ የመሬት መኝታ፡፡
7. በ8ኛው ሺህ በውራውራው
   እናት መድኃኒት ናት ለምዳስሰው፡፡
8. ሀዘናችሁ ገና እኔ ልንገራችሁ
   ወልዳችሁ ስትተኙ ማነው ሚያርሳችሁ፡፡
9. አያችሁ እናንተ የክመንት ልጅ ተገፍተው ኑረው
   ከቋራ ተነስተው ዞሮ እስከመተማ
   ሲፈልጉ አየሁኝ ቋንቋቸው ጠፍቷቸው
   ቄስ ሙሉነህ መርሻ አኑሮ ሰጣቸው፡፡
10. አዬ እናታለም እናቴ ልበልሽ
    በእግዜር እጅ ተይዞሽ አላመላልስሽ፡፡
11. ያንን ጥሩ ጠጁ ያንን ጥሩ ጮማ በልቼበታለሁ
    በራሴ ሀዘን ይገፔ በዓይኔ እቀዳዋለሁ፡፡
12. እናቴ ልበልሽ ጉርሻዬ ልበልሽ ማጫዬ ልበልሽ
    ከጠራሁት ሁሉ የትኛው ልበልሽ፡፡
13. እንዴት ነው መንደሬ ብሳናው እንዶዱ
    አዳራሹንማ እየዘጉት ሄዱ፡፡
14. ከሁሉም ከሁሉም እናት ትሞታለች
    ከማጀት አብልታ አልበላም ትላለች፡፡

## አባሪ ሁለት

## ለሙት ዓመት አዘጋጆች የተደረገ የምርቃት ስነ ስርዓት

**ክመንቲሳ**

ቲትረስ ጋሻ ሸቢን፣ ቲትረስ ጎበብ

ከብትስ ይተረ ኸብዘ ከበንታሊያ ሸቢብ

ከመት ኸበብዛ ሸቢን

ቢርስ ከብታ ሸቢን

ቢንርስ ስበስን ስረሳ ሸኪን

አሸስ ከመግብትዮን ሸቢን

ጉሮኳ ዕድሜ ዮምሸቢን

ጤና ሽይንቻ ጤይነ

ችግርስ ተቤትስ ኻቻላ ሸቢን

ይልተትስ ፏዋ ኼራና ሸቢን

ይትጎዝጉሰስ ኸተና ሸቢን

ተመልኪሰ ቴዎሪጋን ሸቢን

አልጋስ ስሪቲፋንጋ ሻቢን

ይበልስ ችግርስ ትበላ ሻቢን

ጆርኸላ ቦታ ሸዋን ሻቢን

ኹረስ ቦታ ሸዋን ሻቢን

ቢርስ ቦታ ሸዋን ሻቢን

ምርትስ ቦታ ሸዋን ሻቢን

አረስ በኾነ ሸዋን ሸቢን

አገርስ አማን ሸዋን ሻቢን

ኻየስ ብትያ ሸቢን

ዳኛስ ደፈርሳ ሸዋን ሸቢን

ተኾረኾረስ ሸመርሺነስ ሸቢን ሸወን

ተኾሳዬ ታያቻ ሻቢን

**አማርኛ**

ልጆቻችሁ የሚታዘዙ፣ የሚያድጉ ይሁኑ

ከብቶቻችሁ የሚረቡ ያድርጋቸው

ላሞቻችሁ የሚታለቡ ያድርጋቸው

ከብቶቻችሁ የሚባረክ ያድርገው

ንብረታችሁ የሚባረክ ያድርገው

የቅጠሉን ያህል ሲሳይ

የአውራ ጎዳናውን ያክል ዕድሜ ይስጣችሁ

ጤና ለሌለው ጤናውን ይስጠው

ከቤታችሁ ችግር የማይገባ ያድርገው

አይናችሁ ከሚያነባው ያውጣችሁ

ሆዳችሁ ከሚያዝነው ያውጣችሁ

መልካችሁ የማይጠም ይሁን

አልጋችሁ የማይሰበር ይሁን

ከቤታችሁ ችግር አይግባ

የእንቦሳ ቦታ ያድርገው

የልጅ ቦታ ያድርገው

የበሬ ቦታ ያድርገው

የምርት ቦታ ያድርገው

እህል የሚበቅልበት ሀገር ይሁን

ሀገሩን አማን ያድርገው

ገበያውን ጥጋብ ያድርግልን

የዳኛ ርሀብ አይስጠን

ከተወረወረ ጦር ያውጣችሁ

ይዝም ኹራዝ ግልገላ ሸቢን

ኸመነብስ ይሙአ ሸቢን

አሸስ ኹዋ ኹዋ ሸቢን

ዕድሜ ቸኾለታ ሸቢን

ኻመት ነፈቻ ሸቢን

ይገዛ ሲሳይስ ለቻዘዮብ ሸቢን

ታገለ አሻኹን ሸቢን

ዝለን አሻኹን ሸቢን

ተኾረኾረ አይኻ ሸቢን

ስሚኻ ግብርኻ ሸቢን

ሸኽምኻይዝ ብዘኻ ብዛወስ ብዝኻ ሸቢን

ከተዘገበ ጠመንጃ ያውጣችሁ

ከባለጌ ጋር አያውላችሁ

ወልዳችሁ ሳሙ

አሽታችሁ ቃሙ

በእድሜ አይቸኩልባችሁ

ከሲሳይ አይንፈጋችሁ

ከሲሳይ ሰፊውን ይስጣችሁ

የታገለ አይጣላችሁ

የሮጠ አይቅደማችሁ

የወረወረ አይምታችሁ

የሾመ አይሻራችሁ

አፉን ከከፈተ እባብ ያውጣችሁ

## አባሪ ሦስት ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች

| ተ.ቁ | ስም | የመኖሪያ አድራሻ | ዕድሜ | የሥራ ሁኔታ | ጾታ | መረጃውን የሰጡሰበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ወንበር አማረ ሙሉነህ | ጃልሽም | 62 | የህገ ልቦና ሃይማኖት መሪ | ወ | 05/06/2011 |
| 2. | አቶ ኪ/ማርያም አበራ | አይከል | 45 | የወ/ጽ/ቤት/ኃላፊ | ወ | 06/06/2011 |
| 3. | አቶ አስቻለው ቀናው | ጮንጮቅ | 35 | የመንግስት ሰራተኛ | ወ | 09/06/2011 |
| 4. | አቶ እንደሻው ጠጋው | ጃልሽም | 69 | አርሶ አደር | ወ | 17/06/2011 |
| 5. | አቶ አብርሃም ጉበኛ | ጃልሽም | 37 | የመንግስት ሰራተኛ | ወ | 18/06/2011 |
| 6. | ቄስ ቄጡ አያሌው | ድኩላጌ | 68 | ከመዘና ቄስ | ወ | 12/06/2011 |
| 7. | ቄስ ቢምር አስናቀው | ድኩላጌ | 65 | ከመዘና ቄስ | ወ | 13/06/2011 |
| 8. | አቶ በየነ የሽዋስ | ጃልሽም | 32 | የመንግስት ሰራተኛ | ወ | 18/06/2011 |
| 9. | እማሆይ አዛጉ አደመ | ጮንጮቅ | 76 | የቤት እመቤት | ሴ | 13/06/2011 |
| 10. | ቄስ ስመኘው አለማየሁ | ሰራግና | 73 | ከመዘና ቄስ | ወ | 13/06/2011 |

## አጋዥ መረጃ ሰጪዎች

| ተ.ቁ | ስም | የመኖሪያ አድራሻ | ዕድሜ | የሥራ ሁኔታ | ጾታ | መረጃውን የሰጡሰበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አቶ ማሩ ክፍሌ | ጮንጮቅ | 66 | አርሶ አደር | ወ | 09/06/2011 |
| 2. | እማሆይ በተሀ ደመቀ | ጮንጮቅ | 78 | የቤት እመቤት | ሴ | 10/06/2011 |
| 3. | አቶ ብርሃኑ አወቀ | ጀኑዳ | 74 | አርሶ አደር | ወ | 04/06/2011/ |
| 4. | አቶ ሲሳይ ጣው | ጀልሻም | 45 | አርሶ አደር | ወ | 18/06/2011 |
| 5. | አቶ ኖራ በሪሁን | ጀኑዳ | 55 | አርሶ አደር | ወ | 17/06/2011 |

## አስተባባሪ እና አስጎብኚዎች

| ተ.ቁ | ስም | የመኖሪያ አድራሻ | ዕድሜ | የሥራ ሁኔታ | ጾታ | መረጃውን የሰጡሰበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አቶ ቢያድግልኝ ሞላ | ምርት አምባ | 45 | አርሶ አደር | ወ | 05-18/06/2011 |
| 2. | አቶ መልካሙ ሞላ | ምርት አምባ | 30 | አርሶ አደር | ወ | 05-18/06/2011 |

## አባሪ አራት
## ቃለ መጠይቆች

### የግል ቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች

1. ቅማንት ማለት ምን ማለት ነው? መነሻውስ ከየት ነው?
2. የለቅሶ ስርዓት ለወንድ፣ ለሴት፣ ለትንሽ፣ ለትልቅ ልዩነት አለ ወይ?
3. በቅማንት አንድ ሰው ሲታመም በባህላዊ መንገድ ህክምና ይደረግለታል?
4. አስክሬን በሳጥን ነው ወይ የሚቀበረው? ማነው ሳጥኑንስ የሚያቀርበው?
5. ለቀብር ስነ ስርዓቱ ጉድጓድ ሲቆፈር ከየት ወደየት ነው?
6. በለቅሶ ስርዓቱ ላይ ሀዘንተኞች ምን አይነት አልባሳት ያደርጋሉ?
7. በለቅሶ ስርዓቱ ላይ ምን ምን ቁሳቁሶች ይይዛሉ?
8. ከቀብር በኂላ የምግብና የመጠጥ መስተንግዶ ያደርጋል? ምን ምንስ ይቀርባል?
9. ምግብ መጠጡን ማን ነው የሚያዘጋጀው?

### የቡድን ውይይት ጥያቄዎች

1. በክመንት አንድ ሰው ሊሞት ሲል የኑዛዜ ስርዓቱ በምን መልኩ ይከናወናል?
2. አንድ ሰው ከሞተ በኂላ የአገናነዝ ስርዓቱ እንዴት ይከናወናል አስክሬኑስ ለስንት ቀን ይቆያል፣ ማቆያ ዘዴውስ እንዴት ነው?
3. በክመንት አንድ ሰው ሲሞት አስክሬኑ እንዴት ይከናወናል፣ የሚደረገው የክፈን ልብስ የሚያወጣውስ ማነው?
4. በክመንት የቀብር ቦታዎች እንዴት ይዘጋጃሉ፣ በእድሜ፣ በማህበራዊ ደረጃ ወይም በሌሎች ምክንያቶች የቀብር ቦታዎች የሚለዩበት ሁኔታ አለወይ?
5. ከቀብር በፊት በቀብር ዕለትና ከቀብሩ በኂላ የሚፈፀመው ባህላዊ ስርዓቶች ምንድን ናቸው?
6. የተጠመቁና ያልተጠመቁ ማህበረሰቦች ከለቅሶ ስርዓቱ ጋር ያላቸው ተያያዥነት እንዴት ይገለፃል?
7. በለቅሶ ስርዓቱ ላይ ወንድና ሴት ተለይተው ይቀመጣሉ ወይ?
8. በለቀሶ ስርዓቱ ላይ የማህበረሰቡ ተሳትፎ ሀዘንተኞችን ለማፅናናት ምን ምን ያደርጋል?
9. በለቅሶ ስርዓቱ ላይ ለሀዘንተኞች የገንዘቡንም ሆነ የቁሳቁስ ወጪዎች ይደረጋሉ ወይ? በማንስ ይሸፈናል? ለምን?

# ማረጋገጫ

እኔ ሜሮን ሞላ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ፕሮግራም በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ተማሪ ያቀረብኩት ጥናት የራሴ መሆኑን የተጠቀምኩባቸው ተዛማጅ ጽሑፎች በአግባቡ የተጠቀሱ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ----------------------------------------

ፊርማ --------------------------------------

ቀን ----------------------------------------